አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# የግጭት አፈታት ሥርአት ክዋኔ በጌዴኦ ብሔር

በ
ሕሊና ስብስበው

ሰኔ 2005
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረምረቃ ትምህርት ቤት
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚይኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

# የግጭት አፈታት ሥርአተ ክዋኔ በጌዴኦ ብሄር

በ

ሒሊና ሰብስበው

ሰኔ 2005

አዲስ አበባ

# የግጭት አፈታት ሥርአተ ክዋኔ በጌዴኦ ብሄር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚይኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ
ጥናት

በ

ሕሊና ሰብስበው

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ሰኔ 2005

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚይኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር

# የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ በጌዴኦ ብሄር

በ

ህሊና ሰብስበው

2005 ዓም

| የፈተና ቦርድ አባላት | ፊርማ |
|---|---|
| አማካሪ<br>አቶ ዘሪሁን አስፋው | |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| የውጭ ፈታኝ | |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ADDIS ABABA ILS LIBRARY

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት ምስጋና የባህሪ ገንዘቡና የአገልግሎቱ ምንዳ  የሆነው እግዚያብሔር ከእናቱ ከኪዳነምህረት ጋር ምስጋና ይግባው፡፡ ይህ ጥናት ከርእስ መረጣ ጀምሮ አሁን ያለበትን ቅርጽ እስኪይዝ ድረስ የበርካታ ሰዎች ድጋፍ አለበት፡፡ ከሁሉም በፊት አማካሪየ አቶ ዘሪሁን አስፋው ላደረጉልኝ እገዛ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ለጥናት የሚሆነኝን አቅጣጫ በመጠቆም ለተባበራችሁኝ ለጌዴኦ ዞን ልዩ ልዩ ሴክተሮች፣ መረጃ ያለስስት የለገሱኝ የጌዴኦ ብሄር የሀገር ሽማግሌዎች የገዳ ስርአት ባለስልጣናትና የብሄሩ የሃይማኖት አባቶች ምስጋናየና አክብሮቴ እጅግ የበዛ ነው፡፡ በተለይም መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ከጎኔ የነበራችሁት አቶ ጥላሁን እብዶ፣ ሀይቻ ጀቦ ኩራ ፣ አቶ ምጃኔ ጎበና፣ አቶ ኢቹማ፣ አቶ ቴሮ ጃርሶ፣ አቶ ቹምብሮ ሃለቻዮና የተለያዩ ጥቆማዎችን የሰጡኝ አቶ እሸቱና አቶ በላይ አገዘን ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ለመመረቂያ ጽሁፍ ዝግጅቴ የሚሆነኝን ቁሳቁስ በማሟላት፣ የሞራል ድጋፍ በመስጠት አብራችሁኝ ስለነበራችሁ ወንድሜ ሰሎሞን ሰብስበው፣  አባቴ መምህር ሰብስበው እውነቱ፣ እናቴ ሻሼ እንየው፣ እህቴ ብርቱካን እውነቱ፣ ማስተዋል(ማዮ)ና ሌሎች ቤተሰቦቼ ጨርሼ ማየታችሁ ድላችሁ ይሁን፡፡ በመረጃ ስብሰባየ ወቅት በጣም ብዙ እገዛ ያደረጋችሁልኝ አበልጆቼ ሰናይትና ጥላሁን ከነንደኞቻችሁና ወዳጆቻችሁ ምስጋና ያንሳችኋል፡፡ ተመስገን በዚህ የመመረቂያ ጽሁፍ ውስጥ ያለህን አስተዋጽኦ ሳስበው ደግነትህ ይገርመኛል፡፡ ባልንጀራየ ሶሎሞን ተሾመ  ደግሞ ይሂ መሰለኝ አንተ የተመኘኸው ጥናት፡፡ አማረ አበጀ ትልቅ ነገር በማድረግ ዛሬም ከጎኔ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ፡፡ የ2005ዓ.ም ተመራቂ የክፍል ጓድኞቼና ስማችሁን ጠቅሸ የማልጨርሰው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ አሻራችሁ የሰፈረ ወዳጆቼ ሁሉ እግዚያብሔር ይስጥልኝ፡፡

በመጨረሻም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለጥናቴ የሚሆነኝን በጣም ትንሽ ገንዘብ ስለሰጠኝ፤ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪዬን እንድማር እድሉን አመቻችቶ ደመወዝ ስለቆረጠልኝ አመሰግናለሁ፡፡ በግጭት አፈታት ወቅት በቪዲዮ እና በድምጽ መቅረጫ ስቀርጽ ያመናችሁኝና ስኬት እንዲገጥመኝ በምርቃታችሁ ያበረታችሁኝ  የጌዴኦ ብሄር አባላት ሁሉ እግዚያብሔር ያክብርልኝ፡፡

## ሙዳዩ ቃላት

ሀይቻ፡- የሶንጎ አስተዳዳሪ

ሆላ፡- የተሰወረን ወንጀለኛ ለማግኘት የሚደረግ እርግማን

ላንጤ፡- በደንበር መካከል የሚተከል ተክል

ሶንጎ፡- በጌዴኦ ብሄር የሚገኝ ጎጆ ሲሆን ሀይማኖታዊ እምነታዊና አስተዳደረዊ ሁኔታዎች ማስኬጃ

ሮጋ፡- ጌዴኦ የተዋቀረበት የአስተዳደር ክልል

ባሌ፡- የጌዴኦ ብሄር አባል የሆነ ሰው የሚያልፍባቸው የህይወት ኡደት ደረጃዎች ናቸው

አባ ገዳ፡- የገዳ ስርአት መሪ

ኢባ ሮጋ፡- የአንድ የአየር ንብረት ክልል አስተዳዳሪ

አኮማኖየ፡- የሴቶች የበላይነት ነግሶበት ነበር እየተባለ የሚነገርለት እማዊ ስርአት

ጎንዶሮ፡- ከባባድ ግጭቶች ሲፈጠሩ ለመፍታት የሚካሄድ ስርአተ ክዋኔ

ገዳ፡- የጌዴኦ ብሄር የሚተዳደርበት ፖለቲካዊ ሀይማኖታዊና ማህበራዊ አስተዳደር

ጎሳሎ፡- የጎሳ አስተዳደርን መሰረት ያደረገ የአስተዳዳር ስርአት

# አበርክቶ

በጌዴኦ ገዳ ስርአት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን ትርፉን ሳይሆን ዋናውን ጊዚያችሁን ለማህበረሰባችሁ ሰላምና መረጋጋት ለምትሰጡት ሃዩዎችና ወዩዎች አበረክታለሁ፡፡ ከናንተ ጋር በቆየሁባቸው ጊዚያት ደግነት፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ ሰላማዊነት፣ አርአያ መሆንን፣ ፈረሀ እግዚያብሔርን፣... ተምሪያለሁና ይህች ጽሁፌ ለታላቅነታችሁ እውቅናን ትለግስ፡፡ አከብራችኋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ በሚል ርእስ የተደረገው ጥናት ዋና አላማ የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአትና ትውፊታዊነት አውዳዊ ገለጻና ትንተና ማካሄድ ነው፡፡ ይህን አላማም ከግብ ለማድረስ ኢትኖግራፊያዊ ስነዘዴን ተጠቅሚያለሁ፡፡ ይህ ዘዴ ባህላዊ ጉዳዮችን ለማጥናትና የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ እውቀት ለመመርመር ከሚረዱት አይነታዊ የምርምር ዘዴዎች አንዱ ሲሆን ለኔ ጥናት ተስማሚ በመሆኑ ተመርጧል፡፡ በኢትኖግራፊያዊ ዘዴ ለሚጠና ጥናት መረጃው የሚገኘው ከመስክ በመሆኑ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅንና የቡድን ቃለመጠይቆችን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተጠቅሚያለሁ፡፡ በነዚህ ዘዴዎች ያገኘሁትን መረጃም ለመተንተንና ለመግለጽ የተጠቀምኩበት አውደ ትንታኒያዊ ዘዴን ነው፡፡

የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ በሚል የተጠናው ጥናት ንድፈሃሳባዊ መሰረት አውዳዊ ንድፈሃሳብና የስርአተ ክዋኔ ንድፈ ሀሳቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ንድፈሀሳቦች የተመረጡበት ምክንያትም አውዳዊ ንድፈሃሳብ የጌዴኦን ብሄር ግጭት አፈታት በአውዱ ውስጥ በመተንተንና በመግለጽ የማህበረሰቡን እውቀት ለመፈተሽ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ ስርአተ ክዋኔ ንድፈሀሳብ ደግሞ የግጭት አፈታቱን ስርአት እንዲሁም እምነታዊና አምልኳዊ አካሄድ ለመፈተሽ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ ጥናትም የሚከተሉትን ሀሳቦች እንደግኝት መውሰድ ይቻላል፡፡ ለጌዴኦ ብሄር የግጭት መፍቻ ሥርዓት የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች በግለሰቦችና ማህበረሰቦች የህይወት አቅጣጫ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽእኖና የብሄሩ አባላት ለግጭቶቹ ያላቸውን እይታ መሰረት ባደረገ መልኩ በሚፈጸሙት የስርአተ ክዋኔ መጠን ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ ግጭት እንላቸዋለን፡፡ ሌላው የዚህ ጥናት ትኩረት ግጭቶች የሚፈቱበት ተቋምና ማህበረሰቡ ለተቋማቱ ያለውን አመለካከት መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ተቋሙ ከሰማይ አምላክ ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ ስለሚታሰብ ማህበረሰቡ ከፍተኛ እምነት ይጥልበታል፡፡ በተጨማሪ የጌዴኦ ብሄር ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸውን ሂደቶች ከመዋቅራዊና ፋይዳዊ የስርአተ ክዋኔ ጽንሰሀሳቦች ጋር በማጣመር ተተንትኗል፡፡ ይህ ትንተና የሚያሳየውም የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአትና ክዋኔ ከአለማቀፋዊው የስርአተ ክዋኔ ቅርጽ ጋር መመሳሰሉን ነው፡፡

## ማውጫ


ርእስ ገጽ

ሙዳዬ ቃላት....................i

ምስጋና....................ii

አበርክቶ....................iii

አጠቃሎ....................iv

ማውጫ....................v

1.መግቢያ....................1

1.1. የጥናቱ ዳራ....................1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት....................3

1.3. የጥናቱ አላማ....................3

1.4. የምርምር ጥያቄዎች....................3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ....................4

1.6. የጥናቱ ወሰን....................4

1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሂዎች....................5

1.8. የጥናቱ ዘዴ....................5

1.8.1. የመረጃ ምንጮች....................6

1.8.2. የመረጃ መተንተኛና ማቅረቢያ መንገድ....................10

1.9. የመስክ ተሞክሮ....................10

2. ክለሳ ድርሳናት....................15

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ....................15

2.1.1. አውድ....................15

2.1.2. ስርአተ ክዋኔ....................21

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት....................23

3.የአካባቢው ማስተዋወቂያ ........................................................................................ 27
3.1. የአካባቢው መገኛ ........................................................................................ 27
3.2. ሕዝብ ብዛት ................................................................................................ 28
3.3. እምነት ......................................................................................................... 28
3.4. ቋንቋ ............................................................................................................ 28
3.5. መተዳደሪያ .................................................................................................. 29
4. የመረጃ ትንተና .............................................................................................. 30
4.1. በብሄሩ የሚከሰቱ የግጭት አይነቶች ................................................................ 30
4.1.1. ቀላል ግጭቶች ............................................................................................ 30
4.1.2. መካከለኛ ደረጃ ግጭቶች .............................................................................. 35
4.1.3. ከባድ ግጭቶች ............................................................................................ 40
4.2. የጌዴኦ ብሄር አስተዳደራዊ ሁኔታ ............................................................... 45
4.2.1. የአኮማኖየና የጎሳሎ ስርአት ......................................................................... 45
4.2.2. የባሌ ስርአት ............................................................................................... 47
4.3. የጌዴኦ ብሄር ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅሮች ................................................ 49
4.3.1. የቤተሰብ ጉባኤ ............................................................................................ 50
4.3.2. የአካባቢ ሽማግሌዎች .................................................................................. 50
4.3.3. የተለያዩ ሶንጎዎች ....................................................................................... 50
4.4. በብሄሩ የግጭት መፍቻ ተቋማት ወንበር የሌላቸው ቡድኖች ............................... 57
4.5. የግጭት አፈታት ስርአት ክዋኔ አውድ ............................................................. 60
4.6. የከባድ ግጭቶች ስርአተ ክዋኔ ...................................................................... 67
4.6.1. የግድያ ግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ሂደት .................................................... 67
4.6.2. የጎሳ ግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ................................................................. 75
4.6.3. የብሄር ለብሄር ግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ .................................................. 76
5. ማጠቃለያ .................................................................................................... 79
ዋቢዎች ........................................................................................................... 82
አባሪዎች

# 1. መግቢያ

የጌዴኦ ብሄር[1] እንደ አብዛኛው የሃገራችን ማህበረሰብ ትውፊቱ ቃላዊነት የሚታይበት ነው፡፡ በመሆኑም የብሄሩ ማንነት የሚታወቀው እንደ ፎክሎር ያሉ ቃላዊ ጥበብና ባህላዊ አኗኗርን ትኩረታቸው አድርገው በሚያጠኑ የጥናት መስኮች ነው፡፡ ይህ ጥናት የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ በአምስት ምእራፎች ተደራጅቷል፡፡

የመጀመሪያው ምእራፍ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን አላማ፣ የምርምር ጥያቄዎችን፣ የጥናቱን ጠቀሜታ፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ውስንነትና የመፍትሄ አቅጣጫና የጥናቱን ዘዴና የመስክ ተሞክሮን የያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው ምእራፍ ንድፈሃሳባዊ ዳራን የያዘ ሲሆን በውስጡም አውዳዊ ንድፈሃሳብንና ሪቹዋል ንድፈሀሳብን የሚይዝ ነው፡፡ ሌላው በምእራፍ ሁለት የሚገኝ ከጥናቴ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተቃኙበት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ የጌዴኦን ብሄር ያስተዋወኩበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል የአካባቢው መገኛ፣ ህዝብ ብዛት፣ እምነት፣ ቋንቋ፣ መተዳደሪያ ተካተዋል፡፡ የጥናቴ ዋና ክፍል የሆነው አራተኛው ክፍል የመረጃ ትንተና ነው፡፡ ይህ ክፍል ከመስክ የሰበሰብኩትን መረጃ ከተለያዩ ንድፈሀሳቦች ጋር በማቀናጀት የተነተንኩበት ሲሆን የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል ማጠቃለያ ነው፡፡ በማጠቃለያዬም በጥናቴ ላይ የተገኙትን ውጤቶች በማሳየት ለቀጣይ ምን መሆን አለበት የሚለውን ጥቆማ እሰጣለሁ፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ግጭት የማኅበራዊ ተቋማት መስተጋብር ውጤት ነው፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ መገለጫ ገጽታዎች ኅብር፣ መረጋጋትና ስምምነት ብቻ ሳይሆኑ ጥላቻ፣ ግጭትና ግንኙነት ጭምር ናቸው፡፡ ማንኛውንም ማኅበራዊ መስተጋብርና ማኅበረሰብ ከስርዓቱ አሉታዊ ገጽታዎች ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡ ማኅበረሰባዊ ለውጥም ሒደት ሲሆን ግጭት በቡድኖች መካከል የሚከሰት ት ግል ነው (Bush & Folger, 1996; Lederach & Maiese, 2003)[2] ፡፡

---

[1] ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ የሚባለውን ጽንሰ ሀሳብ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/ 1987 አንጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 5 ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ፣ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛምዶ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ የስነልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡ በሚል ይገልጸዋል፡፡(የኢትዮጵያ ህገመንግስት፣ 1997፣ 27) ሆኖም ይህ ጥቅል የሆነ ብያኔ የማጠናውን ማህበረሰብ (ጌዴኦን) በተናጠል ምን ተብሎ እንደሚጠራ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ብሄር፣ ብሄረሰብና ህዝብ ከሚሉት ቃላት መካከል በማህበረሰቡ ዘንድና በመንግስት አካላት በሰፊት ጥቅም ላይ የሚውለውን ብሄር የሚለውን ቃል እየተጠቀምኩ እዘልቃለሁ፡፡

[2] በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ የቀረቡ የውጭ ሀገር ጸሀፍት በንበት ከሚፈጠረው ስህተት ለመዳን ስማቸው በእንግሊዝኛ ፊደሎች ሰፍሯል፡፡ ከስራዎቻቸው ላይ የሚወሰዱ ዓም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እስካልተባለ ድረስ በአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው፡፡

ግጭት እንደ ንድፈሃሳብ የተጠነሰሰው በ19ኛው መቶ ዓመት በተለይም ከካርል ማርክስ የመደብ ትግልና ፖለቲካ-ኢኮኖሚ አወቃቀር ንድፈሃሳብ ነው፡፡ ከማርክስ የመደብ ትግል ትንተና ቀጥሎም ቀልብን መግዛት የቻለው የግጭት ንድፈሀሳብ የተነሳው በጆርጅ ሲሜል የቡድን ግጭት ትንተና ነው፡፡ ሲሜል እንደማርክስ ግጭትን ጨቋኝ ሳይሆን ጠቃሚ ጉዳይ ያደርገዋል፡፡ በሶስተኛ ደረጃነት የማክስ ዌበር የግጭት ንድፈ ሀሳብ ይመጣል፡፡ ማክስ ዌበር እንደካርል ማርክስ የማኅበረሰብ መስተጋብር በግጭት የሚገለጽ ነው የሚል አተያይ የነበረው ይሁን እንጅ የራሱ የሆኑ የግጭት ንድፈሀሳብም ቀምሮ አሳይቷል፡፡ (Sandole & Staroste, 1987, 96)፡፡

የግጭት አፈታት ጥናት በኢትዮጵያ ደረጃ በሰላምና መረጋጋት፣ በስነሰብ፣ በኢትዮጵያ ጥናት እንዲሁም በፎክሎር የትምህርት መስኮች ሰፊጥናት የተደረገበት ነው፡፡ ከነዚህ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩት ከሃያ በላይ ጥናቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ጥናቶች አብዛኞቹ የሆነ አካባቢን፣ ብሄረሰብን ወይም ማህበረሰብን የግጭት አፈታት በአጠቃላይ የሚያዩ፣ የግድያን ግጭት በተናጠል የቃኙ፣ እንዲሁም በሁለት ማህበረሰቦች ግጭት አፈታቶች መካከል ንጽጽራዊ ጥናት ያካሄዱ ናቸው፡፡ በኔ ጥናት ውስጥም በጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ውስጥ ያሉትን ፎክሎሮች በመመርመር ማህበረሰቡ ስለግጭት ያለውን ግንዛቤ መመርመር እና በዚህ ውጥም የሚተላለፈውን እውቀት መፈተሽ ነው፡፡

የጌዴኦ ብሄር አባላትን የግጭት ጽንሰ ሀሳብ ስንመለከት እንደሳይንሳዊው የግጭት ጽንሰሀሳብ በጎ ጎን እንዳለው ተደርጎ አይታሰብም፡፡ በአንጻሩ የማይቀርና በክፉ መንፈስ ጠሪነት የሚከሰት ማህበራዊ ጉዳይ መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ግጭቶች ይፈቱበታል ተብለው የተቀመሩት ግልግል፣ ስምምነት፣ሽምግልናና እርቅን በመጠቀም በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ይፈታሉ፡፡ መነሻቸውም ክፉመንፈስ በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ላይ የሚያመጣው ተጽኖ መሆኑ ስለሚታመን ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችና እምነታዊ የሆኑ ስርአተ ክዋኔዎች[3] ለመፍቻነት ይጠቀማሉ፡፡ ይህም ግጭቶች በዘላቂነትና በአስተማማኝነት እንዲፈቱና አሉታዊ ተጽኗቸው እንዳይጎላ የሚያደርገው ነው፡፡

[3] ስርአተ ክዋኔ የሚለው ቃል የእንግሊዘኛውን 'ritual' እንዲተካልኝ የመረጥኩት ነው፡፡ ይህ ቃል በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ በተለያየ መንገድ ሲቀርብ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ያህልም ስርአት፣ ስነስርአት.፣ ክበራ፣ ክብረበአል የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስነስርአት ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ከተነሳሳሁባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የመጀመሪያ ዲግሪዬን የተማርኩበት አካባቢ መሆኑና ብሄሩን በተወሰነ ደረጃ ማወቄ ነው፡፡ በተጨማሪም በጌዴኦ ብሄር ግጭት ሲፈጠር በቋሚነት በባህላዊ መንገድ ይፈታል፡፡ ነገር ግን በቤተመጽሀፍት ዳሰሳየ በጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ዙሪያ የተሰራ ጥናት አላገኘሁም፡፡

በመሆኑም በጌዴኦ ብሄር በባህላዊ መንገድ የሚያካሂደው የእርቅ፣ ድርድርና የሽምግልና ስርአት በማህበረሰቡ ውስጥ መከሰቱ የግድ የሆነውን ግጭት በማብረድ፤ ተበዳይ ነኝ ያለን ሰው ስነልቦና ከጥላቻ ወደ ተረጋጋ አኗኗር የማምጣትና በብሄረሰቡ የተከለከሉና በወንጀልነት የተፈረጁ ማህበረ ባህላዊ ነውሮችን የፈጸሙ ሰዎችን በመቅጣት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ውስጥም የብሄረሰቡን እውቀት መፈተሽ ተገቢ መሆኑን ማመኔ ግጭት አፈታቱን እንዳጠና አነሳስቶኛል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ሥርአተ ክዋኔን መመርመር ነው፡፡ ዝርዝር አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ለጌዴኦ ብሄር የግጭት መፍቻ ሥርዓት ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችን ማሳየት
2. የጌዴኦ ብሄር ግጭት የሚፈታባቸውን መዋቅሮችን መፈተሽ
3. የጌዴኦ ብሄር ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸውን ሂደቶች ማጤን
4. ግጭቶች በሚፈጠሩበትና በሚፈቱበት ጊዜ ያሉ ፎክሎሮችን መለየት መተርጎምና መተንተን ነው፡፡

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የጌዴኦ ብሄር ግጭት በእንዴት ያለ አውድ ውስጥ ይፈታል? በሚለው አቢይ ጥያቄ ስር የሚከተሉትን ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡ እነሱም፡-

1. በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ብዙ ጊዜ ከሚፈጠሩት ግጭቶች ውስጥ የትኞቹ በብሄሩ የፍትህ ተቋም መፍትሄ ያገኛሉ?

2. የጌዴኦ ብሄር ግጭቶች የሚፈቱት በየትኞቹ የማህበረሰብ ክፍሎች ነው? ግጭቶችን የማይፈቱ ማህበረሰቦችስ? ይህስ ያለው ትውፊታዊነት እስከምን ይደርሳል ?
3. በጌዴኦ ብሄር ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ፍጻሜ እስኪያገኝ በእንዴትና በምን አይነት ሥርአተ ክዋኔ ውስጥ ያልፋል?
4. የግጭት አፈታት ስነስርአቱ አውድ ውስጥ ምን አይነት ጽንሰ ሃሳቦችና ትዕምርቶች ይገኛሉ? ትዕምርቶችና ጽንሰ ሃሳቦችስ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን አይነት ትርጓሜ ያገኛሉ?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የጌዴኦ ብሄር ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአትን በማጥናት የብሄሩን ስነልቦናዊ አቋም ማሳየት የጥናቱ ቀዳሚ ትኩረት ነው፡፡ በግጭት አፈታት ስነስርአት ወቅት ያለውን አጠቃላይ ሂደት ከመዘገብ ባለፈ ትንታኔና ፍች ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ቀደም በግጭት አፈታት ዙሪያ ከተሰሩ ጥናቶች ላይ አዲስ ግብአት በመሆንም ያገለግላል፡፡ ይህ ለትምህርት መስኩ የሚሰጠው ፋይዳ ሲሆን ለፖሊሲ አውጭዎችና ለተጠኝ አካባቢው ማህበረሰብና የመንግስት አስተዳደር የሚሰጠው ጥቅም

- የተለያዩ ህጎችንና ፖሊሲዎችን ለማውጣት የማህበረሰቡን ትውፊት ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የጌዴኦን ብሄር የግጭት አፈታት ትውፊት ያሳያል፡፡
- በጌዴኦ ብሄር ውስጥና ከሌሎች ብሄሮች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት እንዲሁም የግጭት መንስኤዎችን በማወቅ አስቀድሞ መከላከል እንዲቻል ሀሳብ በመስጠት ረገድ ይጠቅማል፡፡
- ከኔ ቀጥሎ በጌዴኦ ብሄር ፎክሎርና ሌሎች ዲሲፕሊኖች ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝዎች የጥናት ፍንጭ ሊጠቁም ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጌዴኦ ብሄር ግጭት አፈታት ስነስርአት ላይ የሚካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም የግጭት አፈታት ስነስርአቱን ብቻ ያያል፡፡ በተጨማሪም የጌዴኦ ብሄር የሚገኝበት የጌዴኦ ዞን በባህላዊ መንገድ በሶስት ሮጋዎች የተከፈለ ነው፡፡ ከሶስቱም ሮጋዎች ውስጥ በርከት ያሉ "ሶንጎዎች" ይገኛሉ፡፡ በሁሉም ሶንጎዎች ውስጥ ግጭቶች በተመሳሳይ መንገድ እንደሚፈቱ ከልዩልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በማረጋገጤ በምቾት የናሙና አመራረጥ ዘዴ የገደብ አጠቃላይ ሶንጎን መርጫለሁ፡፡ ይህ ሶንጎ በርከት ያሉ ባለጉዳዮች የሚሳተፉበትና

የሸንጎው አስተዳዳሪዎችም ነገርን የማብራራትና ተናግሮ የማሳመን ብቃታቸው የተሻለ እንደሆኑ ከሆኑ የባህል ጥናት ባለሙያዎች ጠይቄ የመረጥኩት ነው፡፡

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ይህ ጥናት በጌዴኦ ብሄር አጠቃላይ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስነስርአት ላይ የተካሄደ ቢሆንም በጥናቴ ወቅት አንዳንድ እንቅፋቶች አጋጥመውኛል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የጌዴኦኛን ቋንቋ ያለመቻሌ፣ ምልከታ ባካሄድኩባቸው ጊዚያት አንዳንድ የግጭት አይነቶች ለሸንጎው ያለመቅረብ ችግሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ቋንቋ ያለመቻሌን በቋንቋው አፊ-ፊት በሆኑ የመስክ ረዳቶች መታገዝና በድምጽ መቅረጫና በቪዲዮ ካሜራ የተሰበሰቡትን መረጃዎችም አማርኛና ጌዴኦኛ ቋንቋ በሚችሉ አስተርጓሚዎች ማስተርጎም የተወሰደ መፍትሄ ነው፡፡ ለሸንጎው ያልቀረቡትን ግጭቶች ለማቃለልም ቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በተገቢው መንገድ ተጠቅሚያለሁ፡፡

የግድያና የብሄርና የጎሳ ግጭቶች ጥናቴን ባካሄድኩበት ወቅት ያልተከሰቱ በመሆናቸው በተፈጥሯዊ መቼት ለመመልከት አልተቻለም፡፡ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ወይም በአርቴፊሻል መቼት ለመስራት ባህሉ አልፈቀደም፡፡ ማለትም ትልልቅ ግጭቶች ባልተፈጠሩበት ሁኔታ ውስጥ መከዎን ክፉ ነገር ይጠራል፤ እርዱን የሚፈጽመው ሰው ላይም ችግር ሊያደርስ ይችላል የሚል እምነት መኖሩ ነው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡ ይህም ምልከታ ለግድያ፣ ለጎሳና ለብሄር ግጭቶች እንዳያገለግል አድረጎታል፡፡ ይህን የጥናቴን ጉድለት ለመሙላት ከዚህ በፊት የግድያ ግጭትን በመፍታት ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበራቸውን ሃዩዎችና ወዩዎች ቃለመጠይቅ በማድረግ ግጭት የሚፈቱበትን መንገድ ከነትርጓሜው ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 1.8. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የሚካሄደው ከመስክ በተገኘ መረጃ በመሆኑ ስነዘዴውም ሆነ ንድፈሃሳቡ ከመረጃው የሚነሳ ነው፡፡ ይህም ማለት ኢንዳክቲቭ የሆነ አተያይ ይሆናል፡፡ ይህ አተያይ በስሩ በርከት ያሉ ስነዘዴዎች አሉት ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ኢትኖግራፊያዊ ስነ ዘዴ አንዱ ነው፡፡ አሁን ያለው የኢትኖግራፊያዊ ጥናት ባህሪ ስናይ ሰፊ የሆነ የመስክ ተሳትፎንና የተለያየ የጥናት ስልትን የሚጠይቅ፣ ሁሉንም አይነት ዘዴዎች እንዳስፈላጊነቱ ሊጠቀም

የሚችልና የመስክ ተሞክሮዎችን በማሳየትና መተንተን ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው (Flick, 2006, 229)።

ኢ.ትኖግራፊያዊ ስነዘዴ ከሌሎች አይነታዊ ስነዘዴዎች የሚለየው ለባህል ባለው ልዩ ትኩረት ነው። በዚህ ስነዘዴ ትርጓሜ የሚገኘው ከባህላዊ ድርጊቶች ነው። ስለዚህ መረጃዎችን በምልከታና ምልልሶችን በመቅዳት፣ ፣ በክዋኔዎች፣ ስነስርአቶች፣ በእደጥበብ ውጤቶች፣ ቀልዶችና ታሪኮች ነው። ኢ.ትኖግራፊያዊ አተያይ "የተለየ አተያይ" ማለት ነው። ስለዚህ ኢ.ትኖግራፊሮች ባህላዊ ሁኔታዎችን በተለመደው አይነት መንገድ ሳይሆን ከፍተኛ ጠቀሜታዎች እንዳላቸውና ትእምርታዊ ትርጓሜዎች እንዳላቸው ጉዳዮች ማሰብ ይኖርባቸዋል። ይህ የባህል ትእምርታዊና ፋይዳዊ ባህሪ ደግሞ ባህልን የመፍጠር፣ የማንጸባረቅና ጠብቆ የማቆየት አላማ ያላቸው ጉዳዮችን የተሸከመ መሆኑን መረዳት ይገባል (Randorstoep and Jhonston, 2009, 202)።

ይህ የስነ ዘዴ አካሄድ በዚህ ጥናት ላይ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች የምተነትንባቸውን የፎክሎር ንድፈ ሃሳቦችና አተያዮች ማለትም አውዳዊ አቀራረብና ስርአተ ክዋኔን ስለሚጠራልኝም የመረጥኩት ነው። የባህልን ጥናት መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን ምቹ ስለመሆኑም (Randorstoep and Jhonston, 2009, 202) (Gray, 2004, 22) (Sims and Stephens, 2005, 193,) ይገልጻሉ። በተጨማሪም "ኢ.ትኖግራፊያዊ ተመራማሪ ባህላዊ ድርጊቶች ያለፈና የአሁን ባህልን እንደሚያንጸባርቁና ለባህል እድገትና ለውጥ መፈጠር አቅጣጫን የሚጠቁሙ እንደሆኑ አድርጎ ያያል" (Randorstoep and Jhonston, 2009, 202)።

### 1.8.1. የመረጃ ምንጮች

የፎክሎር ጥናት ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮች ሊጠቀም ይችላል። እነሱም ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጭ ናቸው። ቀዳማይ የመረጃ ምንጩ ከመስክ የሚገኘው መረጃ ሲሆን ካልአይ የመረጃ ምንጩ ደግሞ የተጠቀምኩበትን ስነዘዴ፣ ንድፈ ሃሳብና ግጭትን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚገኙባቸው ዶክመንቶች፣ ድረ-ገጽ ላይ የሚገኙ መረጃዎች እንዲሁም በኢ.ትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎርም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ትምህርት ክፍሎች ለዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች ወዘተ. ናቸው። ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የሚገኘውን መረጃ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ሰብስቢያለሁ።

እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በማቀናጀት መረጃን መሰብሰብ የተለያየ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከነዚህ መካከል እያንዳንዱ ዘዴ ያለበትን ድክመት ለማቻቻል፣ የተለያዩ መረጃዎችን እውነተኝነት ለማረጋገጥ እንዲሁም እነዚህ ዘዴዎች የሚካሄዱት ከተለያየ ሰው በተለያየ ጊዜና ቦታ በመሆኑ የተጣራ መረጃን ለማግኘት ወሳኝ እንደሆነ (Gray, 2004, 33, 257, 326, 344) ይገልጻል፡፡ በዚህ ጥናትም ከመስክ ላይ መረጃ የተሰበሰበባቸው ዘዴዎች በቅደም ተከተል ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

### 1.8.1.1. ምልከታ

ምልከታ የተሰኘው ዘዴ ከኢትኖግራፊክ ስነዘዴ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተጠኝ ማህበረሰቦችን በተፈጥሯዊ መቼታቸው ወይም በመስክ ላይ የሚያጠናም ነው፡፡ ቃሉ ብዙ ጊዜ በቀላሉ ነገሮችን ማየት ከሚለው እሳቤ ጋር ተያይዞ ይቀርባል፡፡ ነገር ግን አንድ የኢትኖግራፊ ዘዴ ዋና ስነዘዴው የሆነ ፎክሎረኛ በምልከታ ወቅት ሁሉንም የስሜት ህዋሳቱን ማለትም እይታውን፣ ደመጣውን፣ ሽታውን፣ ዳሰሳውን ባጠቃላይ ስሜቱን ለባህላዊ አውዱ ሰጥቶ መከታተል ይኖርበታል፡፡ ይህ ተግባር የሁሉም ስሜት ህዋሳቶቹ ጥምረት ሊሆን እንደሚገባው (Goldstein,1964, 77) (Gray, 2004, 238,) (Tony, 2005,10) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እኔም በተጠኘው ብሄር በተፈጥሯዊ መቼት በመገኘትና በመመልከት አካሂጃለሁ፡፡ በምልከታየ የሰበሰብኳቸው መረጃዎችም በገደብ አጠቃላይ ሶንጎ በመገኘት የተመለከትኩት የግጭት አፈታት አውድ ነው፡፡ በምልከታው ወቅትም በዲጂታል ድምጽ መቅረጫ፣ በቪዲዮ ካሜራና በፎቶ ካሜራ በመቅረጽ የመረጃ ክፍተትን ለማየት እዛው መስክ ላይ ትንታኔ አካሂጃለሁ ፡፡

አጥኚዎች በምልከታ ወቅት የሚያስታውሷቸውን ማናቸውም ነገሮች ጥያቄ ሊፈጠሩባቸው፣ ምላሽ ማግኘት ያለባቸው ነገሮችም መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ሁሉም የምልከታ ግኝቶች ለአጥኚው ግልጽ መንገድ የሚጠቁሙም መሆን አለባቸው፡፡ ነገር ግን ከምልከታ የሚገኝ መረጃ ብቻውን በቂ ላይሆን ስለሚችል በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መደገፍ ተገቢ ነው፡፡ ኢትኖግራፊያዊ ጥናት ከምልከታ በተጨማሪ ሌሎች ዘዴዎችንም ሊጠቀም ይችላል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥልቅ ቃለመጠይቅ፣ግለሰባዊ ዶክመንቶች እንዲሁም ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተጠቃሽ ናቸው (Gray, 2004, 238)፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በምልከታ የተገኘን መረጃ የማጠናከር እና በምልከታ ወቅት የሚፈጠሩ ጥያቄዎችን የመመለስ ተግባራትን ይወጣሉ፡፡

### 1.8.1.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለመጠይቅ ሰዎች በውስጣቸው የነበረን ሃሳብ እንዲያወጡ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ሲባል አመለካከታቸውን ስሜቶቻቸውንና የሚያውቁትን በራሳቸው ዘዴ እንዲገልጹ ማስቻሉ ነው (Gray, 2004, 213)፡፡ በኢትኖግራፊያዊ የመስክ ጥናት ተሳትፏዊ ምልከታ ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ቃለመጠይቅም የራሱ የሆነ ሰፊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ቃለመጠይቅ ዘዴ የመስክ ባለሙያው ስለሃሳቦች ወይም ከአውድ ውጭ ስለሆኑ ሁኔታዎች ያውቃሉ ተብለው ከሚታመንባቸው ግለሰቦች መረጃ የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ በቃለመጠይቅ ወቅት መረጃ አቀባዮቹ ስለሁኔታዎች፣ ቁሶች፣ አመለካከቶች ወይም ግለሰባዊ የሆኑ የመላሹ አቋሞች ገለጻ ያደርጋሉ (Goldstin, 1964, 77)፡፡ አንድ አጥኝ በቃለመጠይቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሲያስብ ሊያደርጋቸው የሚገቡ የተለያዩ አይነት ጥንቃቄዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ቀዳሚው የመረጃ አቀባዩን ፍላጎት እና የብቃት ደረጃ በመጠነ መልኩ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ነው፡፡

ኢትኖግራፊያዊ ቃለመጠይቅ አጥኝው በሚያመጣቸው አዳዲስ መረጃዎች አማካኝነት መላሹ ያለውን እውቀት እንዲያወጣ እየረዳ ተለጣጣቂነት ያለው መረጃ እንዲሰጠው የሚያደርግበት ተግባቦታዊ ምልልስ ነው፡፡ በአንጻሩ ሁሉንም አይነት የኢትኖግራፊ ይዘቶች መጠቀም ወይም ስለነሱ በጣም ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠት ግን ቃለ መጠይቁን ወደ መደበኛ ሙግትነት ሊለውጠውና በተጠያቂዎቹ ውስጥ ሊፈጠር የሚገባውን የወዳጅነት ስሜት ቀስ በቀስ ሊያጠፋ የሚችል ነው፡፡ እንዲያውም ተጠያቂው መልስ በመስጠት መተባበሩንም ሊያቆም ይችላል (Flick, 2005, 214)፡፡

ቃለመጠይቅ ዘዴ በኔ ጥናት ውስጥ በምልከታ ወቅት የሚፈጠሩ ጥያቄዎችን ለመመለስ፤ በተፈጥሯዊ አውዳቸው ለመመልከት ያልቻልኳቸውን የግጭት አይነቶች ሪቹዋልና አውዳዊ ሁኔታ ለማጣራት፤ በምልከታ ሂደት የተዘለሉና የተገደፉ ሁኔታዎችን መገላለጥ እና የተለያዩ አስረጅ ትእምርቶችንና ናሙና የሚሆኑ ዝርው ታሪኮችን ለማግኘት አገልግሏል፡፡

በቃለ መጠይቅ የሚሳተፉትም ግጭትን በመፍታት በኩል ሰፊ ሚና ያላቸው የገዳ ስርአት መሪዎች፣ ከግጭት መፍታት ጋር ተያያዥነት ያለው ስራ በመስራት በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦች፣ ከአካባቢው ባህልና ትውፊት ጋር የሚያያዝ ስራ የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች፣ የዞኑን የፖሊስና የፍትህ ተቋማት ሰራተኞች ወዘተ. ነው፡፡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ሶስት አይነት ናቸው እነሱም ውሱን፣ ከፊል ውሱንና ክፍት

ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም አንዱ ያለበትን ድክመት በሌላው ለመሸፈን እንዲመች ሁሉም አይነት ጥያቄዎች አዘጋጅቼ በተገቢው መንገድ ተጠቅሚባቸዋለሁ፡፡

### 1.8.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት በተመራማሪውና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ምልልስ ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ባህላዊ የሆነ መረጃን ለመሰብሰብ፣ ደጋፊ መረጃዎችን ለማግኘትና ከተለያዩ ሰዎች የሚመጡትን የተለያዩ አመለካከቶች በአንድ አይነት ርእሰ ጉዳይ ስር ለማስቀመጥ እንዲሁም ከዚህ ቀደም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ውጤት ለማጤን ያገለግላል፡፡ የቡድን ውይይት መደበኛና ኢ.መደበኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አገላለጽ በተመራማሪው የሚመራና በታቀደ መንገድ የሚካሄድ ወይም በተፈጥሯዊ መቼቱ ውስጥ በአጋጣሚ የሚከናወን ሊሆን ይችላል፡፡ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች በተገቢው መንገድ እንዲሳተፉ ማበረታታትና የአንድን ሰው የበላይነት እንዳይስተዋልበት አጥኚው ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል (Schensul, Lecmi, Nastasi, 1999, 52)፡፡

ለቡድን ውይይት የሚቀርቡ የተለያዩ አይነት ጥያቄዎችና የመወያያ ሃሳቦች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችና የመወያያ ሃሳቦች ውሱን፣ ከፊል ውሱንና ክፍት ሆነው ይዘጋጃሉ፡፡ ነገር ግን የቡድን ቃለመጠይቅ በመሆኑ እምብዛም ከሃሳቡ ርቀው እንዳይሄዱ ከፊል ውሱንነት ጠንከር ብሎ ታይቶባቸዋል፡፡ በኔ ጥናት በቡድን ውይይት በምልከታና በቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚፈጠርን ብዥታ ለማጥራትና ሌሎች መረጃዎችን ማመሳከር ሲያስፈልግ ግልጋሎት ላይ ውሏል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ በቃለመጠይቅ ካገኟኋቸው መረጃዎች በተጨማሪ ልዩ ልዩ ትእምርታዊ ጉዳዮችን ፍች ከቡድን ውይይት ለማግኘት ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም የከበባድ ግጭቶችን ስርአተ ክዋኔ ለመመልከት ስላልቻልኩ በግለሰባዊ ቃለመጠይቅ ካገኘሁት መረጃ በመነሳት የቀሩትን ጉዳዮች እያጣራሁ ለማግኘት ችያሁ፡፡ ይህ ውይይት መደበኛ በሆነ መንገድና ኢ.መደበኛ በሆነ መንገድ ተካሂዷል፡፡ መደበኛው የተካሄደው በቡሌ ከተማ ውስጥ ሲሆን አምስት የሀገር ሽማግሌዎችን ያቀፈ ውይይት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በገደብ አጠቃላይ ሽንጎ የተካሄደው ሲሆን በአምስት ሰዎች መካከል የተከናወነ ነው፡፡

### 1.8.2. የመረጃ መተንተኛና ማቅረቢያ መንገድ

ከመስክ የማገኘውን መረጃ የተነተንኩበት መንገድ በዋናነት አውደ ትንታኒያዊ አቀራረብ ነው፡፡ አውዳዊ ትንታኔ የፎክ ቡድኑን አባላት እይታ በፎክሎር ትንታኔ አቅጣጫ የሚታይበት ነው፡፡  ምክንያቱም የባህል ትርጉም የሚገኘው አውድን መሰረት ባደረገ መልኩ ትንታኔ ሲካሄድ በመሆኑ ነው (Sims and Stephens, 2005, 26)፡፡ በዚህ መልክ የሚተነተኑት መረጃዎች የሚገኙት ከጌዴኦ ብሄር አባላት በመሆኑ ጥናቱ ከማህበረሰብ እውቀት ወጥቶ የእኔ የግል አስተያየት እንዳይሆን በማህበረ ባህላዊ አውዱ ውስጥ እንዲታይ ትልቅ ጥንቃቄ በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ ጥናቱ የቀረበበት መንገድም ገለጻና ትንተና ነው፡፡ ገለጻው የስነስርአቱን ሂደት ከዋኔና አውዱን ለማቅረብ የሚጠቅም ነው፡፡ ትንተናው ባህላዊ ትርጓሜን ሳይገድፍ ሳይንሳዊ ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸውና መብራራት ላለባቸው ጉዳዮች ትንታኔ  ለመስጠት የሚጠቅም በመሆኑ ነው፡፡

## 1.9. የመስክ ተሞክሮ

### የመጀመሪያ ዙር የመስክ ተሞክሮ

ለጥናቴ የሚሆነኝን መረጃ ለማግኘት ወደ ዲላ ከተማ የሄድኩት ታህሳስ 18 2005 ነበር፡፡ ታህሳስ 19 አርብ በዲላ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ጬጬ ገብርኤል የሚነግስበት አመታዊ ክብረ ብዐል ነው፡፡ በዚህ የተነሳም ብዙ የመንግስት ሰራተኞችን ቢሯቸው እንደማላገኛቸው ስለተነገረኝ እኔም ገብርኤልን ለማንገስ በእግረ መንገዴም አንዳንድ ትውፊታዊ ጉዳዮችን ለምሳሌ የሰላምታ አሰጣጥ፣ የሰዎችን ግንኙነት የመሳሰሉትን ለመመልከት ወደቤተክርስቲያን ተጓዝኩ፡፡ ከዚህ ቀን በኋላ ያሉትን ተከታታይ ሶስት ቀናት የጌዴኦ ብሄረሰብ አባላት የሆኑ ሰዎችን በስልክም ሆነ በአካል በመገናኘት አንዳንድ መረጃዎችን ኢ.መደበኛ በሆነ መንገድ ስሰበስብ ሰነበትኩ፡፡

ታህሳስ 23 ቀን ሁለት ሰአት ተኩል ላይ በዞኑ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመገኘት ለምን እንደሄድሁና ምን ማግኘት እንደምፈልግ አስረዳሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ይሄን ጉዳይ የሚመለከቱት የዘርፉ ባለሙያ ማለትም የባህል ምርምር የስራ ሂደት ሃላፊ የሆኑት ስላልነበሩ ከሰአት በኋላ ቀጠሮ ይዤ ተመለስኩ፡፡ በቀጠሮየ ሰአትም የተባሉትን ሀላፊ አግኝቻቸው ስለ ዞኑ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችንና የምገዛባቸውን ሱቆች ጠቁመውኝና በቢሮው በኩል ማግኘት ያለብኝን ድጋፍ ሁሉ ማግኘት እንደምችል የፋይናንስ ድጋፍን ግን በፍጹም እንዳላስብ አስጠነቀቁኝ፡፡ እንዲሁም ሊረዳኝ ይችላል ያሉትን አንድ የህዝብ

ግንኙነት ባለሙያ ለመስክ ረዳትነት አስተዋወቁኝ፡፡ ይህ ሰው የጌዴኦኛ ቋንቋ አፊፊትና አማርኛም በደንብ የሚችል ስለሆነ የመስክ ረዳቴ እንዲሆን ተስማምተን ለየካቲት 26/2005 ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡

ቀጣዩ ስራየ መረጃ ሊያቀብሉኝ የሚችሉ የሃገር ሽማግሌዎችና የገዳ ስርአት ባህላዊ ባለስልጣናት ከመስክ ረዳቴ ጋር ማፈላለግ ነበር ፡፡ በመጨረሻም የካቲት 26 ቀን የደጋው ጌዴኦ ክልል አስተዳዳሪ ወይም ጃቅለባው ወደሚገኙበት ቡሌ ከተማ ከመስክ ረዳቴ ጋር ጉዞየን አደረኩ፡፡ ከሁለት ስአት ጉዞ በኋላ ቡሌ ደርሰን በቡሌ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኛ(አቶ ያሬድ) አመላካችነት ወደ ጃቅለባው ቤት ብንሄድም ሰውየው መንገድ መሄዳቸውንና በሌላ ጊዜ ቀጠሮ ይዘን ብንሄድ ልናገኛቸው እንደምንችል ስለተነገረን ወደ ዲላ ከተማ ወዲያውን ተመለስን፡፡

ዲላ ከተማ እንደደረስንም ሁለት የሃይቻ ማእረግ የነበራቸውና አሁን ግን ሉቦ (ሁሉንም የማእረግ እድገት ደረጃዎች የጨረሱና አሁን መልሰው ወደ ልጅነት የተመለሱ ማለት ነው) የሆኑ የአገር ሽማግሌ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ወደ ምችሌ ማዞሪያ ከመስክ ረዳቴ ጋር ሄድኩኝ፡፡ ሽማግሌዎቹ በአማርኛ መግባባት የሚችሉ በመሆናቸው ለሶስት ስአት ያክል ቃለ ምልልስ በማድረግ የመጀመሪያውን መረጃየን ላገኝ ችያለሁ፡፡

በጌዴኦ ገዳ ስርአት ባህላዊ የስልጣን ተዋረድ መሰረት የጦር አዝማችነት ማእረግ፣ የጌዴኦ አባ ገዳ ወይም ጋዲቾ አስመራጭ ማእረግ ባለቤትና የጌዴኦ ብሄር ታሪክ ጸሃፊዎች መካከል አንዱ የሆኑ እንዲሁም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ለረዥም አመታት በጌዴኦ ዞን ባህልና ስፖርት ቢሮ በሃላፊነት የሰሩትን አቶ ጥላሁን እብዶን 04/27/2005 ከቀኑ በ9፡00 የመስክ ረዳቴ አገናኘኝ፡፡ ከአቶ ጥላሁን እብዶ ጋር የጥናቴን ትኩረትና ምን አይነት መረጃዎችን ማግኘት እንደምፈልግ ተነጋግረን ለማክሰኞ ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን፡፡ ከዚህ ቀን ቀጥሎ ሁለት ቀናት የገና ዋዜማና የገና ብአል የሚከበርባቸው በመሆናቸው እስካሁን ያገኘኋቸውን መረጃዎች በጽሁፍ እያሰፈርኩና ክፍተቶችን እያየሁ የመፍትሄ አቅጣጫ እየፈለኩ የቆየሁባቸው ናቸው፡፡

በ30/2005 ዲላ ባህልና ቱሪዝም ከሄድኩበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ቀናት የመስክ ረዳቴ ሆኖ ይሰራ የነበረው ሰው ጋር ያለኝን የስራ ላይ ግንኙነት ያቆምኩበት ነው፡፡ ምክንያቱም በስልክ ላወራንባቸው፣ ምንም ሰው ላላገናኘኝ ቀጠሮዎች ሁሉ እንዲሁም

ከሰላሳ ደቂቃ በላይ ላልቆየንባቸው ጊዚያት ሁሉ የውሎ አበል ማለትም በቀን 147 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ብር) እንድከፍለው በመጠየቁ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ያህል ገንዘብ የምከፍልበት አቅምም ሆነ ምክንያት ስላልነበረ እስካሁን አብረን የቆንባቸውን ስድስት ቀናት የውሎ አበል በመክፈል በሰላማዊ መንገድ አሰናብቸዋለሁ፡፡ ከሰውየው ጋር የነበረኝን ጊዜ እንዳጠናቀቅኩ በቀጥታ ወደ አቶ ጥላሁን እብዶ መኖሪያ ነው ያቀናሁት፡፡ ከእሳቸው ጋርም ከዚህ በፊት የጻፏቸውን የተለያዩ ጽሁፎች እያሳዩኝ ቆዩ፡፡ ለእሳቸው ያለኝን አድናቆት ከገለጽኩ በኋላ ከፊል ውስን የሆኑትን የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ለሁለት ሰአት ተኩል ያህል ጠየኳቸው፡፡ በመጨረሻ አመስግኛቸው ከቤታቸው ወጥቻለሁ፡፡

ሀሙስ የአብዛኞቹ ሶንጎዎች የስራ ቀን በመሆኑ ወደ ገደብ ወረዳ ዋና ሶንጎ እንድሄድ ለገደብ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ትብብር እንዲደረግልኝ ደብዳቤ በመጻፍ በእርግጠኝነትም ተገቢ መረጃ እንደማገኝ አስረዱኝ፡፡ ነገር ግን የተወሰነ ብዥታ ስለነበረብኝ ለአቶ ጥላሁን እብዶ በስልክ ያለውን ነገር ገለጽኩላቸው፡፡ እሳቸውም ጥሩ አማራጭ እንደሆነና ጥሩ የመናገር ብቃት ካላቸው ሃቻዎች መካከል ዋናው እዛ እንደሚገኙ ስላስረዱኝ ለመሄድ ወስኜ ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑኝን የፎክሎር ቁሶች አዘጋጅቼ አደርኩ፡፡

በ02/05/2005 ከንጋቱ አስራ አንድ ሰአት ተኩል ከዲላ ከተማ በመነሳት ሁለት ሰአት ከአርባ አምስት ደቂቃ ላይ ገደብ ከተማ ገባሁ፡፡ ካም ሞተር ብስክሌት ኮንትራት በመያዝ ወደ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሄድኩ፡፡ በቢሮውም የመጣሁበትን ጉዳይ ለሰራተኞቹ በማስረዳትና ከዞንና ከትምህርት ክፍሉ የተሰጠኝን ደብዳቤ በማሳየት ወደ ሶንጎው እንዲወስዱኝ ጠየቅሁ፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞችም ሶስት ሆነው አብረውኝ ወደ ሶንጎ ቦታ ሄድን፡፡

በሶንጎው ቦታም የሀገር ሽማግሌዎችና ቀድመውን የሄዱ ባለጉዳዮችን አገኘን፡፡ በዚህ ጊዜም ወደ ሃይቻው በመሄድ ጉዳየን አስረዳሁ፡፡ እሳቸው ግን ከአቶ ጥላሁን ዘንድ መልዕክት እንደመጣላቸውና እኔም የምፈልገውን ነገር ሁሉ በተገቢው መንገድ እንደማገኝ እንዲሁም ሁሉንም መቅረጽ እንደምችል አስረዱኝ፡፡ በዚህ በመደሰትም ሊረዱኝ ከመጡት ባለሙያዎች ውስጥ አንደኛው በዲጅታል ካሜራዬ እንዲቀርጽልኝ አድርጌ ሁሉንም ጉዳዮች በጽሞና መከታተል ጀመርኩ፡፡

ጉባኤው የተጀመረው በሶስት ስአት ሲሆን በዛ ያሉ ጉዳዩችን መፍትሄ ሲሰጥና ሌሎችን ደግሞ ለቀጣዩ ሃሙስ ሲቀጥር ውሎ ከቀኑ ሰባት ስአት ተኩል ሲሆን ተገባደደ፡፡ ልክ ሽምግልናው እንዳለቀ ሽማግሌዎቹ ከነሱ ምን እንደምፈልግ ጠየቁኝ፡፡ ቃለ መጠይቅ ላደርግ እንደምፈልግ ሳስረዳቸው ከምሳ በኋላ ብንገናኝና ብንነጋገር ተባብለን ከሸንጎው ወጣን፡፡ ስንወጣም እኔ እንግዳ ስለሆንኩ አብረን ምሳ እንደምንበላና እዛው ጥያቄየን አዘጋጅቼ እንዳቀርብ ተስማማን፡፡ በዚሁ መሰረት ከተማው ውስጥ የተሻለ ወደሆነው አነስተኛ ሆቴል በመሄድ በጋራ ምሳ በላን፡፡ እንደጨረስንም ቃለመጠይቅ እያደረግኩ እስከ ዘጠኝ ስአት ቆየን፡፡

በመጨረሻም ለነበረን ጊዜና ለምሳ ግብዣቸው አመስግኜ ሁለት መቶ ብር ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩኝ፡፡ ገንዘብ መክፈል እንደማይገባና በጌዴኦ ባህል እንግዳ ጉዳዩን እስኪጨርስ በሚገባ ተስተናግዶ እግዚያብሄር ይስጥልኝ ብሎ ብቻ እንደሚሄድ አስረዱኝ፡፡ እኔ ግን ምንም ማለት እንዳልሆነና ዝም ብየ ባፌ ብቻ ላለማመስገን ያደረኩት እንደሆነ አግባብቻቸው ልዎጣ ስል ሽማግሌዎቹ ባህላቸውን ላጠና ስለፈለኩና ላሳየኋቸው ክብር ሽልማት እንደሚገባኝ ገለጹልኝ፡፡

ከመካከላቸው አንዱ አባት "ቅድም የጌዴኦ አባት ሽልማቱ ምርቃን ቅጣቱ ደግሞ እርግማን እንደሆነ አልነገርኩሽም? ሁለቱም ደግሞ ምድር ላይ ጠብ የማይሉ ናቸው፡፡" ሲሉኝ በምልከታየ ወቅት ምርቃት ሲቀበሉ እንዳየኋቸው ሰዎች አቀማመጥ አይነት ተንበርክኬ ከሽማግሌዎቹ ፊት ሆንኩ፡፡

ምርቃቴን ተቀብየ ይደርስ አይደርስ ይሆን የሚለው ሃሳብ ውስጤ መመላሱን የጠረጠሩት አባት "ልጄ የጌዴኦ ምርቃትም ሆነ ርግማን ምድር ላይ ጠብ አይልም፡፡"ካሉኝ በኋላ ከራሳቸው ልምድ ጀምረው ወደ ሌሎቹ የአካባቢ ሰዎች ልምድ በመሄድ የተለያዩ ገጠመኞችን ትረካ አደረጉልኝ፡፡ እዚህ ላይ በውስጤ በጌዴኦ ብሄረሰብ የምርቃትና የእርግማን ታሪኮችና የርግማንና የምርቃት ሁኔታ ሰፊ ጥናት ማድረግ እንደሚቻል እያሰብኩ ተሰናብቻቸው ወጥቻለሁ፡፡

03/05/2005 ጀምሮ ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት በጌዴኦ ዞን ፋይናንስ፣ ግብርና ጽህፈት ቤትና የዞኑ ማስታዎቂያና ባህል መስሪያ ቤቶች ለጥናቱ ዳራ የሚሆነኝን መረጃ ማለትም ስለ ዞኑ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት በተደጋጋሚ ሄድኩኝ፡፡ በረዥሙም ምልልስ ይሁን እንጅ የምፈልገውን መረጃም ከሞላ ጎደል ላገኝ ችያለሁ፡፡ በሌላ በኩል ከዞኑ ፖሊስ መምሪያ

ቢሮም ተለያዩ ግጭት ነክ መረጃዎችንና የሀገረሰባዊ የፍትህ ተቋሙ ምን የህል እውቅና እንደተሰጠውና ምን ያህልስ ጠንካራ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ለማጣራትም ሞክሪያለሁ፡፡ በዚህ ጊዜም ከፖሊስ አካላቱ ዘንድም የተለያዩ ትረካዎችን ስለሰማሁ እነዚህን በስፋት ለማግኘት ደግሞ አብዛኞቹ በስራ የተወጠሩ በመሆናቸው በቀጠሮ ስአት ያለመገኘትና የጀመሩትን ሳይጨርሱ ለስራ መሄድ ስላጋጠመኝ የጽሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀት መረጃየን ለማጠናከር ሞክሪያለሁ፡፡

## ሁለተኛ ዙር የመስክ ቆይታ

ሁለተኛው ዙር የመስክ ቆይታየ ከሚያዚያ 16/2005 እስከ ግንቦት 25/2005 ነበር፡፡ ሚያዚያ 16/2005 ከአዲስ አበባ ተነስቼ ዲላ ከተማ የገባሁ ሲሆን በትንታኔየ ውስጥ ያገኘኋቸውን ክፍተቶች ለማሟላት የተለያዩ ቃላዊ ትረካዎችን ለመሰብሰብና የተለያዩ የግለሰባዊ ልምድ ትረካዎችን ለማግኘት ሞክሪያለሁ፡፡ በዚህ የመስክ ቆይታየ ወቅትም የእያንዳንዱን የጉዞ መስመር መዳረሻ ስላወኩትና የጌዴኦ ብሄር አባላት ያላቸው አቀባበል ጥሩነት ስላበረታታኝ ያለ መስክ ረዳት ለመንቀሳቀስ ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም የሁለተኛው መስክ ቆይታ ለመሄድ የተነሳሁበት ዋና አላማ ሁለት ሰዎች ኦዳያአ ሶንጎ ውስጥ ግንድ ተሸክመው ሲሄዱ ወድቀው አንደኛው ወዲያው መሞቱንና ይህ ሰው የመንጻት ስነስርአት ስለሚፈጸምለት ወጭውን ሸፍኘ መመልከት እንደምችል ከዋና የመረጃ አቀባየ ስለተነገረኝ ነበር፡፡ በቦታው ከደረስኩ በኋላ ግን የመንጻት ስነስርአት የሚካሄደው በሶንጎው ውስጥ ነፍስ ስለጠፋበት ሸንጎው ብቻ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የግድያ ግጭት ሲፈታ መመልከት ስላልቻልኩ የቡድን ውይይት በማካሄድ መረጃ ለመሰብሰብ በማሰብ ወደ በደጋው የጌዴኦ ክልል ልጓዝ ችያለሁ፡፡

በ20/ 08/ 2005 በቡሌ ከተማ የቡድን ውይይት ማካሄድ እንደምፈልግና እንዲሰባሰቡልኝ ከአቶ ያሬድ ጋር ተነጋግረን፡፡ በዚህ መሰረት አራት የሀገር ሽማግሌዎችን እንዳገኘ ስለነገረኝ ከረፋዱ አራት ሰአት አካባቢ ከዲላ ከተማ ተነስቼ ከሰአት በኋላ ከሀገር ሽማግሌዎቹ ጋር በመገናኘት በመጀመሪያ ዙር ከሰበሰብኩት መረጃ ውስጥ መጣራት አለባቸው ብየ ያሰብኩባቸውን ጉዳዮች ለማጣራት ሙከራ አድርጊያለሁ፡፡ በዋናነት ግን

የቡድን ውይይቱ ትኩረት እንዲያደርግ ጥረት ያደረግኩት በከባባድ ግጭቶች ውስጥ በሚካሄደው ስርአተ ክዋኔ ላይ ነው፡፡ ይህንም በተሳካ ሁኔታ አካሂጄ ከኔ ምን ያህል ገንዘብ ሊጠብቁ እንደሚችሉ ከእለቱ የመስክ ረዳቴ ጋር ተነጋግሬ ለእያንዳንዳቸው እስከ ሰማንያ ብር ሊጠብቀቁ እንደሚችሉ ስለገለጸልኝ ከአክብሮትና ምስጋና ጋር አራት መቶ ብር ሰጥቻቼዋለሁ፡፡ በነሱ በኩልም በጣም በዛ ያለ ምረቃት አግንቻለሁ፡፡

በዚህ ጊዜ ያከናወንኩት ሌላው ተግባር በመጀመሪያ ዙር የመረጃ ስብሰባየ ወቅት ያኘሁትን ስነቃል ወደአማርኛ ቋንቋ ማስተርጎም ነበር፡፡ ነገር ግን ከጌዴኦኛ ወደ አማርኛ ጥሩ አድርጎ ይተረጉማል የተባለው ተርጓሚ በርካታ የትርጉም ስህተቶችን ስለፈጸመ እንደገና ለሌላ ጌዴኦኛ አፈ-ፊትና በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው የዞን የባህል ባለሙያ ተርጓሚ ለመስጠት ተገድጃለሁ፡፡ በዚህ የትርጎማ ሂደት ወቅትም ተፈጸሙ የተባሉ ስህተቶችን ለማረም በጣም ብዙ ገንዘብ ባወጣም የጥናቴን አካሄድ የሚመራው በመሆኑ በልዩ ጥንቃቄ ለማካሄድ ሙከራ አድርጊያለሁ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ የጥናቴ ክፍል ለጥናቴ የሚሆኑኝን ከዳህራይ የመረጃ ምንጮቼ ያገኘኋቸውን ንድፈ ሀሳቦችና ተዛማጅ ጥናቶች የማሳይበት ነው፡፡ በመሆኑም በቀዳሚው የክለሳ ድርሳናት ክፍል ንድፈ ሃሳባዊ ዳራን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች አሳያለሁ፡፡

### 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ንድፈሀሳብ አንድን ጥናት በማእቀፍነት የሚይዝ ወይም ለመተንተኛና ለማቅረቢያ የሚሆን የጥናታዊ ጽሁፍ ወሳኝ አካል ነው፡፡ የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ በሚለው ጥናት ውስጥም የአውድና የሪቹዋልን ንድፈሃሳብ ምንነትንና በጥናቱ ውስጥ እንዴት እንደምጠቀምባቸው አቀርባለሁ፡፡

#### 2.1.1. አውድ

የማህበረሰብን እውቀት ትርጓሜ ለመስጠት የሚጠናውን ጉዳይ ማህበረ ባህላዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ወሳኝ ነው፡፡ እንዲሁም ቴክስትን በቁሙ ለማጥናት መሞከር

ወይም ትንታኔ መስጠት ላልተገባ ማጠቃለያ የሚዳርግ ማለትም የማህበረሰብ እውቀትን በአጥኚው የግል አስተያየት የሚለውጥም ነው፡፡ የክዋኔን ጥናት ለራሳቸው የጥናት አቅጣጫ በሚመጥን መልኩ ከወሰዱት መካከል ፎክሎርና አንትሮፖሎጅ ይጠቀሳሉ፡፡ ይሄውም ማህበረሰብ ሰራሽ የሆነውን እውነታ መፈተሽና መተንተን የሚያስችላቸው መሆኑ ቅድሚያ የሚሰጡት የጥናታቸቸው ትኩረት በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ አውድ በዘመናዊ የፎክሎር ጥናት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እየያዘ የመጣ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ጽንሰሀሳብ አንድ ማህበራዊ ቡድን ህዝባዊ ጥበቡን የሚለዋወጥበትና ግንኙነት የሚፈጥርበት ተፈጥሯዊ መቼትና ማህበራዊ ሁኔታ ነው (Sims and Stephens, 2005, 19)፡፡

ቴክስትን በአውድ ውስጥ አስገብቶ ማጥናት የሚለው አስተሳሰብ የመጣው በ1970 ዓም አካባቢ ክዋኔን እንደተለየ ቃላዊ ተግባቦት የመውሰድ ነገር በብዙ ዲሲፕሊኖች ውስጥ እየተለመደ በመምጣቱ ነው፡፡ በዚህ ዘመን የነበረው ክዋኔ ተኮር ጥናት ትኩረቱን ያደርግ የነበረው በመደበኛ (formal)፣ ስልታዊነትና ጥባባዊነት በሚታይባቸው ቃላዊ ጥበቦች (stylistic and aesthetic features of verbal art) ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አንዳች ባህል በሚወስነው አውድ ውስጥ መልዕክት እንዴት ይተላለፋል? የሚለውን የሚያሳይ ነው፡፡ (Myrvold,2007,8)፡፡ በሌላ በኩል በ1970ዎቹ ማብቂያና በ1980ዎቹ መባቻ አካባቢ የተነሳው የክዋኔ ጥናት ከቴክስቶች ትእምርታዊ ይዘትና መደበኛ የሆነ ሂደት ወደ ከዋኞችና ታዳሚያን ማህበራዊ ግንኙነት ነው ትኩረቱን ያደረገው (Bauman & Briggs,1990, 59)፡፡ የክዋኔ ጥናት ይበልጥ የተስፋፋው ደግሞ ቴክስቶች ብቻቸውን የሚሰጡት ትርጉም ማህበራዊ ተላውጦዎችን ግምት ውስጥ ያላስገባ ስለሚሆን ትርጓሜዎችን ያዛባል ከሚለው በመነሳት ነው፡፡

> When fixed texts move into performance they become oral communication and thereby adopt other communicative modes than the literal. Performance studies were also criticized for concentrating solely on contextual aspects and expanding the definition of "text" to metaphorical heights when there was a meaningful text, even a physical written text, present (Myrvold, 2007, 9).

ከጥቅሱ እንደምንረዳው አንድ ውስን ቴክስት ወደ ክዋኔ ሲሄድ አፋዊ ተግባቦት ይሆናል፡፡ ይህም ሌሎች አይነት የተግባቦት ሁኔታዎችን ወደራሱ ያመጣና ሰፊ የሆነ ይዘትና ትርጓሜን ለቴክስቶቹ ይሰጣቸዋል ማለት ነው፡፡ ይሄውም ክዋኔ ተኮር ጥናት አውዳዊ የሆነ ሁኔታ ላይ በማተኮሩ የቴክስትን ትርጓሜ ይበልጥ በማስፋት ወደዘይቤያዊ አገላለጽና የተባ ትርጉም ያመራል፡፡ ይህም የቴክስትን ትርጉም ከተጻፈውና በቁሙ ከምናውቀው በላይም የሚያደርገው ነው(Myrvold, 2007, 9)፡፡ ስለዚህ አውዳዊ ትንተና ለማንኛም ፎክሎራዊ

ጉዳይ የመተንተኛ መንገድነት ተመራጭ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ የሚያጠነክርልኝ የሚከተለው ሀሳብ ነው፡፡

> The meaning of a text is its meaning in context. The transference of any folklore text to a different literary, historical or cultural context grants it a new meaning. Because of their transient nature, folklore texts do not have single meanings, and any grants, historically conscious use connotes previous contexts as an integral part of their set of meanings. A valid interpretation is an interpretation of atext in context (Ben-Amos 1993, 211).

ከላይ በቀጥታ የወሰድኩት ጥቅስ እንደሚያሳየው ማንኛውም ፎክሎራዊ ቴክስት ትርጓሜ የሚያገኘው በአውዱ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ማንኛውንም ፎክሎራዊ የሆነን ጉዳይ ወደ ስነጽሁፋዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ አውዶች ባስገባነው ቁጥር አዳዲስ ትርጓሜን ልናገኝ እንችላለን፡፡ የፎክሎር ቴክስት በልዩልዩ ምክንያቶች የተነሳ አንድ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አያገኝም፡፡ ለዚህም ነው ተገቢነት ያለው የፎክሎር ትንተና አውዳዊ ትንተና የሚሆነው፡፡

የአውድና የክዋኔ ጥናት የበለጠ ለሰፊ ትርጓሜ ምቹ የሚሆነው ቴክስትን በተለያየ ማህበረ ባህላዊ ሁኔታ ውስጥ በማስገባት መተንተን ስለሚቻል ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ክዋኔን የምንለይባቸው መንገዶች ተብለው የተቀመጡት ማህበረ ባህላዊ ጉዳዮች ክዋኔ ሊቀርብበት ይችላል ተብሎ የሚጠበቅበት ወይም በእርግጥም የሚከወንበት ሁኔታ፣ በክዋኔ እንዲሳተፉ ማህበረሰቡ እውቅና የሰጣቸው ሰዎች(ከዋኞች) መኖር፣ ክዋኔውን የሚቀነብቡልን ሃሳባዊ የሆኑና ቅደም ተከተላዊ ሁነቶች መኖር፣ ከዋኞቹ ሲከውኑ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መኖር ናቸው (Myrvold, 2007, 9)፡፡ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ታዲያ ክዋኔያዊ ጥናት ለማካሄድና ቴክስትን ለመተንተንም አስፈላጊ የሚሆኑ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ በአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ትንታኔ በምንሰጥበት ወቅት ማካተት አለብን ብሎ Bascom የፎክሎር ማህበራዊ አውድ መገለጫዎችን ወይም ተግባራዊ የሆነ ትንታኔ ማካሄድ ካለብን የፎክሎርን ማህበራዊ አውድ ማካተት አለብን ብሎ በዝርዝር ያስቀመጣቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም አንድን ውስን የሆነ የፎክሎር ቅርጽ ስንተነትን የጊዜና የቦታን ጽንሰሀሳብ፣ የተራኪዎቹን ማንነት፣ የታዳሚዎቹን መዋቅር፣ የተራኪዎቹንና የቴክስቱን ዝምድና፣ በክዋኔ ወቅት የሚጠቀሙበት ቋንቋዊ፣ ተውኔታዊ ብቃትና የታዳሚው እንዲሁም የፎክ ቡድኑ ቀያዊ ምደባና ሰዎቹ ለምደባው ያላቸውን አመለካከትም ማሳየታችን የግድ ነው (Bascom 1953, 334)፡፡

በአጠቃላይ ስናየው የአንድ ፎክሎራዊ ቴክስት ትርጉም የአውዳዊ ትንተናው ትርጉም ብቻ ነው (Ben-Amos, 1993, 210)፡፡ የሚለው ሃሳብ የዚህ ጥናት የሃሳብ ማጠንጠኛውና ትንተናውም የተቀነበበበት ነው፡፡ በአውድ ወይም ክዋኔ ተኮር አቀራረብ የሚጠና ጥናትም የተለያዩ ሰዎች በመተንተኛ መንገድነት ከፋፍለው ያስቀመጧቸውን የስነዘዴ መስመሮች ተከትለው ወይም የራሳቸውን የትንተና ሞዴል ወስደው ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በትንተና ሞዴልነት ከቀረቡት መካከልም የBauman የመተንተኛ ክፍልፋዮችን እናገኛለን፡፡ Bauman ወደስድስት የሚጠጉ የፎክሎር መከፋፈያ መንገዶችን አስቀምጧል፡፡ እነሱም የትርጓሜ አውድ (ምን ማለት ነው?)፣ ተቋማዊ አውድ (በባህሉ ውስጥ የት ቢከወን የተሻለ ይሆናል/ ነው?)፣ የተግባቦት አውድ (ከሌሎች ፎክሎሮች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ነው?)፣ ማህበራዊ መሰረት (የትኞቹ ሰዎች ናቸው የሚተማመኑበት)፣ ግለሰባዊ አውድ (ከአንድ ሰው ህይወት ጋር ያለው ቁርኝት እንዴት ነው?)፣ ሁኔታዊ አውድ (ለማህበራዊ ሁኔታዎች ያለው ፋይዳ እንዴት ነው? (Bauman, 1983, 67) ፡፡

በሌላ በኩል Benamos ሌሎቹ ምሁራን የከፋፈሉትን የኮንቴክስት ክፍልፋዮች ሁሉ ያጠቃልላል ያለውንና ለመጀመሪያ ጊዜ Malinowski ስያሜ የሰጣቸውን ሁለት አቢይ ክፍልፋዮች አስቀምጧል፡፡ እነዚህም ባህላዊ አውድና ሁኔታዊ አውድ ናቸው፡፡ ባህላዊ አውድ የባህሉ ባለቤቶች የሚጋሩትን የስነምግባር ሁኔታ ባህላዊ እውቀትን፣ እምነታዊ ስርአቶችን ታሪካዊ ሁኔታዎችን የሚይዝ ነው፡፡ ባህላዊ አውድ በጣም ሰፊው ፍክሎርን የመረዳትና የመተንተኛ ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአንጻሩ ሁኔታዊ አውድ ጠባብ ነው፡፡ ለንግግር ፎክሎር በጣም ቀጥተኛ የሆነም ነው (Ben Amos, 1993, 216)፡፡

የእኔ ጥናት ትኩረት የሆነው አውድ ተኮር ምርምርን የማደራጃ መንገድ ደግሞ የ (Bauman,1983) ሁለት አይነት አውዶች ማለትም ባህላዊ አውድና ማህበራዊ አውድ ናቸው፡፡ እንደ (Bauman,1983) ባህላዊ አውድ የስነፍች ጉዳዮችንና ሀገር በቀል እውቀቶችን የሚይዝ ነው፡፡ ማህበራዊ አውድ ግን የሚጠናውን ማህበረሰብ አወቃቀርና በከዋኙና በታዳሚው መካከል የሚኖርን ዝምድና የሚይዝ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት አውድ ክፍሎች በየስራቸው ሊቀመጡ የሚችሉ ክፍልፋዮች አላቸው፡፡ ባህላዊ አውድ ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች አሉት፡፡ እነሱም ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ እና የተግባቦታዊ ስርአት አውድ ናቸው፡፡

**ፍቻዊ አውድ፡-** አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ሊገልጹት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም አንድ ፎክሎረኛ የሚጠናው ፎክሎራዊ ቡድን አባላት የሆኑ ሰዎች

ለአንድ ጉዳይ ሊሰጡዋቸው ከሚችሏቸው ልዩ ልዩ ፍቺዎች እና ማብራሪያዎች ውስጥ አንድ የተለየ እና አዲስ እውነት የሚገልጽ የፍች ገጽታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ በመሆኑም በፍቻዊ አውድ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ተብለው የተቀመጡት ጉዳዮች የተጠኚው አካባቢ ማህበረሰብ ስለሚጠናው ጉዳይ ያላቸው ግንዛቤ፣ እያንዳንዱን ስነቃላዊ ጉዳይ የሚረዱበት መንገድ፣ በሚጠናው ባህል ውስጥ ያሉት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ያላቸው የእርስ በእርስ ዝምድናና የሚሰጠውን ፍች የማጎልበት አቅማቸው ምን ያህል ነው? የሚሉትን ያጠቃልላል፡፡

**ተቋማዊ አውድ፡-** ተቋማዊ አውድ እርስ በእርስ ከተቆራኙ ልዩ ልዩ ነገሮች፣ ባህርያትና ማህበራዊ አላባውያን የተገነባ፣ ለአንድ ተግባር ማከናወኛነት የሚቋቋም ተግባራዊ የድርጅት ስርአት ነው፡፡ ይህ አውድ በማህበረሰቡ በራሱ የተዋቀረ በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት አለው ወይስ በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ያለው ሚናም የላላ ነው? የሚለውን መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ቅርጽስ በተለይ ከየትኛው የማህበረሰቡ ባህላዊ ሁኔታ ጋር ይበልጥ ተዛማጅነት አለው? የሚለውንም የሚይዝ ነው፡፡ በኔ ጥናት ውስጥም ከአባ ውራ እስከ አባ ገዳ ድረስ ያሉት የማህበረሰቡ ተቋማት ያላቸውን ማህበራዊ ሚናና የጌዴኦን ብሄር ግጭት በመፍታት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ለመተንተን ውሏል፡፡ በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ያሉት ማህበራዊ ተቋማት በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማጠናከር ያላቸው ሚና፣ በተቋሙ የሚከወኑ ጸሎቶች፣ ምርቃቶችና እርግማኖች ግጭትን በመፍታት በኩል ያላቸውን ጉልህ ድርሻ የሚመረምር ነው፡፡

**የተግባቦት ስርአት አውድ፡-** በዚህ አውዳዊ ገጽታ ስር መነሳት ያለባቸው ጉዳዮች የተጠኚውን ማህበረሰብ የሚጠና ጉዳይ የገነቡት ልዩ ልዩ የፎክሎር ቅርጾች ምንምን ናቸው? ተጠኚዎቹ ማህበረሰቦች እነዚህን ቅርጾች የሚጠሩባቸው ሀገረኛ ስሞች ምንምን ናቸው? የፎክሎር ቅርጾችን የሚያዋቅሩበትና የሚለያዩበት ባህላዊ ስምምነት ያለው ስያሜ አላቸው? የሚሉትን ጉዳዮች መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአት ወቅት የሚከወኑትን የፎክሎር ቅርጾችና እርስበራሳቸው ያላቸውን ዝምድናና ጌዴኦ ብሄር አባላት ለዚሁ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት ይፈትሻል፡፡ በዚህ ውስጥም እያንዳንዱ የፎክሎር ቅርጽ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር ያለውን ትስስርና ይህ ትስስርም ግጭቶችን በመፍታት በኩል ያለውን ሚና የሚመረምር ይሆናል፡፡

ማህበራዊ አውድ

ሁለተኛው የአወድ ገጽታ ማህበራዊ አውድ ሲሆን አራት አበይት ገጽታዎች አሉት፡፡ እነሱም ማህበራዊ መሰረት፣ ነፍስ ወከፋዊ አውድ፣ ሁኔታዊ አውድ እና ተፈጥሯዊ አውድ ናቸው፡፡

**ማህበራዊ መሰረት፡-** የፎክሎር ማህበራዊ መሰረት በመካከላቸው ዝምድና ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚታይ ዋነኛው የአውድ መገለጫ ገጽታ ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ሊተነተኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ይበልጥ የሚመለከተው የማህበረሰብ ክፍል አለ ወይስ የሁሉም ማህበረሰብ ነው? አንድ ውስን ከዋኝ ብቻ ካለውስ ያንን ዘውግ በመከወኑ ሂደት ቀሪዎቹ ምን ሚና አላቸው?

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጾታ፣ በእድሜ፣ በሙያ/በሥራ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በእምነት/ በሀይማኖትና በጎሳ የተከፋፈለ ነው፡፡ ይህ ክፍለ ብዙ ብሄር የግጭት አፈታት ሂደትን ሁኔታ ወቅት ማህበራዊ መሰረቱ የተለየ ተጽኖ ይፈጥርበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ማህበራዊ መሰረት ያስከተላቸው ተጽኖዎች ይተነተናሉ፡፡

**ግለሰባዊ አውድ፡-** ፎክሎር ግለሰቦች ስሜታቸውንና ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ጥበብ ነው፡፡ በዚህ ስርም እያንዳንዱ ከዋኝ ያለውን የፎክሎር ተሳትፎና በዚያ ውስጥ ያለውን ሚና ማጥናት ተገቢነት አለው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ከዋኝ የሚከውነውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከማንና በምን አይነት የመማር ወይም የመልመድ ስልት እንደቀሰመው ማጥናት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም እያንዳንዱ ግለሰብ ከዋኝ ፎክሎራዊ ቅርጹን በመከወኑ ምክንያት የሚሰጠውን ማህበራዊ ቦታ መፈሸ ተገቢ ነው፡፡

**ሁኔታዊ አውድ፡-** ሁኔታ በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት/ተግባር የሚከናወንበት አውድ ማለት ይሆናል፡፡ በዚህ ውስጥ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓጎም የሚከናወንበት መርህ፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት ቅደም ተከተል ወዘተ ይካተታሉ፡፡

ተፈዋሯዊ አውድ፡- አንድ ፎክሎራዊ ቅርጽ በየትኛው ውስን ጊዜ፣ በስንት ሰአት፣ ማን ነው ከዋኙ፣ እንዴት ባለ ሁኔታ ውስጥ ነው የሚከወን፣ የክዋኔው አላማ ምድን ነው፣ በዚህ ውስጥ የፎክሎራዊ ጉዳዩ የቀድሞና የአሁን መልክ(ትውፊታዊነቱ) ይህን መልኩን የፈጠረውስ ምንድን ነው? የሚሉትን ሀሳቦች በጥልቀት መመርመር ነው፡፡

## 2.1.2. ስርአተ ክዋኔ

ሪቹዋል የሚለው ቃል ከላቲኑ ራይተስ (*ritus*) የተሰኘ ቃል የመጣ እንደሆነና የሚወክለውም ለአንዳች ሃይማኖታዊ ነገር ተብሎ የሚከወንን ዝግጅትና ይህን ጉዳይ እንደሚያሳይ መጽሀፍም እንደሆነ (Segal, 2006, 199) ይገልጻሉ፡፡ ስርአተ ክዋኔ የተለያዩ ጽሁፎች በተለያየ መንገድ ነገር ግን የጋራ የሆነ መሰረታዊ ነጥብ ይዘው ይበይኑታል፡፡ በአብዛኞቹ ጽሁፎች ውስጥ የሚገኙት የጋራ የሆኑ ነጥቦችም መዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ታዳሚ፣ ውጤት፣ ቅዱሳዊነት፣ ቡድናዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ቋሚነት ጎን ለጎንም ተለዋጭነት፣ ውስን መዋቅር እና የጊዜና የቦታ ጽንሰ ሃሳብ ናቸው (Salamone, 2004, 321) ፡፡

ስለስርአተ ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ከጻፉት ምሁራን መካከል አንዷ የሆነችው Bell ስርአተ ክዋኔ ቃላዊ ያልሆነ ነገር ግን ልክ እንደ ስነልሳናዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ ትእምርቶች ያሉበትና እያንዳንዱ ትእምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል ባለው የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ትገልጻለች፡፡ በተጨማሪም ሪቹዋል የአንድን ቡድን የተለመዱ ጽንሰ ሃሳባዊና ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን የሚገልጽ ጉዳይም ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከአንድ ደረጃ ወደ ተለየ ደረጃ የማሸጋገርም ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ይህ ፋይዳ ግን የሚገልጸው በሽግግሩ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ሰፊውን ስርአተ ክዋኔ ሂደትና ማህበራዊ መስተጋብሩን ጭምር በመመርመርና በመግለጽ ውስጥ መሆኑን Bell ታስረዳለች (Bell, 1997, 44)፡፡

በሌላ በኩል ስርአተ ክዋኔ የሰዎች ሃይማኖታዊ የሆኑ እምነቶችን፣ ትእምርታዊ የሆኑ መግባቢያዎችን፣ ማህበረሰባዊ የሆኑትን ንድፈሃሳቦች እና ሌሎችንም ማህበራዊ ትርጓሜዎች የሚያስተላልፍ የመግባቢያ መንገድ እንደሆነና በስነሰባውያን ብያኔ መሰረትም ስርአተ ክዋኔ አውዳዊ የሆነና ሃቲታዊ ጽንሰሃሰብ እንጂ የሰዎች ድርጊት ዋናው ጉዳይ ምንድን ነው? ወደሚለው የሚወስድ እንዳልሆነ ይታሰባል፡፡ በአንጻሩ ይህ ጉዳይ

የሰዎቹ አስተሳሰብ (እይታ) እና የሚሰጠው ትርጓሜ እንደሆነ ያትታሉ (Myrvold ፡2008፡ 21)፡፡

በስርአተ ክዋኔ ድርጊት ውስጥ ያለው ፋይዳ ማህበራዊ ወይም ግለሰባዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚያሳየው ማህበራዊ የሆነውን ስርአተ ክዋኔ ግለሰቦች የሚፈጽሙት ለራሳቸው ግለሰባዊ ፋይዳ ሊሆን መቻሉን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እኛም ሆንን ሌሎች የሚያውቁትና የሚረዱት ስርአተ ክዋኔውን እየከወንን መሆናችን ነው (Myrvold፡ 2008፡ 19)፡፡ ስለዚህ ስርአተ ክዋኔዎች ሲጠኑ የሚከወኑበትን ማህበረሰብ ማንነት እና የሚጠናውን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እንዲቻል የከዋኞቹን ማንነትና የክዋኔ ምክንያት መረዳት ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ስርአተ ክዋኔውን ከነአውዱ በጥልቀት በማጥናት የሚመጣ ነው፡፡

በግጭት አፈታት ጥናት ውስጥም የሚከወኑትን ስርአተ ክዋኔዎች ለመረዳት በግጭት አፈታት ስነስርአት አውድ ውስጥ መገኘት፤ በግጭት አፈታት ቴክስት ክዋኔ ወቅት ተሰላፊ የሚሆኑትን የሃይማኖት አባቶች፣ የጌዴኦ ባሌ ባለስልጣናትንና ተጋጭዎቹን በአካል በማግኘት ለግጭት አፈታትና ለስርአተ ክዋኔው ያላቸው ስሜት መጤን አለበት፡፡ በመሰረቱ የአንድ ስርአተ ክዋኔ መካሄድ ዋና ምክንያት በአንድ ማህበረሰብ የሚከሰተው ማህበራዊ ወይም በግለሰብ የሚከሰተው አለመረጋጋትና ቀውስን መቀነስና በማህበረሰቡ ውስጥ እርካታን መፍጠር ነው፡፡ ይህም የተፈጠረውን ችግር የመቀነስና ማህበሩን የማስተሳሰር ተግባርም ይኖረዋል፡፡ የስርአተ ክዋኔ ግቡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠርን ግጭት ወደ ማረጋጊያነት መቀየር ላይ ነው (Myrvold, 2007, 19)፡፡

## ስርአተ ክዋኔን ለማጥናት የሚያገለግሉ ሞዴሎች

ስርአተ ክዋኔን ከሃማኖትና ማህበረሰብ ጋር በማዛመድ ሂደት ውስጥ የስርአተ ክዋኔን ፋይዳና መዋቅር በሚመለከት የየራሳቸውን ጽንፍ ይዘው ሲሟገቱ እናያለን፡፡ ይህም ስርአተ ክዋኔንና ማህበረሰብን የሚመለከቱ የተለያዩ አተያዮችን እንድናገኝ አስችሎናል፡፡ ከእነዚህ አተያዮችም የፋይዳውያን፣ የድህረ ፋይዳውያንና የመዋቅራውያን አመለካከቶች ናቸው (Bell, 1997, 23-46)፡፡

ሪቹዋልን ለማጥናት እነዚህን የጥናት መስመሮች እንደግለሰብ የአጠናን ስልትና የአረዳድ መንገድ ተበትነው ቢገኙም አጥኝዎች እንዳገኙት መረጃ እና እንደ ግንዛቤያቸው ሁኔታ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ አሁን ባለንበት የበይነ ዲሲፕሊናዊ ጥናት ደረጃም የትኛውን አመለካከት ልገልገል በሚል መጨነቅ ሳይሆን ከየዘመኑ ምሁራን የእይታ አቅጣጫ ውስጥ

ተስማሚ የሆነውን በመቀንጨብ መረጃን መተንተን እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ለኔ ጥናት ከየዘመኑ ሊቃውንት የአስተሳሰብ ደረጃ ውስጥ ለጥናቴ የሚሆነኝን በመውሰድ ትንታኔየን አስኬዳለሁ፡፡ ነገር ግን ማንኛውንም አይነት የስርአተ ክዋኔ ጥናት ሲካሄድ መታሰብ ያለባቸው የጥናት አካሄዶች ተብለው በ(Bell, 1997,165) የተጠቀሱትን ጉዳዮች ልብ ማለቴ ጥናቴን የበለጠ የተቃና ያደርግልኛል፡፡

Bell ስርአተ ክዋኔን ለመተንተን የሚስችሉ ደንቦችን አስመልክታ ስትገልጽ ጥቂት የሆኑ የሪቹዋልን ስርአት ለመተንተን የሚያስችሉ ደንቦች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው ተደጋጋሚነት ያላቸውንና በተለያዩ የሪቹዋል አይነቶች ውስጥ የሚገኙትን ተመሳሳይ ትዕምርቶችንና አካላዊ ገለጻዎችን መለየት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ የሚገኙት ሪቹዋሎች ተመሳሳይ ቅርጽና ይዘት ወይም ተመሳሳይ ትርጓሜ ሊያስገኙ የሚችሉ ትእምርቶች ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ግን ግለሰባዊ ስርአቶች እምነታዊ ትእዛትን ያሳያሉ፡፡ እነሱም መሰረታዊ የሆኑ የአለም አተያዮች ማለትም አለማቀፋዊ፣ ባህላዊ፣ አካላዊና ስነህይዎታዊ ጉዳይ ይገልጻሉ ወይም ኢንኮድ ያደርጋሉ (Bell, 1997, 176)፡፡ ሌላውና ዋናው ጉዳይ ደግሞ አንድን ስርአተ ክዋኔ ለማጥናት ወሳኝ የሆነው የBell ጥቆማ አውድን ተከትሎ ማጥናት ነው፡፡

የተወሰኑት ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ደግሞ የስርአተ ክዋኔ ስርአታዊ አካሄድ ለማሳየት እና ለሚካሄደው የተዋረዳዊ ሂደት፣ ከማእከላዊነት፣ ቃላዊ ማንነትና ከሌሎች ጋራ ያለው ግንኙነት ማለትም ምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ፍልስፍናዊ አቋምና ሀይማኖታዊ ፍልስፍና ወሳኝ ናቸው፡፡ በእርግጥ የስርአተ ክዋኔ ስርአታዊ ድርጊቶች ከሌሎች ማህበረባህላዊ ሁኔታዎች ጋር በቀላሉ ላይገጥሙ ይችላል፡፡ የማያጠራጥረው ጉዳይ ግን እነኝህ ማህበረ ባህላዊ ተላውጠዎች ስርአተ ክዋኔውን ማህበረሰቡን በቀላሉ እንድንረዳው ሊያደርጉ የሚችሉ ግብአቶች ሊኖራቸው መቻሉ ነው (Bell, 1997, 177)፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተመጽሐፍቶች ባካሄድኩት ዳሰሳ የግጭት አፈታት በተለያዩ ትምህርት ክፍሎችና በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት በርከት ያሉ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በፎክሎር የትምህርት መስክ ጥናት ከተካሄደባቸው መካከል በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች፣ በአፋር፣ በትግራይ፣ በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች፣ በደቡብ ክልል የተለያዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የተካሄዱት ወዘተ.

ይገኙባቸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል በአብርሃም ታደሰ የተጠናውን ጥናት ከጌዴኦ ብሄር ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት ቃኘቻለሁ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ጥናቶች ከኔጥናት ጋር በግጭት አፈታት ዙሪያ ከመሰራታቸው ውጭ ምንም አይነት የትውፊት ተመሳስሎ የሌለ በመሆኑ ቅኝት አላካሄድኩባቸውም፡፡

ቀዳሚው ጥናት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሄረሰብ በሚል በ1999ዓ.ም በአብርሃም ታደሰ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ አቢይ አላማ በሲዳማ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከናወኑትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ ስርአቶችና ደንቦች ማጥናት በብሄረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን የተለያዩ አይነት የግጭት አይነቶች መጠቆምና እነዚህን ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱት አካላት የትኞቹ እንደሆኑና በእርቁ ወቅት የሚጫወቱትን ሚና ማጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና በጽሁፍ የተገኙ መረጃዎችን በመጠቀም መረጃ ሰብስቧል፡፡ የአብርሀም ጥናት ከመስክ ላይ መረጃዎቹን በምን ዘዴ እንደሰበሰበ እንጅ በምን አይነት ዘዴ እንደሚያደራጅና እንደሚያቀርብ ግልጽ አላደረገም፡፡

ጥናቱ በንድፈሃሳባዊ ዳራው ስለግጭት መንስኤና የአፈታት መንገዶቹ በሚል አቢይ ርእስ ስር የግጭት አፈታት ዘዴ በአለም አቀፍ ደረጃ፣ የግጭት አፈታት ዘዴ በአፍሪካ ደረጃ፣ የግጭት እሳቤ በኢትዮጵያ ደረጃና አንዳንድ የተጠኑ የኢትዮጵያ ምሳሌዎች በሚሉ ንኡሳን ርእሶች ስር አስፍሯል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጥናቶች ከሱ ጥናት ጋር ስላላቸው ዝምድና ማብራሪያ አይሰጥም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጽንሰሃሳቦች ከትንተናው የተነጠሉ እንዲሆኑ አድርጎበታል፡፡

የመረጃ ትንተናው በበርካታ ንኡሳን ርእሶች የቀረበ ሲሆን ከግድያ ግጭት አፈታት ስነስርአት ውጭ ያሉትን ትንተናዎቹን ስንመለከት አብዛኛው ትኩረታቸው በግጭቶቹ መነሻ ምክንያት ላይ ነው፡፡ ይህም ከአላማው ማለትም የግጭት አፈታትን ማሳየት ከሚለው ጋር በተወሰነ መልኩ ይጋጫል፣ ይሄውም የግጭት መነሻ ቅድመ ግጭት ሲሆን ግጭት መፍታትና መቆጣጠር ደግሞ ከግጭት በኋላ የሚመጣ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአብርሃም ታደሰ ጥናት የተካሄደበት ብሄር(ሲዳማ) የኔ ጥናት ከሚካሄድበት ብሄር(ጌዴኦ) ጋር አጎራባች በመሆናቸው የተነሳ በተለያዩ ጊዚያት ቀላልና ከባድ ግጭቶች ተከስተው መፍትሄ እንዳገኙ የኔ ጥናት ያረጋገጠ ሲሆን የአብርሃም ታደሰ ጥናት ግን የብሄር ለብሄር ግጭት በሚለው ርእሱ ስር ሲዳማ ከአጎራባቹ ኦሮሚያ ጋር ያካሄደውን ግጭት ብቻ ነው የተነተነው፡፡ ይህም ጥናቱ የመረጃ ክፍተት እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአብርሃም ታደሰንና የኔን ጥናት ተመሳስሎና ልዩነት ስናይ ተመሳስሎው የሁለታችንም ጥናት በባህላዊ የግጭት አፈታት ስነስርአት ላይ ማተኮሩና ሁለታችንም የምናጠናቸው የግጭት አፈታቶች በአጎራባች ብሄሮች(ትውፊታዊ ጉዳዮችን የሚጋሩ) መካከል የሚፈጠር መሆኑ ነው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ በተለያዩ ብሄረሰቦች የተካሄደ መሆኑና ንድፈ ሀሳቡ የግጭት አፈታትና ይሄው ጽንሰ ሃሳብ በአለም በአፍሪካና በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል የሚለው ሲሆን የኔጥናት ንድፈ ሃሳብ የፎክሎር ንድፈ ሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳቦች መሆናቸው ለየት የሚያደርገው ነው፡፡

በዚህ ክፍል ከጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስነስርአት ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ አይነት ጥናቶች ቅኝት ተካሂዶባቸዋል፡፡ ከነዚህም ብሄሩን መሰረት አድርገው ከተሰሩት መካከል በ2000 ዓ.ም የተሰራው የምንዳ ገብሬ "የጌዴኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ተረኮቻቸው" የሚለው ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ጥናት ዋና አላማው በጌዴኦ ብሄር ዝርው ተረኮችና ልማዳዊ ስርአቶች መካከል ምን ግንኙነት አለ? ዝርው ቃል ትረካዎቻቸው ክፍልፋዮች አላቸው ወይስ የላቸውም? እነዚህ ክፍልፋዮች መስፈርታቸው ምንድን ነው? የክፍልፋዮቹ አላማና ግብ ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ገላጭ መሆኑን ገልጿል፡፡ ነገር ግን ገለጻ የማቅረቢያ ዘዴ እንጅ የምርምር ስልት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ለጥናቱ የሚሆነውን የመስክ መረጃም በተሳትፏዊ የመስክ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት ዘዴዎች እንደሰበሰበ ገልጿል፡፡

በንድፈሃሳባዊ ቅኝቱ የተረክ ምንነት፣ አይነቶች፣ የተረክ መዋቅር፣ የተረክ ግልጋሎት፣ የተረክ ታዳሚ፣ የተረክ መቼት፣ የዝርው ቃል ተረክ ጥናት ባገራችን በሚሉ ንኡሳን ርእሶች ስር ከፋፍሎ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ከጥናቱ ርእስም ሆነ ከመረጃ ትንተናው እንደምንረዳው የጥናቱ አቢይ ትኩረት ተረክና ልማዳዊ ስርአቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ትኩረት ሰጥቶ በንድፈሃሳቡ ሲያትት የነበረው ስለተረክ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪ ከዋና አላማው የተገለጸው አቢይ ጉዳይ ጎሳዊ የተረክ ምደባ ሆኖ፤ ይህም የትንተናውን አብዛኛውን ክፍል ይዞ ሳለ በንድፈ ሃሳቡ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ይህም አንባቢውን ስለልማዳዊ ስርአት ግንዛቤ የማያስጨብጥ ሆኗል፡፡

በትንተናው ክፍል በቅድሚያ ትንታኔ የሰጠው በጌዴኦ ውስጥ ስለሚካሄዱ ልማዳዊ ስርአቶች ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ስለሶንጎ፣ ቄጣላ፣ ፋጭ፣ ጎንዶሮ፣ ጋብቻና ሀዘን የተነተነ ሲሆን

በሁለተኛው ክፍልም በተረኮች ጎሳዊ ምደባ ሰፋ ያለ ትንታኔ አካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት ሶስት አይነት አካባቢያዊ የተረክ ምድቦች መኖራቸውን አመልክቷል፡፡ ነገር ግን አጥኚው ይዞት የተነሳውን ሁለት አቢይ ርእሰ ጉዳይ ማለትም የጌዴኦ ብሄር ቃላዊ ዝርው ትረካና ልማዳዊ ስርአት ለማስተሳሰር የቻለና ሁለቱን ጽንሰ ሃሳቦች በተገቢው ሁኔታ ያዳረሰ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ የብሄሩ ልማዳዊ ትውፊቶች ብሎ ያነሳቸው አምስት ጉዳዮችም ሆኑ ዝርው ትረካ በራሳቸው በጣም ሰፋፊ ርእሰ ጉዳዮች በመሆናቸው ነው፡፡

ከእኔ ጥናት ጋር ያለውን ቁርኝት ስመለከት የኔጥናት ትኩረት በሆነው የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስነስርአት ውስጥ የሚነሱትን ሶንጎ፣ ፋጭና ጎንዶሮ በጣም በስሱ የቃኘ መሆኑ ነው፡፡ የሚለየው ደግሞ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ቃል ትረካ በሚለው ጥናት ልማዳዊ ስርአት ውስጥ ያስገባውን ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ በአቢይነትና በጥልቀት የማይ መሆኔ ነው፡፡ በሌላ በኩል በሱ ጥናት ዋና ዘዴ ተብሎ የቀረበው የመረጃ ማቅረቢያ ዘዴ የኔ ከመረጃ ማቅረቢያዎቼ ውስጥ አንዱ ብቻ መሆኑ መሰረታዊ የሚባሉት ናቸው፡፡

በ2005 ዓ.ም በጳውሎስ አለማየሁ “Potentials and Challenges of Indigenous Institutions for Good Governance: The case of Gada among The Gedeo” የሚል ጥናት ለማህበራዊ ስነሰብ ትምህርት ክፍል አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የጌዴኦ ገዳ ስርአትን መሰነድና መልካም አስተዳደርን በማምጣት በኩል ያበረከተውን አስተዋጽኦና ያገጠመውን ተጽዕኖ ማሳየት ነው፡፡ የጳውሎስ ጥናት ንኡሳን አላማዎችም የጌዴኦ ገዳ ሥርአቱን ታሪካዊ ሁኔታ ማሳየት፤ የጌዴኦን ገዳ ሥርአት መዋቅርና ፋይዳ መፈተሽ፤ የጌዴኦ ገዳን ባህላዊ ሥርአት መሰነድና የገዳ ሥርአቱ ለመልካም አስተዳደር የሚያመጣውን ፋይዳ መፈተሽና የገዳ ሰስርአቱ ከዘመናዊ ስርአቱ ጋር ተዛምዶ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡ የጳውሎስ ጥናት አይነታዊ ዘዴን የሚጠቀም ሲሆን ምልከታ ቃለመጠይቅና የሰነድ ምርመራን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ የጳውሎስን ጥናትና የኔን ጥናት የሚያመሳስላቸው በጌዴኦ ብሄር ላይ መሰራታቸው ነው፡፡ እንዲሁ የጳውሎስ ጥናት የጌዴኦ ገዳ ስርአት ለግጭት አፈታት ስነስርአት ያለውን አስተዋጽኦ በጥልቀትም ባይሆን ማየቱ ነው፡፡

ሌላው ጥናታዊ ጽሁፍ “Ethnicity and Inter-ethnic Relations: the ‘Ethiopian Experiment’and the Case of the Guji and Gedeo” በሚል በ2007ዓም በአሰበ ረጋሳ በፍልስፍና የሀገር በቀል እውቀት ሁለተኛ ዲግሪ ከቶሮምሶ ዩኒቨርሲቲ ለማግኘት

የተጠናው ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጎሳዎች(ብሄሮች) መካከል በሚፈጠረው ግንኙነት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ያለውን ተጽእኖና ጉጅንና ጌዴኦን ለግጭት የዳረጋቸውን ጉዳይ መመርመር ነው፡፡ በዚህ ስርም ታሪካዊ ግንኙነታቸው ለአሁን ግንኙነታቸው ያበረከተውን አስተዋጽኦ መመርመር፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተፈጠረው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ለጉጂና ጌዴኦ ግንኙነቶች ያበረከተውን አስተዋጽኦ መፈተሽ፣ የሁለቱን ብሄሮች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት ማሳየትና አሁን ካለው አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት የሁለቱን ህዝቦች የወደፊት ግንኙነት መተንበይና መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡ የጥናቱ ስነዘዴ ደግሞ አንትሮፖሎጂካል አተያይና ታሪካዊ አተያይ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ ይህን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በጉጅና በጌዴኦ መካከል የሚፈጠረውን ግጭት በባህላዊ መንገድ እንዴት እንደሚፈታ ማሳየታችን ነው፡፡

## 3. የአካባቢው ማስተዋወቂያ

ይህ ክፍል የጌዴኦ ዞን አጠቃላይ ሁኔታ የማቀርብበት ነው፡፡ በመሆኑም የአካባቢው መገኛ፣ ሕዝብ ብዛት፣ እምነት፣ ቋንቋና መተዳደሪያ በአጫጭሩ አሳያለሁ፡፡

### 3.1. የአካባቢው መገኛ

የጌዴኦ ብሄር መገኛው በጌዴኦ ዞን ነው፡፡ የጌዴኦ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ 21 ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ዞኑ 134,700 ሄክታር የቆዳ ስፋት ሲኖረው 6 ያህል ወረዳዎች አሉት፡፡ የጌዴኦ ዞን ዋና ከተማ ዲላ ነው፡፡ ይህ ከተማ ከአዲስ አበባ 365 ያህል ኪሎሜትር በስተደቡብ ሲገኝ ከክልሉ ርእሰ መዲና ከሃዋሳ በ85 ያህል ኪሜ ርቀት ላይ ከአዲስ አበባ ሞያሌ በሚወስደው ዋና መንገድ ላይ ይገኛል፡፡

ዞኑን በደቡብ በምስራቅ እና በምእራብ ኦሮሚያ ክልል ሲያዋስነው በሰሜን ከሲዳማ ዞን ጋር ይዋሰናል፡፡ ዞኑ ከ$7^0$39· እስከ$7^0$81·ሰሜን ላቲቱድና ከ$35^0$24· እስከ $37^0$ 90· ምስራቅ ሎንግቲውድ መስመሮች መካከል ይገኛል፡፡ የተፈጥሮ አቀማመጡ ከባህር ወለል በላይ ከ1201 ሜ እስከ 300 ሜ እንደሆነ ከዞኑ ግብርና መምሪያ የሩብ አመት ሪፖርት ላይ የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

የዞኑ አብዛኛው ክፍል ተራራማና ከፍተኛ ቦታ የሚበዛበት ነው፡፡እንዲሁም ከአምስት እስከ አስራ ሰባት ፐርሰንት የሚሆነው ክፍል ዝቅተኛና ረባዳ መሬት እንደሆነ ከዞኑ ባህልና ማስታዎቂያ ቢሮ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል፡፡

## 3.2. ሕዝብ ብዛት

የጌዴኦ ዞን በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙት ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ካላቸው ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የጌዴኦ ዞን ህዝብ የዞኑ ፋይናንስ ጽህፈት ቤት 2004 ዓ.ም መረጃ እንደሚያመለክተው 977,078 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 489,721 የሚሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡ የሴቶች ቁጥርም 487,357 ነው፡፡(ከጌዴኦ ዞን ፋይናንስ መምሪያ የመረጃ ማሰባሰብና ማሰራጨት የስራ ሂደት )

## 3.3. እምነት

በጌዴኦ ዞን ውስጥ በርከት ያሉ እምነቶች ይገኛሉ፡፡ በጌዴኦ ዞን የሚገኘውን የእምነት ስብጥር ስናይ ፕሮቴስታንት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና፣ ካቶሊክ፣ እስልምናና ባህላዊ እምነት ናቸው፡፡

በዞኑ ከሚገኙት እምነቶች መካከል ፕሮቴስታንት ቀዳሚውን ቁጥር ሲይዝ ባህላዊ ሃይማኖት እና ኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታትለው ይገኛሉ፡፡ በዞኑ የሚገኙት ሀይማኖቶች አብዛኞቹ በጽሁፍ የሰፈረ ዶግማና ቀኖና ያላቸው ናቸው፡፡ የጌዴኦ ሃገረሰባዊ እምነት ግን ጽሁፋዊ ያልሆነና ትውፊታዊ በሆነ መልኩ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ነው፡፡ የጌዴኦ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት በሰማይ አምላክ "ማጌኖ"[4] የሚያመልክ ነው፡፡ ይህ አምላክ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ ሰማይና ምድርን የዘረጋ ፣ ለማህበረሰቡ ክፍሎች ጥበቃ የሚያደርግና የጌዴኦ ገዳ ስርአት ባለስልጣናትን የሚሾምና የሚሽር፡፡ በትእዛዝ፣ በወግና በእምነት የሚተዳደሩትን የሚባርክ በአንጻሩ እነዚህን የሚተላለፉትን አይቀጡ ቅጣት የሚቀጣ አምላክ ነው (ቃለመጠይቅ፡ሀይቻ ቦሩ፣ 02/06/2005)፡፡

## 3.4. ቋንቋ

በጌዴኦ ዞን በርከት ያሉ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ ከሚነገሩ ቋንቋዎች መካከልም ጌዴኦኛ፣ አማርኛና ኦሮምኛ በስፋት የሚነገሩ ሲሆኑ ጉራጊኛ፣ ሲዳምኛ፣ ወላይተኛ፣ ስልጤኛ ወዘተ.

[4] ማጌኖ ተብሎ የሚጠራው አምላክ አንድ ብቻ የሆነና ሰማይና ምድርን የፈጠረ እንደሆነ የብሄሩ አባላት ያስረዳሉ፡፡ ማጌኖን የፕሮቴስታንት፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ የእስልምና፣ የካቶሊክም ሆነ ሌላ እምነት ተከታይ ሆኑ ሁሉ እንደራሳቸው አምላክ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ማለትም ለክርስቲያኖች ማጌኖ ማለት እግዚያብሄር ማለት ሲሆን ለእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ አላህ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የእንግሊዘኛው "God"አቻ ትርጉም ነው ልንለው እንችላለን፡፡

ተከታዩን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ አቶ ጥላሁን እብዶ) የአብዛኞቹ የጌዴኦ ብሄር አባላት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጌዴኦፋ (ጌዴኦኛ) ነው፡፡ ጌዴኦኛ ቋንቋ ከምስራቃዊ ከፍተኛ ቦታዎች ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ይመደባል፡፡

ጌዴኦኛ ቋንቋ ከአጎራባች አካባቢዎቹ ከኦሮሚያና ሲዳማ አካባቢዎች ጋር ባለው ከፍተኛ ቁርኝት የተነሳ በከፍተኛ ሁኔታ የቋንቋ ዝምድና አላቸው፡፡ በመሆኑም የጌዴኦኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ ሰዎች ከሲዳምኛና ከኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ይግባባሉ (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/02/03) ፡፡

## 3.5. መተዳደሪያ

የጌዴኦ ዞን አብዛኛው ማህበረሰብ በግብርና፣ በንግድ፣ በመንግስት ስራና በእደ ጥበብ ሙያ ይተዳደራል፡፡ በዞኑ ከሚገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት በግብርና ሙያ የሚተዳደሩት ናቸው፡፡ እንደወረዳው ግብርና መምሪያ የሩብ አመት ሪፖርት ማኑዋል ከዞኑ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 24% በአመታዊ ሰብል 64.04% በቋሚ ሰብል፣ 0.7% በግጦሽመሬት፣ 3% በደንና ቁጥቋጦ፣ 0.64% ሊለማ የሚችል 0.48 ሊለማ የማይችልና 6.9% በሌሎች የተሸፈነ ነው፡፡

የጌዴኦ ዞን በሶስት ተለምዷዊ ስነምህዳሮች የተከፋፈለ ሲሆን 2.2% እርጥበታማ ቆላ፣ 25.5% ደጋ%፣ 72.3% ወይና ደጋ የአየር ሽፋን ያለው ሲሆን የዞኑ አማካይ የዝናብ መጠን ከ760 እስከ 1800ሚሊ፣ አማካይ የሙቀት መጠን ከ12.6$^0$ሴንቲግሬድ እስከ 22.5ዲግሪሴንቲግሬድ ሲደርስ የመሬት አቀማመጡ ከባህር ወለል በላይ ከ1201ሜትር እስከ 3000 ሜትር ነው፡፡ በመሆኑም ከአየር ንብረቱና የመሬቱ ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሰብል አይነቶች ይበቅላሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ቡናና እንሰት በዋናነት የሚቀመጡና የዞኑ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆኑ ምርቶች ናቸው፡፡ የብእርና የአገዳ ሰብሎች በስፋት የሚመረቱ ሲሆን ፍራፍሬና የውጭ ሀገር ዝርያ ያላቸው የተፈጥሮ ደኖች የሚገኙበትም ነው፡፡

ዞኑ በባህላዊ ጥምር የአስተራረስ ልምድ የተነሳ ከፍተኛ የደን ሽፋን ያለው ነው ፡፡ ይህ የአስተራረስና ባህላዊ የአካባቢ ጥበቃ ልምዱም በገጸምድርና ከርሰ ምድር ውሃ እና ሌሎች ሃብቶች የበለጸገ እንዲሆን አስችሎታል፡፡ እንዲያውም በተፈጥሮ የሚገኙትን እና በባህላዊ መንገድ የሚለሙትን ደኖች በቅርስነት ለማስመዝገብ እንቅስቃሴ መጀመሩን ከዞኑ ግብርና መምሪያ የ2005 የሩብ አመት ሪፖርት የተገኘ መረጃ ያሳያል፡

## 4. የመረጃ ትንተና

የመረጃ ትንተናየ ከመስክ ያገኘሁትን መረጃ ከልዩ ልዩ ንድፈሀሳቦችና ሳይንሳዊ አተያዮች ጋር በማዛመድ ትንታኔ የማካሂድበት ነው፡፡ በዚህ ክፍልም በጌዴኦ ብሄር ተደጋግመው የሚከሰቱ የግጭት አይነቶችና የተሰጡ ውሳኔዎች፣ የጌዴኦ ብሄር አስተዳደራዊ ሁኔታዎችና የግጭት መፍቻ ተቋማት፣ የጌዴኦ ብሄርን የግጭት አፈታትን ስርአተ ክዋኔ አውድ እና የከባድ ግጭቶች አፈታት ሪቹዋሎች በሚሉ ንኡሳን ርእሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. በብሄሩ የሚከሰቱ የግጭት አይነቶች

በዚህ ርእስ ስር በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችን ከነመነሻ ምክንያታቸው እገልጻለሁ፡፡ በተጨማሪ ለባህላዊው የግጭት መፍቻ ሥርዓት ቀርበው የሚሰጡ ውሳኔዎችን ከአብነቶች ጋር ማለትም ደረሱ የተባሉ እርግማን ምርቃት፣ ካሳና የመብት ክልከላ ከመሳሰሉት ጋር በማጣቀስ አቀርባለሁ፡፡

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ልዩልዩ የግጭት አይነቶች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ የግጭት አይነቶች እንደሚያስከትሉት ጉዳት መጠን፣ የተጋጭዎች ማንነት፣ በሚፈቱበት የግጭት መፍቻ ተቋም እና ለመፍታት እንደሚመረጡት የመፍትሄ አካላት (የሀገር ሽማግሌዎች) በሶስት ዋናዋና ክፍሎች ከፋፍሎ ማስቀመጥ እንደሚቻል ይገልጻሉ (ቃለመጠይቅ፣ ሀይቻ ቦሩ፣ 02/06/2005፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/05/2005)፡፡ እነዚህ ሶስት ክፍሎች የሚያሳዩት የግጭት አይነቶች ካላቸው ደረጃ አንጻር ነው፡፡ እነሱም ቀላል ግጭቶች፣ መካከለኛና ከባድ ናቸው፡፡

እነዚህን ሶስት የግጭት አይነቶችና እንደ ደረጃቸው የግጭት አፈታት ስነስርአታቸውም ሆነ ግጭቶቹ የሚያስከትሉት ማህበራዊና አኮኖሚያዊ እንዲሁም ስነልቦናዊ ድቀት አየተወሳሰበ የሚሄድ ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን በየተራ ከነሂደቱና በስራቸው ከሚይዙት የግጭት አይነቶች እንዲሁም በምን መንገድ እንደሚፈቱ እናያለን፡፡

#### 4.1.1. ቀላል ግጭቶች

በጌዴኦ ብሄር ቀላል ተብለው የሚቀመጡ የግጭት አይነቶች ውስጥ ቀዳሚዎቹ በቤተሰብና በጎረቤት የሚነሱ ግጭቶች፣ ከብቶችን በሰው ማሳ ውስጥ በማሰማራት ወዘተ. በመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚፈጠር ነው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በጣም ቀላል ከመሆናቸው የተነሳ የሚፈቱት በቤተሰብ ደረጃና በጎረቤት ሽማግሌዎች ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ግጭቶች አንዳንድ ጊዜ

በቀላሉ ሳይፈቱ ከቀና ወደ ከባድ ግጭት የማምራት ሁኔታ ስለሚኖራቸው በጥንቃቄ ይታያሉ፡፡

#### 4.1.1.1. የቤተሰብ ግጭት

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ በተደጋጋሚ እየተፈጠሩ በቀላሉ መፍትሄ ከሚያገኙት ግጭቶች መካከል አንዱ የቤተሰብ ግጭት ነው፡፡ የቤተሰብ ግጭት ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው መከባበር ሲጠፋ፣ በትዳር ውስጥ በሚፈጠር አለመግባባት እንዲሁም ከውርስ ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ከጌዴኦ ብሄር እሴቶች ውስጥ አንዱ መከባበር ነው፡፡ ለምሳሌ እጅ በመታጠብ ፣ ድልድይ በመሻገር፣ ምግብ በመብላት አይነቶች ውስጥ ልጅ ለአባቱና ታናሽ ለታላቁ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አባትና ልጅ በጉርብትና እየኖሩ አባት እያለ ልጅ እርድ አይፈጽምም፡፡ እነዚህ የጌዴኦ መከባበር እሴቶች ካልተተገበሩ በቤተሰብ መካከል መቃቃርና ተደፈርኩ ብሎ ማሰብ ይመጣል፡፡ ይህ እንግዲህ ከበድ ወዳለ ደረጃ ላይ ካልደረሰ መፍትሄ የሚያገኘው በመጀመሪያው የግጭት መፍቻ ተቋም(በቤተሰብ ጉባኤ) አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ የግጭት መፍቻ ተቋም ቀርቦ ጉባኤው ጉዳዩን ባየበት አቅጣጫ ማለትም ቀላል ጥፋት ነው ብሎ ካሰበ ምክርና ቀለል ያለ ቅጣት ከባድ በደል ነው ብሎ ካመነ ግን ከቤት እንዲባረር ከማድረግ ጀምሮ እስከመርገም ድረስ ይቀጣል፡፡

አጥፊው ጥፋቶችን እየደጋገመ የሚሰራ ከሆነና የቀደሙትን ደረጃዎች አልፎም የማይታረም ከሆነ እንዲገረፍ ይወስንበታል፡፡ በዚህም መሰረት የሚገርፉ ጎረምሳዎች ከቤተዘመድ አባላት ይመረጡና እሰሩ ተብለው ይታዘዛሉ፡፡ ከዛም የቤተዘመድ አባላቱ ልጁን እጅና እግሩን በጣም ሊያሰቃይ በሚችል ሁኔታ ከግንድ ጋር ያስሩታል፡፡ ሲታሰርም ለቤተሰቡ በተለይም ለአባቱ ያለውን ክብር ለማሳየት ምንም አይነት ተቃውሞና ላለመታሰር የመሞከር ነገር አያሳይም፡፡ ምክንያቱም ላለመታሰር መሞከር በቤተሰቡ ውስጥ ያሉትን አካላት ያለማክበሩን ስለሚያሳይ አባቱ ተበሳጭቶ ሊያዝንበትና ሊረግመው ስለሚችል ነው፡፡ ከዛ በኋላ አባት ራቅ ብሎ በመቀመጥ ይበቃዋል ከስህተቱም ያርመዋል ብሎ እስኪያምን ድረስ እንዳይሞትና የአካል ጉዳት እንዳይርስበት በሚያደርግ ሁኔታ በደንብ ይደበደባል፡፡ የሚፈታውም ልጁ ከጥፋቱ መማሩን ካመኑ በኋላ ነው፡፡ አባት ይህን ያደረጉት ለቤተሰባቸው መረጋጋትና ልጃቸውን ከጥፋት እንዲታረም በማሰብ ነውና ማንም ለምን ብሎ አይጠይቃቸውም (ቃለመጠይቅ፤ተካ ቦሩ፣ 26/05/2005)፡፡

ይህ የቤተሰብ(የአባትና ልጅ) ግጭት ስር የሰደደ ከሆነና አባት በልጃቸው ላይ ተስፋ የቆረጡ ከሆነ ግን የማያዳግም እርምጃ ይወስዱበታል፡፡ ይህ እርምጃም እርግማን ነው፡፡ እርግማኑም ከአባቱ እንደበት የወጣው በሙሉ አንዱም ሳይቀር ይደርሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አይን እምቢ ይላል፤ እግር ይሰበራል፤ አይተርፍም፡፡ ጆሮ ይዘጋል፡፡ ስለዚህ ይህን ያህል አባቱን ላለማስቀየም ይጥራል፡፡አባቱም የሚታረመውን ልጅ በአጭር ላለመቅጨትና የአካል ጉዳተኛ ላለማድረግ ሲሉ አይረግሙም (ቃለመጠይቅ፣ ተካ ቦሩ፣ 26/05/2005)፡፡

በእውነትም የአባት እርግማን የደረሰባቸውና ህይወታቸው የተመሰቃቀለባቸውን ሰዎች አስመልክተውም ለልጆቻቸው እንዲሁም ወደ እርግማን ለሚጠጉ ሰዎች የማስጠንቀቅ አላማ ያላቸውን እውነተኛ ናቸው የሚባሉ ትረካዎች ያቀርቡላቸዋል፡፡ ለአብነት ያህልም

> አንድ እናትና አባቱ ማየት የተሳናቸው ሆነው ሳለ እነሱን በመርዳት ፋንታ እየሰከረና በር እየደበደበ ሲያስቸግር ተው እንዲህ አይነት ነገር አይጠቅምም ብለው ቢመክሩት እምቢ ብሎ ያስቸገረን ልጅ አባትየው እኔን አይነስውሩንና ደካማውን በሬን እየደበደብክ እንዳስቸገርከኝ ችግሬን እንድታየው አንተም አይነስውር ሆነህ ልጆችህ ያስቸግሩህ፡፡ የኔን ሀዘን ላንተ ይስጥህ አባቴ እንዲህ ብሎ አዝኖብኛል ብለህ የምታስታውስበት ቀን ይምጣ ተብሎ ተረገመ ይሄው በወጣትነቱ አይነስውር ነው እድናለሁ ብሎ ሃብቱን በየሀኪም ቤቱና ጠንቋይ ቤቱ ጨርሷል ልጆቹ ሲያስቸግሩትና ሲያስቃዩት ይውላሉ፡፡ አሁን ተጸጽቻለሁ ይላል፡፡ የፈሰሰ ውሃ አይመለስም...(ጥላሁን እብዶ፣ ቃለመጠይቅ፣ 30/05/2005) የሚለውና ፡-
>
> አንድ ጎረቤታችን ነበር ልጁ ዱርየ ሆኖ ቁም ነገር እምቢ ብሎ አስቸገረው፡፡ ከዛ በኋላ መከረው አስመከረው ተው አለው፡፡ አስገረፈው፡፡ በሽንጎ ተናገረ በቃ ተው አለው ተው አለው እምቢ አለ፡፡ ከዛ እንግዲህ አታርግ ስልህ እኔን ናቅሽኝ አይደል...እግዚያብሄር ይናቅህ የኔን አባትነት እንደካድክ ጌታየ ይካድህ፡፡ አትባረክ፡፡ አሁንም ማፈሪያ ነህ ከዚህ በላይ ማፈሪያ ሁን፡፡ ለዘር አትብቃ፣ የተናቅህ የተዋረድህ ሁን አባቱን አሳዘኖ እንዲህ ሆነ ተባል፡፡ ሰው ይፍረድብህ አሉት፡፡ አሁን ልጁ እያደር እየመነመነ ሂዶ እዚህ ከተማ ውስጥ አብዶ የወደቀ ቆሻሻ ጫት ሲበላ...ይውላል...በቃ ቀውስ ነው የተናቀ ነው፡፡ የሚያዝንለት ምጽዋት የሚሰጠውም የለም፡፡ በቃ አሁን የሰይጣን መጫዎቻ ሆኗል፡፡ አሁን ልብሱንም በቅርብ አወለቀ አሉኝ አይኑም ጆሮውም ተደፍኗል፡፡ የአባት እርግማን እንዲህ ያደርጋል (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታዮ ሞላ፣ 08/06/2005)

ሌላው ከቤተሰብ ግጭት ውስጥ የሚመደበው የባልና ሚስት ግጭት ነው፡፡ ይህ ሊፈጠር የሚችለው ባል በሚስቱ ላይ ቀናተኛ ሲሆን፣ በየጊዜው በውሃ ቀጠነ ሲጨቃጨቃት፣ መብቷን አብዝቶ ሲጥስ ማለትም አንዲት የጌዴኦ ሴት ባለትዳር ከሆነች በኋላ የምትጠቀምበትን የመዋዋቢያ ነገሮችን ሲከለክላት ወይም ልብሷን በተገቢው ጊዜ ካልገዛላት፣ ሹርባዋን እንድትሰራና ቅቤ በየጊዜው እንድትቀባ ካላደረገ፣ እንደ አንባር

አይነት ጌጣጌጥ ካላሟላ የሚለው በእሷ በኩል ሲሆን በእሱ በኩል ደግሞ ሚስቱ ምግቡን በተገቢው ጊዜ ካልሰራች፣ የሚገባውን ክብር ተሽቆጥቁጣ ካልሰጠች ማለትም ሲገባ እግሩን በሙቅ ውሃ ማጠብ ቆማ ምግብ እንዲበላ ማድረግ፣ ጎጆዋን መንከባከብና እንስትን በንጽህና አዘጋጅታ ማቅረብ በሚሉት ምክንያቶች ሊጋጬ ይችላሉ (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/ 05/2005)፡፡

ከላይ በተዘረዘሩትም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ካልተግባቡ ባል ሚስቱን በመደብደብ ሊያርማት ይሞክራል፡፡ ምክንያቱም በጌዴኦ ብሄር ባህል መሰረት ሚስቱን የማረም ሃፊነት ያለበት በመጀመሪያ አባወራ ስለሆነ እየደበደባትም ቢሆን እንዲያርማት ባህሉ ይፈቅድለታል፡፡ ነገር ግን የባልና ሚስት ግጭቱ በመርገብ ፋንታ እየከረረ ሄዶ ባልና ሚስቱ ግጭታቸውን ሰው እንዲያውቅላቸው ከፈለጉ ሁለቱም የሚያደርጉት ነገር የተለያየ ነው፡፡ በግጭቱ አስቀድማ የተማረረችው እሷ ከሆነች ወደ ቤተሰቦቿ በመሄድ ችግሯንና ከቤቷ የወጣችበትን ምክንያት ለእናቷ ታስረዳለች፡፡ ከዛ በኋላ በሰፈር ሽማግሌዎች ይመከራል እናም ወደ እናቷ ቤት በመሄድ ደጋግሞ ደጅ ከጠና በኋላ ጥፋቱ እውነትም የሱ ሆኖ ከተገኘ ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ይህ ካሳ ግን ከጌጣጌጥ የሚያልፍ አይደለም፡፡

የባሏን ጥፋተኝነት በሰው ፊት አሳምና ካሳዋን የተቀበለች ሴት ጉዳዩን ሙሉ ለሙሉ ይቅር ብላ ወደ ቤቷ ትመለሳለች፡፡ ምክንያቱም በእርቅ ስነስርአቱ ወቅት ቤተሰቦቿም ሆኑ የሰፈር ሽማግሌዎች ትእዛዛቸውን ስለሰማቻቸው ሳታንገራግር ስለተቀበለች ይመርቋታል፤ እምቢ ብትል አንድም ማህበራዊ ሕይወቷ ይጎድፋል አንድም እምቢተኝነቷ እርግማን ያስከትልባታል፡፡ ይሄም ከፍተኛ የሆነ ስነልቦና ተጽኖ የሚፈጥር ነው፡፡ በአንጻሩ ሴቷ ብትበደልም ችላ ምንም ቢሆን ከቃላችሁ አልወጣም ካለች ፈጣሪም የቤታቸውን ሰላም ለማውረድ ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ቤታቸው ውስጥ ደስታ ይሰፍናል ማለት ነው፡፡ ይህን አስመልክተውም አቶ ቦሩ ደረሰ ያሉት ታሪክ፡-

> እንዲያውም ባለፈው እህቴ ከባሏ ጋር ተጋብታ መኖር ከጀመረች ወደ ስምንት አመት ቢሆናትም ልጅ አልወለዱም ነበር፡፡ እና ቀስ እያለ ፍቅር እየጠፋ ሄደና በየጊዜው እየተጣሉ ተቸገርን ከዛማ አልመለስም ወደቤቱ ብላ ስታስቸግር የሰፈር ሽማግሌዎች ሲቆጧት ከቃላችሁ አልወጣም ትልና ታስደስታቸዋለች፡፡ ከዛ መረቋት ማህጸንሽን ይክፈተው ውለጅ፣ ብሩክ ልጅ ውለጅ፣ ቤትሽ ሰላም ይሁን ብለው መረቋት ከዛ በአመቱ መንታ ልጆችን በሰላም ተገላገለች ቤታቸውም ደስታው ሃብቱ ተመልሷል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ዳንኤል፣ 07/06/2005)

ከዚህ ቃላዊ ትረካ እንደምንረዳው በትዳር ውስጥ ከባለትዳሮች መፋቀርና አብሮ ለመኖር ከሚካሄድ ስምምነት ውጭ የሀገር ሽማግሌዎች በጎ ተጽእኖ ልዩ ቦታ እንዳለው ነው፡፡

ምክንያቱም የሀገር ሽማግሌዎች ምርቃት እና እርግማን የተጋቢዎቹን ሰላም ይመልሳል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ከፍች የሚቀድም ነገር በቤቱ ውስጥ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይህም በፍች ምክንያት የሚኖረውን የቤተሰብ አለመረጋጋት የመቀነስ በጎ ተጽእኖ ነው ልንለው እንችላለን፡፡

በባልና ሚስቱ ግጭት አስቀድሞ የተማረረ እሱ ከሆነ ጥዋት ከእንቅልፉ እንደተነሳ ግጭታቸውን ይፈቱልናል ብሎ ያመነባቸውን ሽማግሌዎች በሱና በሷ በኩል ጠርቶ እያስቸገረችው እንደሆነ በማስረዳት እንድትመከርለት ያደርጋታል፡፡ በዚህ መንገድ ግጭቱ እንዲበርድ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ከላይ የተገለጹት የሽምግልና ሂደቶች ፍሬ ሳይኖራቸው ቢቀር በቀጥታ ወደፍች የሚያመሩት ሴቷ አምስት ልጅ ከወለደች በኋላ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም በጌዴኦ ብሄር አባላት ዘንድ የሚታመነው አንዷት ሴት ቀልብ የምትገዛው (አርቃ ማሰብ የምትጀምረው) አምስተኛ ልጇን ከወለደች በኋላ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም አምስት ልጅ እስክትወልድ ድረስ ባል የሚስቱን ታታሪነት በጉጉት ይጠብቃል እንጅ ለፍች ውሳኔ አይቸኩልም፡፡ ይሄ እሴትም ሴትን ልጅ አምስት እስክትወልድ ጊዜ ድረስ በራሷ ብቁ ያልሆነች የሚያስመስል ርእዮተ አለም በውስጡ ያለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በተጋቢዎች መካከል የሚፈጠር ግጭት የማይቀር ከመሆኑ የተነሳ በጣም ረዥም ጊዜ በወሰደ የመቻቻል ባህል ትዳሩን ከፍችና ቤተሰቡን ከአለመረጋጋት የሚጠብቅ ነው፡፡

#### 4.1.1.2. በጎረቤታሞች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች

በጎረቤታሞች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች በሁሉም ደረጃዎች (በቀላል፣ በመካከለኛና በከባድ) ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ አብዛኞቹ በመካከለኛና በከባድ ግጭት ደረጃ ለይ የሚገኙ ግጭቶች መነሻቸው በቀላል ደረጃ ላይ እያሉ መፍትሄ ያለማግኘታቸው ነው፡፡ ከእነዚህ የግጭት አይነቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰቱት ሴቶችና ህጻናትን የሚመለከቱ ቀላል የሚመስሉ መጎሻሸሞች፣ የድንበር መገፋፋትና ቀላል ስርቆቶች ናቸው፡፡

በሴቶችና ህጻናት አማካኝነት የሚፈጠሩት ግጭቶች ልጅና ልጅ በየጊዜው ሲጣሉ እናቶች ለልጆቻቸው በማገዝ የጎረቤት ልጅን ሲቆነጥጡና ሲቆጡ እናቶችም በበኩላቸው ልጃቸውን የጎረቤት ሰው እንዲቀጣባቸው ያውም በመድልኦ ስለማይፈልጉ ትንሽ የሚመስል ቁርሾ ላይ ይገባሉ፡፡ ይህ ትንሽ ቅያሜ ግጭት የሚሆነው ብዙ ጊዜ ብቻውን ሳይሆን ከሌላ ግጭት ፈጣሪ ምክንያት ጋር በመዳመር ነው፡፡ ይህን ግጭት ለመፍታት ቀዳሚዎቹ የየቤቱ አባወራዎች ናቸው፡፡ አባወራዎቹ በየቤታቸው ያሉትን ሚስቶቻቸውን በመቆጣት

ግጭቱን ለማብረድ ይሞክራሉ፡፡ በነሱ አልፈታ ካለ የሰፈር ትልልቅ ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው ሁለቱንም በመገሰጽና በመምከር ሊያስታርቋቸው ይሞክራሉ፡፡ የአካባቢውን ሽማግሌዎች የማስታረቅ አቅም አንደኛው ወገን ያልወደደው ከሆነ ለአካባቢው ሶንጎ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

በገደብ ሶንጎ ምልከታ ካሄኩበት ወቅት በጎረቤታማቾች መካከል የተፈጠረ ግጭት ሲዳኝ አንዲት ነብሰጡር ሴት የጎረቤት ልጆች እየሰደቧት እንደሆነና አባታቸውም እርምጃ እየወሰሰደባቸው ያለመሆኑን ገልጻ የልጆቹ አባት ላይ ክስ አቅርባ ነበር፡፡ ሽማግሌዎቹም የተከሳሹን መልስ ከሰሙ በኋላ ሁለቱንም ወገኖች ገስጸው በተለይ ደግሞ የከሳሿን ባለቤት ለምን ሚስቱን እንደማይቆጣርና የቤቱና የአካባቢውን ጉድ ለምን ሸንጎ ድረስ እንዳመጣ በቁጣ ስሜት ከገሰጹት በኋላ ሁለተኛ ቢጣሉ ለሸንጎው 2000(ሁለት ሽህ) ብር ለመንግስት ደግሞ 5000(አምስት ሽህ) በድምሩ 7000(ሰባት ሽህ) ብር እንደሚቀጡ በማስፈረም እዛው ላይ ይቅር ተባብለው እንዲሄዱ አድርገዋቸዋል፡፡

### 4.1.2. መካከለኛ ደረጃ ግጭቶች

በዚህ ደረጃ ላይ ሰፍረው የምናገኛቸው ግጭቶች ለቤተሰብ ጉባኤ ከበድ ያሉ ለአካባቢው ሶንጎ እንዲሁም ማስታረቅና ማስተዳደር ስራቸው ላልሆነ ግጭት ፈችዎች በቀላሉ ሊፈቱ የማይችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በአብዛኛው በቀላል ግጭት ደረጃ ላይ እያሉ መፍትሄ ስላልተሰጣቸው እየተባባሱ የሄዱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከመጀመሪያውም በብሄሩ አባላት ዘንድ ከበድ ያለ የቁጣ ስሜት የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡ በዚህ ስር የሚመደቡ የግጭት አይነቶች መካከል ከበድ ያሉ ስርቆቶች፣ የድንበር መገፋፋት፣ ብድርን መካድ፣ ድብደባና አካል ማጉደል ዋናዋና የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች ከሽምግልና ባለፈ በሶንጎዎች እልፍ ካለም አባ ገዳ ድረስ ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ግጭቶች መፍትሄ ለማግኘት ይነስም ይብዛም የየራሳቸው የሆነ ቀላልና መካከለኛ ስርአተ ክዋኔ ይጠይቃሉ፡፡ እነዚህ ስርአተ ክዋኔዎች ብዙ ጊዜ ስነልቦናዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው፡፡

#### 4.1.2.1. ስርቆት

ከጌዴኦ ብሄር እሴቶች መካከል አንዱ አለመስረቅ ነው፡፡ ስለዚህ የሰረቀ ሰው የሰረቀበትን ምክንያት የሚያሳይ ምልክት አስቀምጦ እንዲሄድ ባህሉ ይፈቅዶለታል፡፡ ይሄውም ሌባው ከሰው ማሳ ገብቶ ቡና ሊለቀም፣ ከሰው ጋጣ ገብቶ እንስሳትን ሊሰርቅና ከብቶቹን የሚያበላው ነገር ካጣ ከሰው ማሳ ሳር ሊያጭድ እንዲሁም የራሱ ያልሆነን እንሰትና እህል

ከማሳም ሆነ ከተቀመጠበት ቦታ ያለባለቤቱ ፈቃድ ሊጠቀም ይችላል፡፡ ነገር ግን ሌባው ባለቤቱ እንዳይረግመውና እንዳያስረግመው ከሰረቀበት ቦታ ላይ ለምለም ሳር አስቀምጦ ይሄዳል፡፡

ይህ ሳርም የሰረኩት እኔ ወንድምህ (ጎረቤትህ) ነኝ፡፡ የሰረኩህም ልጎዳህ ፈልጌ ሳይሆን እኔንም ሆነ ቤተሰቤን ርሃብ ሊጨርሰን ስለሆነ ብንሞት አንተም ትጎዳለህ ብየነው፡፡ ስለዚህ እኔ ላይ ሆላ[5] አስብለህ እንዳልሞትብህ፡፡ የሚል መልክት የሚያስተላፍ ነው፡፡ይህ ተቸግሮ የሰረቀ ሰው  የሚያስተላፈው መልእክት በመሆኑ ማን ይሆን የተቸገረ ዘመዴ በማለት የተሰረቀው ወገን ለሌባው ይጨነቅለታል እንጅ ሊጎዳው አያስብም፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥም እንዲጎዳ በማሰብ እርግማን አይካሄድም፡፡ የሰረቀው ሰው ግን ሌባ ሆኖ ማንም አያውቅብኝም በሚልና እንዳይረገም በማሰብ ቄጤማ ቢያስቀምጥ አምላክ ተቆጥቶ የማያዳግም እርምጃ ይወስድበታል ተብሎ ይታመናል (ቃለመጠይቅ፣ ምጃኔ ጎበና፣ 02/06/2005 ) ፡፡

በሌላ በኩልም የሰረቀበት ቦታ ላይ የሚያስቀምጠው ለምለም ሳር መሆኑ ሰውየው ሲሰርቅ አብሮት የነበረው ክፉ መንፈስ በተሰረቀው ነገር ላይ እንዳያርፍና ቀሪውን እንዳያጎድለው ወይም በመሰረቁ የተናደደው ሰው የጠፋበት ንብረት ቦታ ላይ ቄጤማ ሲያይ መንፈሱ እንዲረጋጋ በማሰብ ነው፡፡ ቄጤማ አረንጓዴ ነው፡፡ ጌዴኦ ደግሞ አረንጓዴ ነገር ይወዳል[6] (የቡድን ቃለመጠይቅ፣ ቡሌ፣ 20/08/2005)፡፡

በሌላ በኩል ግን የሚሰርቀው ሰው ስራው ሌብነት ከሆነና የሰረቀው ነገር ከባድ ሆኖ እንዲሁም ያን ርጥብ ቄጤማ ሳያስቀምጥ ከሰረቀ ከዛም የሌባው ማንነት ሳይታወቅ ከቀረ የሰፈሩ ሰዎች አሳደው ለመያዝ ይሞክራሉ፡፡ ካለዛ ግን ንብረት የተሰረቀበት ሰው ለሸንጎ ሃላፊዎች ሄዶ የደረሰበትን ነገር በማስረዳት ሆላ እንዲባል ይጠይቃል፡፡ ከዛም የአካባቢው ሰዎችና የሸንጎው አስተዳዳሪ በተገኙበት በጥዋት ምግብ ሳይበሉና ውሃ ሳይነካቸው ሶንጎ በመሄድ በአንድ ላይ ሆላ ይላሉ፡፡ ሆላ ማለት ተጋለጥ ማለት ነው፡፡ ሆላ ሲባል የአካባቢው ሰው በአንድ ላይ ሆኖ  የጎዳቸው እንዲጎዳ ጸሎት የሚያቀርቡት  ነው፡፡ ይህ ጸሎት

---


[5] ሆላ አንድን ተደብቆ የሰረቀ ሌባ እንዲጋለጥ የሚደረግ የጋራ የሆነ ጸሎት ነው፡፡ ይህ የጸሎት አይነት የብሄሩ አባላት በጋራ  በመሆን የሰረቀው  ሰው ወይም ተጸጽቶ የሰረቀውን ነገር እንዲመልስ ካለዛም ክፉ ነገር ደርሶበት ለሰው መቀጣጫ እንዲሆን ምግብ ሳይበሉና ውሃ ሳይነኩ የሚያደርሱት ጸሎት ነው፡፡

[6] በጌዴኦ ብሄር አረንጓዴ የክብር መግለጫና የቅዱስ መንፈስ መጥሪያ ነው፡፡ ከግጭትአፈታት በተጨማሪ በሌሎች ክብረበአላት ለምሳሌ በደራሮ በአል በአባ ገዳ የንግስና በአልና ሌሎች ጸሎቶች እንዲሁም በብሄሩ የየአ ጉባኤ ወቅት ምንጊዜም ቢሆን አረንጓዴ ቅጠል ይነጠፋል፡፡ አባገዳውም በስርአተ ሲመቱ ወቅት ወደሶንጎው ሲገባ በባዶ እግሩ ሆኖ በመንገዱ ላይ ክብሩን ለመግለጽ የኮባ ምንጣፍ ተነጥፎለት እንደሚሄድ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ የቪዲዮና የፎቶ ግራፍ ዶክመንቶች ተመልክቻለሁ፡፡ የብሄሩ አባላት ለደን ጥበቃ ያላቸው ልዩ አመለካከትና የአካባቢ ጥበቃ ልምዳቸው ጠብቆ የያዛው የበርካታ ሀገር በቀል ዛፎች ባለቤትነታቸው ሌላው የጌዴኦና አረንጓዴ ነገርን ትስስር የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም በብሄሩ ልዩ ክብር የሚሰጠው የሸንጎ ቦታም በልዩ ልዩ እጽዋት የተከበበ መሆኑ ሌላው በጌዴኦና በአረንጓዴ ነገሮች መካከል ያለውን ቁርኝት የሚያሳይ ነው፡፡፡

በሃይማኖት መሪዎችና በሶንጎ አስተዳዳሪዎች የሚመራ ሲሆን የሰረቀው ሰው ከመካከላቸው ቢኖርም ሆነ ከመካከላቸው ባይገኝ በጸሎት ይረግሙታል፡፡ ይህ እርግማን ሌባው ላይ እንደሚደርስ ስለሚታመን አንዳንዴ ሆላ እንደሚባል ከተነገረ ሆላ ሳይባል ራሱንም ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ የሆላው ይዘትም

> ይብላኝልህ ለዛ ለሌባው፡፡ እግዚያብሄር ያጋልጥህ፣ እግዚያብሄር ያጥፋህ፣ ያሽመድምድህ፣ የሰረከውን እንድትመልስ ያድርግህ፣ ከበላኸውም አይስማማህ፣ ከበላኸውም እግዚያብሄር አንተን እንደቁንጣን ይግደልህ፡፡ እንደበላኸው አንተን አውሬ ይብላህ፡፡ አታምልጥ ምድር ትያዝህ፣ አታምልጥ፣ ያፍዝዝህ፡፡ በማለት ይረግሙታል፡ ፡... ሆላ ይፈራል፡፡ በጣም ይፈራል፡፡ ስለዚህ ፈርቶ እኔነኝ ካለ ሆላ አይባልም መልስ ወይ ክፈል ወይ ይቅርታ ጠይቅ ካስ ምናምን ይባላል ይቀርለታል፡፡ ካላለ ግን ሆላ ክፉ ነው... ይቀስፋል እኮ! (ጥላሁን እብዶ፡ቃለመጠይቅ-30፣ 05፣ 2005)፡፡

በዚህ መልክ ሆላ ሲባል ሆላ ሊያስብል የመጣው ሰው በጉልበቱ መሬት ላይ በመሆን መሬት ላይ ያለውን ሳር በመያዝ አሜን ማለት ይኖርበታል፡፡



ፎቶ ግራፍ አራት፡- ቤታቸው በመዘረፉ ሆላ የተባለላቸው ሴት ሆላ በሚባልበት ወቅት

ስለዚህ የስርቆት ወንጀል የፈጸመ ሰው የሰረኩት ተቸግሬ ነው አንተ ጋር እያለ እኔ ጾሜንባድር ፈጣሪም አይወድም በሚል ባህሉ በሚያዘው መሰረት የሰረቀበት ቦታ ላይ ምልክት ትቶ ከሄደ ስርቆቱ ወንጀልነቱ ቀርቶ እንደ እርዳታ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን ምልክት ያስቀመጠን ሰው ማስረገም የተቸገረን ለመርዳት ያለመፈለግ በመሆኑ የፈጣሪ ቁጣ ከሌባው ይልቅ በተሰራቂው ላይ ይሆንና እርግማኑ በሱ ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡ በአንጻሩ የሰረቀው ሰው ማን ሊሆን ይችላል ብሎ በማሰብ ለመርዳት መሞከር የበለጠ ክብርን የሚያጎናጽፍ ተግባር ነው፡፡

ሰርቆ የተሰወረንና ዘረፋ ያካሄደን ሰው ግን በመጀመሪያ አሳዶ ለመያዝ በመሞከር ካልተቻለ ደግሞ በአለበት ሆኖ እንዲጎዳ ወይ ንብረቱን እንዲመልስ ሆላ የማድረግ ስነስርአት ይፈጸማል፡፡ ሆላ ሊደረግ ሲል ወይ በፍጥነት ጥፋቱን ካመነ ወይም ሆላው ሰርቶ ወንጀለኛው በይቅርታ ከተመለሰ ካሳ ሰጥቶና ይቅርታ ጠይቆ ከተሰራቂ ጋር ይታረቃሉ፡፡ ስለዚህ በነዚህ ሶስት አይነት እርምጃዎች ንብረታቸው የተሰረቀባቸው ሰዎች ስነልቦናዊ እረፍት ያገኛሉ፡፡ የመጀመሪያው ከመሰረቅ ይልቅ እርዳታ እንዳደረገ ስለሚሰማው፣ ሁለተኛው የሰረቀው ሰው በእርግማኑ የተነሳ ፈጣሪው እንደሚበቀልለት ስለሚያስብ ሶስተኛው ደግሞ አጥፊን በህዝብ ፊት ሌብነቱን አስመስክሮ በይቅርታና ካሳ ስለተበቀለ ነው፡፡ በአንጻሩ ሶስቱም አይነት ሌቦች ደረጃው የተለያየ ይሁን እንጅ ስነልቦናዊ ቅጣት ይገጥማቸዋል፡፡

#### 4.1.2.2. ድንበር መግፋት

በጌዴኦ ብሄር ከበድ ያለ ጠብ ከሚፈጥረው ጉዳይ ውስጥ አንዱና ዋነኛው የድንበር ግጭት ነው፡፡ ይህ ግጭት እስከ ደም መፋሰስም ሊያደርስ ይችላል፡፡ በመሆኑም በጌዴኦ ብሄር አባላት ዘንድ የድንበር ላይ ግጭት እንዳይነሳ ላንጤ የተባለ ተክል በድንበር ላይ ይተከላል፡፡ ይህን ተክል አስመልክተው አቶ ጥላሁን እብዶ ሲያስረዱ

> ላንጤ የሚባል ጨርሶ የማይጠፋና የቃልኪዳን ምልክት የሆነ ተክል አለ፡፡ ላንጤ ለሌላ ሃይማኖታዊ ክብረ ብአልም ቃል ኪዳንን ስለሚያሳይ ይገኛል፡፡ ይህን ተክል የሚተክለው በሉባ ደረጃ ያለ ማለትም አባገዳ ሊሆን የሚችል ሰው ነው፡፡ ሉባ ያልደረሰ ሰው አይተክለውም፡፡ ሲተክሉም በሁለቱ ሰዎች ደንበር ላይ ፊታቸውን ወደኋላ ዞረው ነው፡፡ በሚተክሉበት ወቅት ይህን ከነቀልክ እንደተክሉ ይንቀልህ፡፡ አይንህ ይታዎር እጅህ ጉንድሽ ይሁን በማለት ነው የሚተክሉት፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡ ላንጤውን ነቅሎ ድንበር ለመጋፋት ይፈራል፡፡ ... በዚህ ድንበርን የማካለልና ላንጤ የመትከል ስነስርአት ወቅት ከየጎሳዎች የተውጣጡ አራት ወይም አምስት ምዮዎች (የሃይማኖት አባቶች) ይገኛሉ፡፡ እነሱ ባልተገኙበት የሚካሄድ ላንጤ ተከላ በሌላ ጊዜ ለግጭት ሊያጋልጥ ይችላል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶጥላሁን እብዶ፣ 30/ 05/ 2005)፡፡

ስለዚህ በድንበር ላይ የተከሰተ ግጭት ሌላ አይነት ጉዳት ሊያመጣ ካልቻለ በስተቀር መፍትሄ የሚመጣለት ግጭቱ በተፈጠረበት ቦታ ላይ ላንጤ በመትከል ነው፡፡ የማስተዳደርና ሃይማኖትን የመምራት ማህበራዊ ስልጣን ያላቸው ሉቦዎችና ምዩዎች ላንጤ ተከላ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ የሆነውን ትእምርት ይይዛል፡፡ ይህም እንደ ሃይቻ ቦሩ ገለጻ የሃይማኖት አባቶች አይተክሉም ያያሉ እንጅ ሃዩ ደግሞ አያይም ይተክላል እንጅ ስለዚህ አስተዳዳሪ የተከለውን የእግዚያብሄር ሰው እያየው ስለሆነ የተተከለው

መቃዎምም አምላክን መቃወም ነው ተብሎ ያታሰባል (ቃለ መጠይቅ ሃይቻ ቦሩ፣ 02/06/2005)፡፡ የጌዴኦ ብሄር አባላት በምንም መንገድ ቢሆን ዎዮዎች(አስተዳዳሪዎች)ና ሃዩዎች(የሃይማኖት አባቶች) የሚያዟቸውን አንዱንም ሳይተው ይፈጽማሉ፡፡ ምክንያቱም የሃዩዎችና የዎዩዎች ስልጣንና ሃላፊነት ከላይ ከማጌኖ(ከሰማይ አምላክ) የመጣ መሆኑ ስለሚታመን ነው፡፡

### 4.1.2.3. ገንዘብን የሚመለከቱ

የጌዴኦ ብሄር አባላት በተለያየ ምክንያትና አጋጣሚ ለሰው ገንዘባቸውን ያለማስረጃ ይሰጣሉ፡፡ በዚህ የተነሳም ተበዳሪ የወሰደውን ገንዘብ አልሞላ ብሎት ወይም ገንዘቡን መመለስ አሳስቶት ሳይመልስ ሊቀር ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳም በአበዳሪና በተበዳሪ መካከል ቂም መያያዝና ቁርሾ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህን ቁርሾ ለማብረድም የሃገር ሽማግሌዎች እጃቸውን ያስገባሉ፡፡ በዚህም መሰረት አበዳሪው ምን ያህል ገንዘብ በአይነት ከሆነም ምን እንዳበደረውና እንዳዋሰው ይጠይቁታል፡፡ የሱን ገለጻ ከሰሙ በኋላ ተበዳሪውንም ሄደው ምን እንደተበደረ ወይም እንደተዋሰ ይጠይቁታል፡፡

የሁለቱም ሃሳብ አንዳይነት ከሆነ ወይም አበዳሪ እውነቱን ከተናገረ ተበዳሪም ካመነ ብዙ ነገሮችን ግምት ውስጥ ያስገባ(ሁለቱንም የማያበሳጭ) የመክፈያ ጊዜ ለተበዳሪው ይሰጠዋል፡፡ በዚህም ይፈርማል፡፡ የሚፈርመውም በተባለው ጊዜ ሊያስረክበው ካልሆነ ግን ሽማግሌዎቹ የራሳቸውን ውሳኔ ሲያሳልፉ ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በተቃራኒው ሆኖ መካካድ ካለ ማለትም አበዳሪ ብዙ ቁጥር ያለው ገንዘብ ወይም ውድ እቃ ነው ያበደርኩት ቢልና ተበዳሪው ወይ ዝቅ አድርጎ ቢያስብ ወይንም ጨርሶ ቢክድ ሽማግሌዎቹ ተውሶ ወይም ተበድሮ መካድና የሰው ገንዘብ መፈለግ ያላቸውን መዘዝ አንድ በአንድ ለሁለቱም ወገኖች የቀደመ ታሪክ እያጣቀሱ ያስረዷቸውና እንዲምሉ ያዟቸዋል፡፡ የአማማሉን ሁኔታና የሚያስከትለውን ውጤት በሚመለከት አቶ ጥላሁን እብዶ፡-

> ጥቂት ገንዘብ ከሆነ እዛው በቤተዘመድ ወይም በአካባቢው ባለ ሶንጎ እንዲማማሉ ተደርጎ ሊያልቅ ይችላል፡፡ ብዙ ብር ከሆነና ከካደ ግን በብዙ ሽማግሌ ይጠየቃል፡፡ አሁንም ከካደ ለጌዴኦ ጠቅላይ ሸንጎ (ኦዳያአ) የሚባል አለ፡፡ ከዛ ቃርሶ(የድንጋይ መሳያ) አለ፡፡ ይህ ሰባቱ ነገዶች የተማማሉበት ነው፡፡ ድንጋዩ እንደምላጭ ነው፡፡ ከሃዲው እዛ ሄዶ ከወሰድኩ እንደዚህ ቃርሶ ያድርገኝ ይላል፡፡ ከፈራ ግን ያለበትን ገንዘብ በሙሉ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ለመማልም ሆነ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ የሸንጎው አባላት ይረግሙታል፡፡ ከተረገመ በሶስት ቀን ውስጥ ይሞታል፡፡ ይህ እርግጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ እምነት ስለሆነ አይተርፍም (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30-05-2005)፡፡

### 4.1.2.4. ድብደባ

ድብደባ በልዩ ልዩ ግጭቶች አማካኝነት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ድብደባ በጌዴኦ ብሄር አባላት ዘንድ ወንድ አስብሎ የሚያሸልምና አድናቆትን የሚያስገኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ሌላ ሰውን ቢያስቀይም ወይም ቂም መያያዝ ቢኖር ጊዜያቸውን ሰውተው የሚያስታርቁ ሽማግሌዎች እያሉ መደባደብን ምን አመጣው? ከሚለው የመነጨ ነው፡፡ በመሆኑም የትኛውም አይነት ድብደባ ቢኖርና ምንም ያህል ተደብዳቢው በዳይ ቢሆን ጉዳዩን ሽማግሌዎቹ ማየት የሚጀምሩት ተደብዳቢው ካሳ ከተቀበለና ተጎድቶም ከሆነ ደብዳቢው የደበደበውን ሰው እስኪያገግም ድረስ ከተንከባከበው በኋላ ነው፡፡

ነገር ግን የተደብዳቢው ቤተሰቦች ካሳ ተቀብለውም ሆነ ስነስርአቶች ተፈጽመው ቂሙ በቀላሉ ላይወጣላቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ጎንዶሮ[7] ይካሄዳል፡፡ በዚህም ይረገማል፡፡ በዚህ ስነስርአት ውስጥ በዳይንና ተበዳይ ሴሮ[8] ያካሄዳሉ፡፡ ሴሮውም በዳይና ተበዳይ ቂም አንስተው ቢጣሉ ምን አይነት ቅጣት እንደሚጠብቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ አንድ የጌዴኦ ብሄር አባል ሴሮ ጥሶ ድጋሚ ሊጣላ አይችልም ምክንያቱም ሴሮው ብቻውን ሳይሆን ከእርግማን ጋር የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ ድንገት ግን ምን ይመጣል በሚልና ቂሙ ብሶበት ቢጎዳዳ የሽማግሌዎቹ እርግማን ሴሮ የጣሰውን ለይቶ ይደርስበታል ተብሎ ያታመናል፡፡

### 4.1.3. ከባድ ግጭቶች

ከባድ ግጭት ከስሙ መረዳት እንደምንችለው ደረጃው ላቅ ያለና ከባድ የሆነ ስነልቦናዊ ማህበራዊና አኮኖሚያዊ ቀውስ ሊስከትል የሚችል ነው፡፡ በዚህ ስር ነፍስ ማጥፋት፣ የጎሳ ለጎሳ ግጭትና የብሄር ግጭት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በአጥፊውም ወገን ሆነ በበዳይ ወገን የሚያደርሱት አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት በጣም የከፋ ስለሚሆን የብሄሩ ባህል በሚያዘው መሰረት የተለያዩና ውስብስብ የሆኑ ስነስርአቶች መፈጸማቸውን ግድ ነው፡፡ እርቁም የሚፈጸመው እነዚህን ሰፊና ውስብስብ ደረጃዎች ካለፈ በኋላ ነው፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ደረጃዎች ካልተፈጸሙ በበዳይ ላይም ይሁን በተበዳይ ላይ ከሚያስከትሉት ስነልቦናዊ ቀውሶች በተጨማሪ በማህበረሰቡ አባላት ላይም አካላዊ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

---

[7] ጎንደሮ በአንድ ዋንጫ በዳይና ተበዳይ እንዲጠጡ የማድረግ ስነስርአት ነው፡፡
[8] ሴሮ ማለት ገደብ ወይም ደንብ ማለት ነው፡፡

#### 4.1.3.1. ግድያ

በጌዴኦ ብሄር ግድያ እንደ መነሻ ምክንያቱ ውጤቱም ይለያያል፡፡ በመሆኑም ነብስ ያጠፋ ሁሉ እንደ ወንጀለኛ አይታይም፡፡ ማለትም ነብስ ያጠፋበት ምክንያት በብሄር ለብሄር ግጭት ከሆነ፣ ብሄሩ እንዲገደል የወሰነበት ከሆነ፣ ብሄሩን የሚበጠብጥ የውስጥና የውጭ ጠላት ተብሎ የተፈረጀ ከሆነ ግድያ ወንጀል ሳይሆን ጀግንነትን የሚያመላክትና በማህበረሰቡ ዘንድ የክብር ደረጃን የሚያጎናጽፍ ይሆናል፡፡ ትልልቅ እንስሳትንና ጠላት ተብሎ የተፈረጀን አካል መግደል ያለውን ክብር አስመልክቶ ጥላሁን እብዶ "ጠላትን መግደል ጀግንነትንና የወኔ ምልአትን የሚያሳይ ነገር ነው፡፡ ይህን የሚያሳይ ነገር ይዞ መጥቶ ያስመሰክርና ቄጣላ የሚባል ነገር አለ እሱ ይካሄድለታል፡፡ ዝም ብሎ አይገባም፡፡ በደም ተረማምዶ ነው ጀግንነቱን አሳይቶ የሚገባው፡፡ ትልቅ እንስሳ ከሆነ ደግሞ ቆዳው ውጭ ላይ ይሰቀልና እስኪደርቅ ድረስ ይጨፈራል... " (ቃለመጠይቅ፣ጥላሁን እብዶ፣ 30-05-2005 )፡፡

በጌዴኦ ብሄር አንድ ሰው ብሄሩ እንዲገደል የወሰነበትን ሰውን ከገደለ በጣም ከባድ የሆነ ወንጀል እንደፈጸመ ስለሚታሰብ የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዱበታል፡፡ እርምጃዎች ከመወሰዳቸው በፊት ግን ጠንከር ያለ ባህላዊና ማህበረሰብ አቀፍ የሆነ የወንጀል ምርመራ ይካሄዳል፡፡ ይህ ወንጀል በጣም የከፋ በመሆኑም በገዳ ባሌ ስልጣን ደረጃዎች ውስጥ ከፍተኛ እርከን ላይ ባሉ ሰዎች የሚመረመር ይሆናል፡፡

ምርመራውም ምን አይነት አገዳደል ነው የተገደለው? ሆን ብሎ ተዘጋጅቶበት ነው ወይስ በድንገት(እለታዊ ብስጭት) በጭካኔ ነው፣ አልሞት ባይ ተጋዳይ ነው ወይስ ጥጋበኛ እንዲሁም ምን አነሳሳው ስካር ነው ወይስ ቂም? አላስቀምጥ ብሎት ነው ወይስ ራሱ ጠግቦ ነው? የሚለው ነገር በደንብ ይመረመራል፡፡ ከዛም ከሶስተኛው የእድሜ እርከን በላይ ያሉ የሃገር ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው መወሰድ ያለበትን እርምጃ ይወስናሉ፣ በዚህ ወቅትም የጨዋጀዎች ውሳኔ ይበልጥ ተሰሚነት አለው፡፡ ምክንያቱም ከረዥም እድሜ ልምዳቸው የሚያገኙት ተጨባጭ የውሳኔ ብቃታቸው የሚነሳ ነው፡፡ ስለዚህ የግድያውን ምክንያት የአገዳደሉን ሁኔታ የሚችና የገዳይ የቀደመ ባህሪን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

በግፍ የገደለ፣ በስነምግባሩም ጥሩ የማይባል ወዘተ. አይነት ከሆነ የሚወሰነው ውሳኔ የከፋ ነበር ማለትም ሞት ሊፈረድበት ይችላል፡፡ የአገዳደሉን ሁኔታ ስንመለከት ለገዳይ ቤተሰብ

ልጃችሁን ሸንጎው እንዲሞት ወስኖበታል ስለዚህ አንዳንድ ሁኔታዎችን አመቻቹ፣ ኑዛዜም ካለ ተቀበሉ፣ ምግብም አብሉት ሳይሞት ባደርግለት ብላችሁ የምታስቡትን ነገር አድርጉለት ተብሎ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወላጆቹ ልጆቻቸው እንዳይገደሉባቸው ሽማግሌዎቹን ይለምናሉ፡፡ አንዳንዴ ይቅርታ ሊደረግለት ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ከብዙ አቅጣጫ ታይቶ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ በሞት እንዲቀጣ የተወሰነው ይጸናል፡፡ የሞት ፍርዱ ተፈጻሚ የሚደረገውም በብሄሩ ውስጥ ካሉት ሰባት ወንድማማች ጎሳዎች በተውጣጡ ሰባት ወጣቶች ነው፡፡

እነዚህን ወጣቶች የሚመርጡት የአካባቢው ሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ አባገዳዎች(ጋዲቾዎች) በዚህ ጉዳይ እጃቸውን አያስገቡም እንዳላችሁት አድርጉ እኔ ከደሙ ንጹህ ነኝ በማለት ራሳቸውን ያርቃሉ፡፡ ምክንያቱም አባ ገዳዎች ከግድያ ነጻ ሰዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ከሰባቱም ጎሳዎች የተውጣጡ ወጣቶች በአንድነት ለዚሁ ተብሎ በተሰራ ከጫፉ አበጥ ባለ ዱላ በአንድነት ይመቱታል ሲመቱ አንዱ ወደኋላ ወይም ወደፊት መቅረት የለበትም ምክንያቱም ከኋላ የመታው ሰው ወይም ከፊት ቀድሞ የመታው ሰው ብቻውን እንደገደለው ስለሚቆጠር እና የቀደመ ወይም ወደ ኋላ የቀረ ሰው ጎሳ እንደ ነብሰ ገዳይ ሊቆጠር ስለሚችል ነው (ቃለመጠይቅ፣ ተካ ቦሩ፣ 26/05/2005 )፡፡

በሌላ በኩል አልሞትባይ ተጋዳይ ሆነው፣ መጠጥ አሳስኗቸው፣ ቂም ሳይይዙና በድንገት የሰው ነብስ ያጠፉ እንደሆነ ሊፈረድባቸው የሚችለው ቅጣት እንዲታረቁ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ በእርቅ ወቅት ካሳ የለም፡፡ ምክንያቱም ነብስ ውድ ስለሆነች ወይም የነብስ ባለቤት አምላክ ስለሆነ በቀሉንም ሆነ ካሳውን ራሱ ይቀበል እንጅ የሟች ቤተሰብ ልጃቸውን ህይወት የሚተካም ነገር አያገኙም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ነገር ግን ሰውየው ከጥፋተኝነት ስሜቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ነጻ የሚሆንበት የመንጻት ስነስርአት እና ከሟች ቤተሰቦች ጋር የጎሪጥ እንዳይተያዩና ከበቀል ሞት ስጋት ነጻ እንዲሆን እርቅ ይፈጽማል፡፡ ይህም በገዳይ በኩል ሲሆን በሟች ተቆርቋሪዎችና ቤተዘመዶች ዘንድ ልጃችን ሞቶ እሱ በሰላም ይኖራል የሚል ብሽቀት እንዳይኖርና ሌላ የሚያገረሽ የበቀል ስሜት እንዳይኖር ገዳዩን ከተለያዩ ማህበረ ባህላዊ መብቶቹና ከዴሞክራሲያዊ መብቶቹ እንዲታገድ ይደረጋል፡፡

ማለትም በገዳ ስርአት የባሌ የስልጣን ደረጃዎች ውስጥ በየትኛውም ቢሆን አይመረጥም፣ በሸንጎ ውስጥ ቅጠል አይነጠፍለትም፣ በሸንጎ ውስጥ የማህበር ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ

ቢኖር ሃሳብ መስጠትም ይሁን ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ በቤተ ዘመድ ቅቤ አይቀባም[9] ራሱም ቢሆን ተደብቆ ካልሆነ በስተቀር ቅቤ አይቀባም፡፡ በትልልቅ ልመናዎች ማለትም ድርቅ ሲመጣ ጦርነትና ያልተፈለገ ክስተት ሲፈጠር እሱ እንደ አንድ የብሄሩ አባል ሄዶ በጸሎት አይሳተፍም፡፡ ሲሞት የሚቀብሩት ሶስት ዘመዶቹ ብቻ ናቸው እንጅ ቤተ ዘመድ ተላቅሶ በደመቀ ስነስርአት አይቀበርም የሚሉት ውሳኔዎች ይሰጡበታል፡፡ ስለዚህ የሟች ቤተሰቦች የልጃቸውን ገዳይ ማህበሩ ስለሚበቀልላቸው ይተውታል፡፡ ይህ አሁንም ድረስ ያለ የማህበረሰቡ ወግና ልማድ ነው፡፡ እንደሆነ የቃለመጠይቅና የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ነግረውኛል፡፡ የሞት ፍርድ ግን አሁን የለም፤ ምክንያቱም ሰው የገደለ ሰው ወዲያው በፖሊሶች ተይዞ በዘመናዊው የፍትህ ተቋም ውሳኔ ያገኛል፡፡ እርቅም የሚፈጸመው ከፍርድ ውሳኔ በኋላ ነው፡፡

### 4.1.3.2. የጎሳ ግጭት

የጌዴኦ ብሄር ሰባት ጎሳዎች አሉት፡፡ እነዚህ ጎሳዎች የአንድ እናትና አባት ልጆች እንደሆኑ እና በዘር ግንድ አንድ አይነት እንደሆኑ የተለያዩ አፈታሪኮች ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም ከተነሱበት የጌዴኦ ብሄር መነሻ ማለትም ከኦዳያኣው ላይም ስለ አንድነታቸውና ወደፊትም ስለሚኖሩበት ጥልቅ መተሳሰብና መዋደድም ሰባት ድንጋዮችን ተክለው ተማምለዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ቢጣስ መሃላ ተጣሰ ነውና አይጣሉም፡፡ ቡድን ፈጥረውም አይደባደቡም፡፡ ነገር ግን በታሪካዊ አጋጣሚዎች በጣም ውስን ለሆኑ ጊዜያት ተጣልተው ብዙ ነፍስ ሳይዋደቅ በእርቅ ደምድመውታል፡፡

በጌዴኦ ብሄር የጎሳ ግጭት የሚነሳው በቤተዘመድ እንጅ መሰረታዊ መነሻውን የኔ ጎሳ ይበልጣል የኔ ትልቅ ነው በሚል የማንነት ጥያቄ አይደለም፡፡ ይህን ለማለት መነሻቸውን ሲያስረዱም የሁሉም ጎሳ አባላት ራሳቸውን በብሄራቸው ውስጥ እንጅ በጎሳቸው ውስጥ አይመለከቱትም፡፡ በጎሳ መከፋፈሉ ሚስጥሩ ዝምድናን መሰረት ያደረገ ጋብቻ እንዳይፈጠር እንጅ ጌዴኦ ወንድምአማች ስለመሆኑም የየትኛውም ጎሳ አባላት ይስማማሉ፡ ፡ ነገር ግን በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች የተለያዩ ግጭቶች እንደተፈጠሩና በባህላዊ ሽምግልና መፍትሄ እንዳገኙ በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል (ቃለመጠይቅ፣ ተካ ቦሩ፣ 26/05/ 2005)፡፡

[9] በጌዴኦ ባህል ቅቤ የተለያዩ አይነት ባህላዊ ስርአቶች ሲፈጸም የሚቀርብ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ትዳር መያዙንም ሆነ ሚስቱን መፍታቱን በይፋ የሚያሳየው ቅቤን አብዝቶ በመቀባት ነው፡፡ እንዲት የጌዴኦ ሴትም ውበቷን የምትጠብቀው ቅቤ በመቀባት ሲሆን ማንኛውም የጌዴኦ ብሄር አባል ለእንግዶቹም ሆነ ለሚያከብራቸው ሰዎች ክብሩን የሚያሳያቸው ቅቤን አብዝቶ በመቅባት ነው፡፡

ከቃለመጠይቅ እንዳገኘሁት መረጃ በ1999 ዓም አደሞና ጉርሶ የተባሉ ጎሳዎች ተጣልተው ደምም ተፋሰዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ያልተለመደ ነገር በመሆኑ የጌዴኦ ገዳ ተቆጥተዋቸው የተጣሉበትም ምክንያት ሳይታወቅ ስለቀረ በዚው ታርቀዋል፡፡ ሲታረቁም የሞተ ሰው ስለሌለ ለተጎዱት በባህሉ መሰረት ካሳ ተከፍሎ ነው፡፡ በጎሳ ግጭት ወቅት ሰው ቢሞት ገዳይ የገደለው የራሱን ወገን ማለትም ከጥንት ወንድሙን አሁን ደግሞ አጎቱንና አገቡኙን በአጠቃላይ ደግሞ የብሄሩን አባል በመሆኑ ወንጀል እንጅ ጀግንነት አይደለም፡፡

በባህሉ መሰረት ደግሞ ሰው የገደለ የብሄሩ አባል እርቅና መንጻት ካልተፈጸመለት ወንጀሉ ለትውልድ የሚተላለፍ ሃጢያት ስለሚሆን ይቅርታ መጠየቅና መታረቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ በግርግር ውስጥ ሆኖ እንኳን ሳይታዎቅ ቢቀር ያለብዙ ድካም ሰውየው የአምላኩንም ሆነ የማህበሩን እርቅ በሃይቻዎችና በሀገር ሽማግሌዎች በኩል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በግድያ ግጭት አፈታት ስነስርአት ውስጥ አልፎ እንዲታረቅ ይደረጋል፡፡ ካልታወቀና ሰውየው ራሱ በዳይ ነኝ አስታርቁኝ ካላለ ነፍስ በማጥፋቱና ከደሙ ባለመንጻቱ ከሱ ጋር ሲበሉ ሰውነታቸው እንዳለ ነፍርቆ በቃ ቆሳስለው ስለሚታወቁ አስቀድሞ ቢታረቅ ስለሚሻለው ቤተዘመዱም አያስቀምጠውም ስለዚህ ይታረቃል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ጎሳ ለጎሳ መጋጨት አያስፈልግም ብለው ያምናሉ (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/ 05/ 2005) ፡፡

#### 4.1.3.3. የብሄር ግጭት

የብሄር ግጭት በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ከሚከሰቱት የግጭት አይነቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ግጭት ብዙ ጊዜ የሚከሰተው ከሚያጎራብቱት ሁለት ብሄሮች ማለትም ከሲዳማና ከጉጅ ጋር ነው፡፡ እነዚህ ብሄሮች በባህል በአስተዳደር ስርአትና በሌሎች ጉዳዮች ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች እርስ በራሳቸው ይጋጫሉ፡፡ ከሚጋጩበት ምክንያት ውስጥ ዋናው የድንበር መገፋፋት ነው፡፡ ይህ መገፋፋት ደግሞ እንደመነሻ ይሆንና ከባድ የሚባል ጦርነት ይጀመራል፡፡ በዚህ ጦርነት ውስጥ ጉዳዩ ከድንበር የሚዘልና ወደ ማንነትም የሚመጣ በመሆኑ ለጦርነት የበቃ የጌዴኦ ብሄር አባል ሁሉ የጦርነት እና የድል ማብሰሪያ ዜማውን እያንጎራጎረ ወደ አጎራባች ብሄሩ ይዘምትና የሚገለውን ገሎ የሚያቆስለውን አቁስሎ የሚማርከውን ማርኮ ይመለሳል፡፡ ወይም ድል ይደረጋል፡፡ ማሸነፉም ይሁን መሸነፉ በእርቅ ካልተቋጨ ዘላቂ ሰላም እንደማይመጣ ይታወቃልና ለእርቅና ድርድር ይቀርባል፡፡

እርቅ ለማካሄድም የፈለገው ወይም እርቅ እንዲወርድ የሚፈልገው ጌዴኦ ብሄር ከሆነ የሀገር ሽማግሌዎች፣ በሉባ ደረጃ የሚገኙት የባሌ ባለስልጣናት እና ሃዩዎች(የሃይማኖት አባቶች) በአንድ ላይ ይሆኑና ለአምላካቸው ጸሎት ያደርሳሉ፡፡ ጦርነቱ እንዲቆም ከህዝቡ ጋር ይለምናሉ፡፡ በዱሮ ገዜ ወደ አጎራባች ብሄሩ(ጥለኛቸው) አንዲት ሴት የሰላም መልክት አስይዘው ይልኩ ነበር፡፡ ይህች ሴት እስክትመለስ ይጠብቁና የተላከችው ሴት ያመጣችውን መልክት ይወያዩበታል፡፡

በግጭት አፈታት ሂደት ወቅት የሚያስፈልገው ስነ ስርአት እንደየባህሉ ይቀርብና በሁለቱም ብሄሮች አባገዳና በካቢኔው ተመርቆ እርቅ ይካሄዳል፡፡ እርቁ ሲፈጸምም የሁለቱንም ብሄሮች ስምምነት የሚጠይቅ በመሆኑ የሁለቱም ብሄሮች አባገዳዎች ምርቃትና የማስታረቅ ስነስርአቱን ሊመሩ ይገባል፡፡ አሁን አሁን ግን ግጭት ሲፈጠር መንግስት እጁን ማስገባቱ ስለማይቀር የሁለቱን ብሄሮች የሰላም መልክት የሚያደርሰው መንግስት ነው፡፡ ነገር ግን ግጭቶች በመንግስት ጣልቃ ገብነት ስለማይበርዱ[10] የሚካሄዱትን ባህላዊ ስነ ስርአቶች በሙሉ መንግስት ከዳር ሆኖ ይከታተላል፡፡ በአንጻሩ የመንግስት የሃይል እርምጃም ሆነ ጣልቃ ገብነት የብሄሮችን የእርስ በእርስ ግጭት የበለጠ የሚያሰፋና እልቂቱንም የሚጨምር ነው፡፡

## 4.2. የጌዴኦ ብሄር አስተዳደራዊ ሁኔታ

የጌዴኦ ብሄር አስተዳደራዊ ሁኔታዎች በሚለው ርእስ ስር የብሄሩን አስተዳደራዊ ሁኔታዎች አሳያለሁ፡፡ በዚህም ቀደምት ናቸው ተብሎ በብሄሩ አባላት የሚነገርላቸው የአስተዳደር ክፍሎች ማለትም የአኮማኖየ ስርወ መንግስትና የጎሳሎ አስተዳደር እንዲሁም አሁን በማስተዳደር ላይ የሚገኘው የባሌ የአስተዳደር የሚቃኝበት ነው፡፡

### 4.2.1. የአኮማኖየና የጎሳሎ ስርአት

የጌዴኦ ብሄር ባህላዊ አስተዳደር ስርአትን የሚያስተዳድሩ ሶስት ስርወ መንግስታት እንደነበሩ የብሄሩ አባላት በአፈታሪክ ያስረዳሉ፡፡ በዚህም መሰረት 'የአኮማኖየ' ስርወ መንግስት(እማዊ ስርአት)፣ የጎሳሎ የአስተዳደር ስርአት እና የባሌ ስርአት የተባሉትን ስርወ-መንግስታት በቅደም ተከተል እናገኛለን፡፡ የአኮማኖየ ስርአት እማዊነት ይስተዋልበት የነበረና የሴቶችን የበላይነት ያሳየ ስርአት ሲሆን ይመራ የነበረውም

[10] በጌዴኦ ብሄር ውስጥም ሆነ ብሄሩ ከሌሎች ብሄሮች ጋር በተለያየ ጊዜ የሚፈጠሩትን ግጭቶች ለመፍታት በመንግስታዊ የጸጥታ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ሙከራና የሃይል እርምጃ ተወስዶ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ይህ የማያዋጣ እንደነበር እንዲያውም ግጭቶችን የበለጠ የሚያስፋፋና የበለጠ ቀውስ ውስጥ የሚጨምር ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት ጉዳዮችን እያስፈጸመ በጌዴኦ ባህላዊ አስተዳደር አማካኝነት ለመፍታት መሞከር ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ኮማንደር አብርሀም)

በንግስት(በሴት መሪ) ነበር፡፡ በዚህ ስርአት ሴቶች አስተዳደራዊ የሆነውንና የአደባባዩን ስራ ሲሰሩ ወንዶች ደግሞ የቤት ውስጥ ስራዎችን እንዲሰሩ ይገደዱ ነበር፡፡ በ'አኮማናየ' ስርአት የሚወለዱ ልጆች ስም የሚጠራው በእናታቸው ስም እንደነበረ (የጌዴኦ ብሄር ታሪክ፣ 2000፣ 19) ያሳያል፡፡ የንግስቷ አስተዳደር ለወንዶች በጣም አስቸጋሪ እንደነበር ሲገልጹም

> " ንግስቷ በጣም አስቸጋሪ ከመሆኗ የተነሳ ወንዶችን የምታስቸግርበትን ዘዴ ስትፈጥር ነው የምታድረው፡፡ በዚህም መሰረት ወንዶችን አየር ላይ የሰንበሌጥ ቤት ስሩልኝ፣ በአለም ላይ የሌለ ምግብ ፈጥራችሁ መግቡኝ፣ ብቻ የማትለው የላትም ነበር... አንድ ቀን እንደልማዷ ወንዶችን ሰብስባ ባለፈው ጊዜ ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ አድርጋችሁ በሰንበሌጥ ቤት ስሩልኝ ብያችሁ ነበር ለምን እስካሁን አልሰራችሁልኝም አሁንም በአጭር ጊዜ ሰርታችሁ አሳዩኝ ብላ ቀን ቀጥራ ሰደደቻቸው፡፡ እናም ወንዶቹ ሲጨነቁና እንዴት እንደሚሰሩ ሲያስቡ የተባለው ቀን በመድረሱ ተደናግጠው ተሰብስበው ምን እናድርግ ሲባባሉ አንድ አፈጣጠሩ ድንክ የነበረ ብልህ ሰው ከመካከላቸው ተነሳና እንግዲህ ይህ የማይቻል ነገር ነው፡፡ ማድረግ ያለብን በጨለማ በጨለማ እየተሰባሰብን ጥልቅ ጉድጓድ እንቆፍርና በሰንበሌት እንሸፍነው ከዛም ከላዩ ላይ ወንበር እናስቀምጥ፡፡ የተባለው ቀን ደርሶ ንግስቷ የታል ቤቱ ስትል ቤቱ የሚታይሽ እዛ ወንበር ላይ ስትሆኚ ነው እንላትና ቤቱን ልታይ ወንበር ላይ ስትወጣ ገደል ትገባለች፡፡ ከዛም እንዳትተርፍ ቀጥቅጠን መግደል ነው የሚል ሃሳብ አቅርቦ ሁሉም ወንዶች በዚህ ተስማምተው ንግስቷን ገደሏት፡፡ ንግስቷም ልትሞት ስትል የጌዴኦ ሴት እንግዲህ ጠንካራ ሁኚ ቀሚስሽንም ስትለብሽ ወደታች መዝርጭ ብላ ተናግራ ነበር፡፡ አሁንም ድረስ ለምን እንደተናገረች ባያውቁትም ቀሚስ ሲለብሱ ወደታች ይመዠርጣሉ..." (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ዳንኤል፣ 10/ 06/ 2005)፡፡

ከትረካው እንደምንረዳው የብሄሩ አባላት ወንዶች በሁኔታው ስለተማረሩ በውስጥ ለውስጥ ሴራ የአኮማናዮዋን ንግስት በመግደል እማዊ ስርአቱ እንዲያከትም ማድረጋቸውን ነው፡፡

የአኮማናየን ስርአት እንዳበቃ ወደስልጣን የወጣው የጎሳሎ አስተዳደር ነው፡፡ የጎሳሎ ስርአት ስያሜው የጎሳ አስተዳደር ከሚለው የሚነሳ ነው፡፡ ይህ አስተዳደር ፍጹማዊ የሆነ አንድ የጎሳ መሪን በመሾም የሚካሄድ በአንድ ሰው ብቻ የሚመራ ስርአት ነው፡፡ የጎሳሎው ዋና ዋና ተግባራት አምላክን የመለመን፣ ህዝቡ ለአደንና ለጦርነት ሲወጣ ምርቃት መስጠት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የዚህ ስርአት ዋናዋና እሴቶች የሚባሉት የወንዶችን የበላይነት ማረጋገጥ ማለትም የተወለዱ ልጆች በአባት እንዲጠሩ ማድረግና ይህንን መከታተል፣ ንብረትን በአባወራ ስም ማድረግ፣ ሴቶች ወደ ሸንጎ እንዳይወጡ መከልከል፣ ማናቸውንም እምነታዊ ባህላዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በአምባገነንነት ማስተዳደር፣ ሶንጎ ማደራጀት፣ ህግ መደንገግና የዳኝነት ስርአት መዘርጋት ናቸው፡፡

የጎሳሎ ስርአት ግን ብዙም ሳይቆይ አምባገነንነትና ማን አለብኝነት እየተስፋፋበት ሄደ፡፡ በዚህም የተነሳ በአካባቢው የእሴት መጥፋት፣ ከባህልና ከማህበራዊው ደንብ መውጣት ወንጀለኝነት መስፋፋት የመሳሰሉት መከሰት ጀመሩ፡፡ ህዝቡም ትእዛዛትን መጣስና ማጉረምረም ጀመረ፡፡ በዚህ ወቅት ነው እንግዲህ የራሱ የሆነ አስተምሮ ይዞ የተነሳ አንድ የጌዴኦ ብሄር አባል አዲስ የሆነ የፖለቲካና የሸንጎ አስተዳደር በድብቅ ማስተማር የጀመረው፡፡ ይሔውም አንድ ግለሰብ የራሱን አመለካከት ማንም በሌለበት ማስተማር ነው፡፡ በመጨረሻም የአካባቢው ነዋሪዎች ግለሰቡ ብቻውን የሚያወራውና ህዝብ እንደተሰበሰበ አስመስሎ ፍትህ የሚሰጥበትን መንገድ ስለወደዱት በጋራ በመሆን የጎሳሎ አስተዳደሪውን በመግደል አዲሱን የባሌ ስርአት እንዲጀመር አድርገዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/ 05/ 2005)፡፡

### 4.2.2. የባሌ ስርአት

በጌዴኦ ብሄር የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ የጎሳሎ ስርአትን በመጣል ወደ ስልጣን የመጣው ባሌ ሰርአት ነው፡፡ ባሌ ማለት ማንኛውም የጌዴኦ ብሄር አባል የሆነ ወንድ ልጅ በእድሜው የሽግግር እርከኖችን የሚያልፍበት ነው፡፡ እያንዳንዱ እድገት ደረጃ ስምንት ስምንት አመት የሚፈጅ ዘጠኝ ደረጃ ያለው ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የባሌ ኡደት 72 አመታትን ይወስዳል ማለት ነው፡፡ የጌዴኦ ብሄር አባል የሆነ ሁሉ ሁሉንም የእድገት ሽግግር ላያልፍ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የጌዴኦ ወንድ ልጅ ባሌውን የሚረከብ ከአባቱ በመሆኑ ነው (የጌዴኦ ህዝብ ታሪክ፣ 2000፣ 22)፡፡ በዚህ ስርአት የጌዴኦ ወንድ በተለያየ የእድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ የሚያልፋቸው ደረጃዎች ቃዳዶ፣ ሲዳ፣ ሉማሳ፣ ራባ፣ ሉባ፣ ዩባ፣ ጉዱሮ፣ ዳዶ፣ ጫዋጂ ናቸው፡፡

የጌዴኦ ገዳ ስርአት አወቃቀርም ሆነ ምርጫ ከባሌ ስርአት የሚነሳ ነው፡፡ ይሄውም ከቃዳዶ እስከ ራባ ድረስ ባሉት የእድገት ደረጃዎች ወታደራዊ እምነታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ሲለማመዱ ይቆያሉ፡፡ በአምስተኛው ደረጃ ማለትም በሉባ የእድገት ደረጃ ብቁ ሆኖ የተገኘ ሰው ስልጣን ተረክቦ ማስተዳደር ይጀምራል፡፡ ከሉባ ቀጥሎ ባለው ዩባ ደረጃ የሉባነት ስልጣኑን በቅርቡ ያስረከበና በስልጣን ላይ ላሉት አካላት የማማከር ተግባር የሚፈጽም ነው፡፡ በተጨማሪም ስለ ገዳ ስርአት አሿሿም የማስተማርና አራተኛው ደረጃ ላይ ያሉትን ወደ አምስተኛው ደረጃ ለመሸጋገር እንዲችሉ እርዳታ የሚያደርግ ነው፡፡ ሰባተኛው የእድገት ደረጃ ጉዱሮ ሲሆን በዚህ ደረጃ መለስተኛ የማማከር አገልግሎትና በአገር ሽማግሌነት አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፡፡ ስምንተኛው ደረጃ ስልጣንን

ለማስረከብ የሚዘጋጅና ምርቃት የሚሰጥ አካል ነው፡፡ የመጨረሻው የስልጣን ደረጃ ጫዋጀ ሲሆን ምንም አይነት ሀላፊነት የሌለውና ሁሉንም የእድገት ደረጃዎች ጨርሶ ወደ ህጻንነት ደረጃ የተመለሰ ነው፡፡

በዚህ የደረጃ ክፍፍል ውስጥ በጌዴኦ ብሄር ግጭት አፈታት ወቅት ከመጀመሪያው እስከ አራተኛው ደረጃ ያሉት ሚናቸው ብዙ ጊዜ የመታዘብና የመማር ነው፡፡ ከሉባ እስከ ዳዶ ያሉት አራት ደረጃዎች ግን ግጭት የመፍታት ስራን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያከናውኑ ናቸው፡፡

### የጌዴኦ ባሌ መዋቅር

የጌዴኦ ዞን በዘመናዊ መንገድ በ6 ያህል ወረዳዎች ይከፈል እንጅ በባህላዊ መንገድ በሶስት ባህላዊ የአስተዳደር ክልሎች (ሮጋዎች) ተከፋፍሎ ይገኛል፡፡ የጌዴኦ ብሄር ሶስቱንም የአስተዳደራዊ ክልሎች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሃማኖታዊ ስርአት በማእከላዊነት የሚመራው የያኣ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡ አብዛኞቹ የያኣ ጉባኤ አባላት በሉባ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ባለስልጣናትና የሃይማኖት አባቶች ናቸው፡፡ የዚህ ጉባኤ መሪ አባ ገዳ ወይም ጋዲቻ ነው፡፡ በምክትልነትም የጦር ጠቅላይ አዛዥና አፈጉባኤ(ቦባሳ) የያኣውን ጉባኤ ይመሩታል፡፡ ከነሱ ጋርም ወዮዎች (ከሰባቱም ጎሳዎች የተውጣጡ የሃይማኖት አባቶች) በጉባኤው ውስጥ ቅጠል የሚነጠፍላቸው (ወንበር ያላቸው) ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ባለስልጣናት ተጠሪነታቸው ለህዝብ ሲሆን ምንም አይነት ጥፋት የማይሰሩና በሰማይ አምላክ የተመረጡ እንደሆኑ ይታሰባል፡፡

ከላይ ያየናቸው የአየር ንብረትን መሰረት አድርገው የተከፋፈሉት ሮጋዎችም የደጋው ክልል አስተዳደር (የሱቦ ሮጋ 'Suubboo roga')፣ የቆላማው አየር ንብረት ክልል (የሪቀታ ሮጋ 'Riqataa roga')ና ወይና ደጋማው የአየር ንብረት ክልል (የዲበታ ሮጋ 'Dhibataa roga') ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ሮጋዎች በገዳ የሹመት ስርአት የሚመረጡ፣ በገዳ ስርአት አስተዳደር መሰረት የሚመሩ፣ ተመሳሳይ መዋቅር ያላቸው ባህላዊ አስተዳዳሮች ናቸው፡፡ ይህ አስተዳደር ስርአት በያኣ ጉባኤ የሚመራ ነው፡፡

የያኣ ጉባኤ መሪ በሆነው አባገዳ በኩል ስልጣናቸው የሚጸድቅ የጌዴኦ ብሄር ባህላዊ ካቢኔዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው ጀእላባ (jalaaba) ሲሆን የአባ ገዳ

ምክትል በመሆን ብሄሩን የሚያስተዳደር ነው፡፡ ሁለተኛው አባሮጋ (abbaroga) የሶስቱ የአስተዳደር ክልሎች(ሮጋዎች) መሪ ሲሆን በየክልሎቹ የሚገኝና ከአባ ገዳውና ከጃእላባው ትእዛዛትን እየተቀበለ የሚመራና ትእዛዛትን የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ሶስተኛው የአስተዳደር መዋቅር ጃልቀባ(jalkaba) ሲሆን የአባሮጋዎች ምክትል በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ የስልጣን አካል ከአባሮጋው የሚተላለፈውን ትእዛዝ የሚፈጽምና የሚያሥፈጽም ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የባሌ ባለስልጣናት ደግሞ ሁላቲ ሃይቻዎች(hulati hayicha) ናቸው፡፡ እነዚህ ሀይቻዎች በጌዴኦ ብሄር ውስጥ የሚገኙት ሰባት ጎሳዎችን የሚወክሉና በየሶንጎው የሚገኙ ናቸው፡፡ አምስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የጌዴኦ ብሄር አስተዳደራዊ መዋቅር ባጤቲ ሃይቻ(baxxeti hayicha) ነው፡፡ በባጤቲ ሀይቻ ደረጃ የሚገኙት የብሄሩ ባለስልጣናት ህዝቡን በቅርበት በየሶንጎው የሚያስተዳድሩና ግጭቶችን የሚፈቱ ናቸው፡፡ ስድስተኞቹ የጌዴኦ ብሄር ባለስልጣናት ዳባሌ(dabbale) የሚባለው የአስተዳደር ክፍል ነው፡፡ ይህ የአስተዳደር ደረጃ ከባጤቲ ሀይቻ ትእዛዛትን ሊቀበል የሚችል የአስተዳደር ክፍል ነው፡፡ በጌዴኦ ብሄር የአስተዳደር መዋቅር መሰረት የመጨረሻው የአስተዳደር መዋቅር ሙራ(murra) ነው፡፡ ሙራ ስራው አስተዳደሩንና ህዝቡን በድልድይነት ማገናኘት ሲሆን አላማውም አስተዳደራዊና ባህላዊ ትእዛዛትንከመሪዎቹ ወደ ህዝቡ ማድረስ ነው፡፡

## 4.3. የጌዴኦ ብሄር ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅሮች

በዚህ ርእስ ስር በጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስነስርአት ወቅት ተሳታፊ የሚሆኑ የብሄሩ አባላትን ማንነትና በብሄሩ ውስጥ የሚፈጠሩ የተለያዩ አይነት ግጭቶች ሲፈጠሩ እስኪፈቱ የሚሄዱበትን ማህበረ ባህላዊ መዋቅሮች እተነትናለሁ፡፡ በመሆኑም በሽምግልናው ስርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት እነማን እነማን ናቸው? በምን መንገድና መስፈርት ነው የሚመረጡት? በዚህ አገልግሎት ላይ የሚቆዩበት ዘመን ገደብ አለው? የሚሉትን ጥያቄዎች የምመልስበት ነው፡፡

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ግጭት ሲፈጠር እንደ ግጭቶቹ አይነት የሚፈቱት ሰዎች ማህበራዊ ደረጃም የተለያየ ነው፡፡ በብሄሩ ውስጥ ቀላል ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱት በቤተሰብ ደረጃ ሲሆን መካከለኛና ከባድ ግጭት ደግሞ በባሌ ስርአት እርከን መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ግጭት መፍቻነት የሚያገለግለው የቤተሰብ ጉባኤ ሁለተኛው የአካባቢ ሽማግሌዎች ሶስተኛው ሶንጎ ሲሆን ይህም ባለሶስት ደረጃ ነው፡፡ ይሄውም የአካባቢ ሶንጎ ፣ማህበራዊ ሶንጎ ና ጠቅላይ ሶንጎ ነው፡፡

### 4.3.1. የቤተሰብ ጉባኤ

ይህ ጉባኤ በቤተሰብ መካከል የሚቋቋም ሲሆን የሚፈታውም የቤተሰብ ችግሮችን ብቻ ነው፡፡ የቤተሰብ ጉባኤ የሚመራው በአባወራው ነው፡፡ በጌዴኦ ብሄር ባህል መሰረት አንድ የጌዴኦ ብሄር አባል የሆነ ባል በቤተሰቡ ላይ በርከት ያሉ ስልጣኖች አሉት፡፡ ስለዚህ ተሰሚነቱም ከፍ ስለሚል በቤተሰቡ ውስጥ የሚፈጠርን ግጭት ሁሉ የመቆጣጠር እና የመፍተታት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ምን አልባት ግጭቱ በባልና በሌሎች የቤተሰብ አባላት ከሆነና ባልየው ውሳኔ ለመስጠት የማይችልበት ምክንያት ሆነው የሚቀርቡ ጉዳዮች ለምሳሌ የአካል ጉዳተኛ ማለትም የመስማትና የመናገር ችግሮች ካሉበት፣ የአእምሮ ዝግመት ካለበት፣ ተናግሮ የማሳመን ችግር ያለበት ከሆነ፣ ታሞ የአልጋ ቁራኛ ከሆነ ወዘተ. ሃላፊነቱ ከቤቱ ሊወጣ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት በሰፈር የሀገር ሽማግሌዎች እልፍ ካለም እንደ ጉዳዩ ክብደት እስከላይኛው የስልጣን ደረጃ ሊሄድ ይችላል፡፡

### 4.3.2. የአካባቢ ሽማግሌዎች


በጌዴኦ ብሄር የሚገኙት የአካባቢ ሽማግሌዎች ቀላል የሚባሉ ግጭቶችን ይፈታሉ፡፡ በአካባቢው ሊኖሩ ከሚችሉት ግጭቶች ውጭ የመፍታት ስልጣን የላቸውም፡፡ ግጭት መፍታትም መሰረታዊ ስራቸው አይደለም፡፡ ስለዚህ ባለጉዳዮች ግጭቶችን ለመፍታት ሲያስቡ በኔ ጉዳይ ማን ቢገኝ ጥሩ ነው? ለኔ የሚጠቅመኝን ሀሳብ የሚመክረኝ፣ በደሌ እንደኔ ሊሰማውና በዳየን አፉን ሊያስይዝልኝ የሚችለው ሰው ማን ሊሆን ይችላል? የሚለውን በማሰብ የሚካሄድ የግለሰብ ምርጫን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም አስታዋይነት፣ ጥሩ አርአያ ሊሆን የሚችል ሰው መሆንና በእድሜ ትልቅ መሆን ለአካባቢያዊ ግጭት ፈችነት መመረጥ መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው (ቃለመጠይቅ፣ ሃይቻ ጀቦ ኩራ፣ 02-06-2005)፡፡

### 4.3.3. የተለያዩ ሶንጎዎች

የጌዴኦ ብሄር ሀይማኖታዊ አስተዳደራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚፈጽምበት የራሱ የሆነ ቦታ አለው፡፡ ይህ ቦታ ሶንጎ በመባል ይጠራል፡፡ ሶንጎ የሚባለው በሰፊ ግቢና በደን የተከበበ ቅዱስ ቦታ ሲሆን በሁሉም የብሄረሰቡ አካባቢዎች ይገኛል፡፡ ትልቆቹ ሶንጎዎች ኦዳ-ያአና በላያአ በመባል የሚጠሩት ናቸው፡፡ በጌዴኦ ብሄር ከ500 በላይ ሶንጎዎች ሊገኙ እንደሚችሉ (የጌዴኦ ብሄር ታሪክ፣ 2000፣ 43) ያስረዳል፡፡

ይህ ቅዱስ ስፍራ ሃጢያት የማይሰራበትና የጌዴኦ ብሄር አባል ስለማንነቱ፣ ስለባህሉ፣ ስለእሴቱ፣ ስለትውፊቱ ወዘተ. ትምህርት የሚያገኝበት ነው፡፡ የብሄሩ አባል ለቀጣዩ የእድገት እና የሹመት ደረጃ እንዲሸጋገርም ልዩ ልዩ ምዘና የሚካሄድበት የጌዴኦ ማንነት እምብርት ነውም ሊባል ይችላል፡፡ ሶንጎ ሰፋ ባለ ቦታ ላይ የሚሰራ ጎጆ ቤት ሲሆን ሁለት በር ያለው ነው፡፡ በሶንጎ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ ትእምርታዊነትና ባህላዊ ፋይዳ ያላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንድ ትልቅ ዛፍ፣ የጦርና ብትር ማስቀመጫ ባላ እንጨት፣ የገበጣ ጉድጓዶች እና ከሶንጎው ጀርባ የጌዴኦን ልምላሜ የሚያሳዩ ዛፎችና ልዩልዩ ዕጽዋቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች አንድን ሶንጎ ሶንጎ የሚያስብሉ ሲሆኑ ሁሉም የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው፡፡

ይሄውም በሶንጎው ቅጥር ግቢ የሚገኘው ትልቅ ዛፍ የጌዴኦን ብሄር ትልቅነት፣ ጌዴኦ ለግሉ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድ በማሰብ ጭምር ከመቶ አመት በላይ የሚቆይ ዛፍ የሚተክል መሆኑን፣ እንዲሁም በተለየዩ ማህበራዊ መስተጋብሮች ወቅት ሰዎችን ከፀሃይ የሚከላከልም ነው፡፡ የጦርና የበትር ማስቀመጫው ደግሞ ወደ ጸሎትና ፍርድ ሲኬድ እንዲሁም ወደ ሶንጎው ሲገባ ፀረሰላም መሳሪያዎች ስለማይገቡ የሚቀመጡበት ስፍራ ነው፡፡ የገበጣ ጉድጓዶቹ ደግሞ የሽማግሌዎቹ የመዝናኛና የዘመን መቁጠሪያዎች ናቸው፡፡ ከሶንጎው ጀርባ ያለው ደን ደግሞ የአካባቢውን ልምላሜ እና የብሄሩን የወደፊት ተስፋ ሚያሳይ ነው (ጥላሁን እብዶ ፣ቃለመጠይቅ፣ 30/05/2005)፡፡



**ፎቶ ግራፍ ሶስት፡- የየገደብ አጠቃላይ ሶንጎ ከፊል ገጽታ**

#### 4.3.3.1. የአካባቢ ሶንጎዎች

ሶንጎ የተባለው የግጭት መፍቻ፣ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በየመንደሩ ይገኛል፡፡ በተቋሙ ውስጥ ስልጣን ያላቸውን አካላት ባጣቲ ሃይቻና ሁላቲ ሀይቻ (የሶንጎ አስተዳዳሪ)፣ ሙራ (ተላላኪ)፣ ሃዩ (አስጸላይዎች) እና ጸሀፊዎች ናቸው፡፡ በዚህ ንኡስ ርእስ ስርም ስለነዚህ ሰዎች ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ እና ማህበረሰቡ ስለሚሰጣቸው ቦታ የሚብራራበት ነው፡፡

ተቋሙ የሚመራው በሃይቻ ነው፡፡ እነዚህን የስራ ድርሻዎች የሚሰጡት የማህበረሰቡ ክፍሎች በጌዴኦ የባሌ ስልጣን ደረጃዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ እነኝህ ማእረጎች የሚገኙት ከቀደሙት ባለስልጣናት በዘር ነው፡፡ አሿሿሙም ከዚህ ቀደም በአባቱ ባሌ ባለስልጣን የነበረ ሰው ስምንት አመት ካስተዳደረ በኋላ ከልጆቹ መሃል በስነ ምግባሩም ሆነ በባህል እውቀቱ የተሻለ ነው ያለውን መርቆ ለሸንጎው በመስጠት ነው፡፡ ይህ ከዚህ ቀደም ባለስልጣን በሆነው አባቱ ተመርቆ ለሹመት የቀረበ ሰው ለተከታታይ ስምንት አመታት ሸንጎውን በሙሉ ሃላፊነት ያገለግላል፡፡ እንደ አጋጣሚ ግን ባለስልጣኑ ለሸንጎው የሚሆነውን ልጅ መርቆ ሳይሰጥ በሞት ቢለይ በተለየ መንገድ ምርጫው ይካሄዳል፡፡ ይህ ምርጫ ግን ማህበረሰቡ በፈለገው መንገድ ሳይሆን በፈጣሪ ፈቃድ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በባለስልጣንነት የተመረጠ ሰው ህዝቡን ሊበድልና ፍርድ ሊያጓድል አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሚሾመውም ወይም ስልጣኑ የሚሰጠው በአባቱ ባሌ መሰረት ይሁን እንጅ በፈጣሪ ፈቃድ መሆኑ ስለሚታመን ነው፡፡ ይሄም የፈጣሪን ስልጣን ያላግባብ መጠቀም በመጀመሪያ በሱና በቤተሰቡ ካለፈም በዘር ማንዘሩ ላይ የአምላክ ቁጣ የሚያስከትል በመሆኑ ነው፡፡

አባት ስልጣኑን ሲያወርስ ምን አልባት የአባትየው ፍቅር ጨዋ ላልሆነ ሰው ቢሆንና እሱን ወደ ስልጣን የማምጣት ስሜት ቢያድርበት ወይም ደግሞ ህዝቡ የወደደው ሌላ ሰው ኖሮ ለሹመት ቢመረጥ በማህበረሰቡ ላይም ሆነ በተሿሚው ሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚከሰት ያምናሉ፡፡ ከጥንት እስከዛሬ ባለስልጣናትና የሃይማኖት አባቶች ሃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡ እንዲሆኑ ያስገድዳቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ማህበረሰቡ ደግሞ መሪዎቹ ከፈጣሪ የተመረጡ ናቸው ብሎ ማመኑ በአስተዳደራቸው እንዲተማመን ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተለይም የግጭት አፈታትና የፍትህ ስርአት በቀላሉ ለመድልኦና ለኢፍትሀዊነት የሚያጋለጥ ነው፡፡ መሪዎችን መድሎ እንዳይፈጽሙ ተገልጋዮችም

እንዳይጠራጠሩ የመሪዎቹ ከአምላክ መመረጥ ትረካ ወሳኝ ስነልቦናዊ ሚና አለው፡፡ ይህም የጌዴኦን ሶንጎ ተአማኒነቱን እንደያዘ እንዲቀጥል ያደረገ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

የዚህ ተቋም በለስልጣናትና አስጸላዮች የስራ ድርሻቸውን ያገኙት ከቤተሰባቸው ውስጥ አስተዋይ በመሆን፣ ባህሉን ጠንቅቆ በማወቅ በዘር ሀረግ (የአባታቸውን ባሌ በመቀበል) ነው፡፡ ሹመታቸውን ይዘው መቆየት የሚችሉት እስከ ስምንት አመት ድረስ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም የባሌ ሹመት መቆየት የሚችለው ለስምንት አመት ብቻ በመሆኑ ነው (ቃለመጠይቅ፣ ጀቦ ኩራ፣ 02/06/2005)፡፡

በጌዴኦ ብሄር ሸንጎ ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶች ቀርበው ይታያሉ፡፡ ለሁሉም አይነት ግጭቶች አስፈላጊ የሆነ ያሉትንና ሽማግሌዎቹ ይሁን ያሉትን ውሳኔ ይፈጽማሉ፡፡ በዚህ ሸንጎ ከአካባቢ የሀገር ሽማግሌዎች የሚላኩ መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ግጭቶችም ይፈታሉ፡፡ በአንጻሩ በእነዚህ ሸንጎዎች ላይፈቱ የሚችሉ የግጭት አይነቶች ይኖራሉ ማለትም ባለጉዳዮቹ የሸንጎው ባለስልጣናት ተገቢ ውሳኔ አልሰጡኝም ብለው ካሰቡ ወደ ሮጋ ወይም ወደ ጠቅላላ ሸንጎ ይግባኝ ሊሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ማናቸውንም አይነት ወንጀሎች ማስረጃ እስከሌላቸው ድረስ በሙሉ ስልጣን ይዳኛሉ፡፡

### 4.3.3.2. የሮጋ ሶንጎዎች

የዚህ ስልጣን ባለቤቶች በጠቅላላ ሶንጎዎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የሚያስተዳድሩትም አንድ የአስተዳደር ክልልን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የስልጣን ደረጃ በብሄሩ ውስጥ ሶስት ሮጋዎች ስላሉ በየስምንት አመቱ የሚመረጡ ሶስት ሶስት ሰዎች ብቻ ናቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ የስልጣን ደረጃ የሚገኙት ሰዎች የሚፈቱት የግጭት አይነት ከየሶንጎዎች በይግባኝ የሚላኩትን አንዳንድ ወንጀሎችና ደረጃቸው ላቅ ያለ የድብደባና የግድያ ወንጀሎችን ነው፡፡

በዚህ ደረጃ የሚገኙ የባሌ ባለስልጣናት በአካባቢው ባለ ሶንጎ ውስጥ፣ ህዝብ በሚበዛበት ሸንጎና ከባባድ ወንጀሎች ወደ ተፈጸሙበት አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ግጭት የመፍታትና የማስተዳደር ተግባራቸውን ይወጣሉ፡፡ የጌዴኦ አባሮጋዎች የስልጣን ዘመናቸው ስምንት አመት ብቻ ነው፡፡ ከስምንት አመት አገልግሎታቸው በኋላ እንደ አማካሪና ስራ አስለማጅ በመሆን ተከታዩን ስምንት አመት ከጀርባ ሆነው ይዳኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጥንቱ የግድያ ግጭት አፈታት ወቅት የውሳኔ ሰጭነቱን ሚና በዋናነት የሚወጡት ስምንቱን አመት የስልጣን ደረጃቸውን የጨረሱት አባሮጋዎች ነበሩ፡፡

አባሮጋዎችም እንደአባገዳ ሁሉ በቅዱስነታቸውና ከሰማይ አምላክ(ማጌኖ) የተላኩ ናቸው ተብለው መታሰባቸው(እነሱም ይህን እጅግ በጣም ያምኑበታል) ግጭቶችን ያለመድልኦ ለመፈጸም የሚያስገድዳቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ አባሮጋዎች የሚሰሩትን ነገር ፍትሃዊ ባይሆን ምን አልባት ሳያውቁት ቢሆን እንኳ ከፈጣሪያቸው ፈጣን የሆነ ቅጣት እንደሚገጥማቸው አቶ ጥላሁን እብዶ የሚከተለውን ትረካ ነግረውኛል፡፡

> "በጣም ተጠንቅቆ ነው ማገልገል ያለበት ምክንያቱም ይህ ሃላፊነት ከላይ የመጣ ነው፡፡ ህዝቡም አማኝ ስለሆነ ማሳዘን ቅጣቱን ከባድ ያደርገዋል፡፡ እንዲውም በቅርቡ ወደ አንድ አባሮጋ አንድ ሌባ ሳያውቀው መጥቶ መርቀኝ ይልና ምርቃት ከአባሮጋው ተቀብሎ ሃያ ብር ሰጥቶ ሄደ፡፡ አባ ሮጋውም ምርቃቱን አበርክተው በሃያ ብሩ ለቤቱ ምናምን ገዙበት ወዲያው በብሩ የተገዛውን ነገር ሲቀምስ ታመመ ምን ገጥሞዎታል? ሰሞኑን ምንስ ሃጢያት ሰርተዋል? ተብለው በሽማግሌ ሲጠየቁ ግራ እንደገባቸው ያሌባ ተይዞ መጣ፡፡ ወዲያውም ሌባውም አባሮጋውም ሞቱ ሳያውቁ ባደረጉት ነገር ነው እንግዲህ እና እኔ ተጠንቀቁ እያልኩ እመክራለሁ፡፡ መቀጣጫ ናቸው ማንም ቢሆን በሰው ገንዘብ ጉልበቱን ያላወጣበትን አይበላም፡፡ ምክንያቱም ያጠፋል" (ቃለመጠይቅ፡ ጥላሁን እብዶ፡ 30/05/2005)፡፡

ይህም የሚያሳየው ማንኛውም ሮጋ ጉቦ ተቀብሎ ወይም በስህተት ማናቸውንም አይነት አስተዳራዊ በደሎች እንደማይፈጽም ነው፡፡  ይህም የግጭት አፈታቱን ይበልጥ ተአማኒ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

### 4.3.3.3. ጠቅላላ ሸንጎ (ኦዳያአና በላያአ)

ይህ ሸንጎ የጌዴኦ ብሄር መነሻ እንደሆነ የተለያዩ ዝርው ትረካዎች ያስረዳሉ፡፡ ሸንጎው የጌዴኦ ብሄር አባላት መነሻ ብቻ ሳይሆን ስለአንድነታቸውና ፍቅራቸው የተማማሉበት የፍጹም እምነትና ፍቅር ቦታ ነው፡፡ የሚመራውም በታላቁና ንጹሁ አባ ገዳ ነው፡፡ እነኝህ ምክንያቶችም ተሰሚነቱን ከፍ ያደርጉለታል፡፡ ስለዚህ በየትኛውም ሸንጎ መፍትሄ ያልተገኘለት የግጭት አይነት  ከዚህ ሸንጎ ውጭ አይሆንም፡፡ ይህ ሸንጎ በብሄሩ የመጨረሻ የፍትህና የአስተዳደር ደረጃ በመሆኑ ፍትህ በጥንቃቄ የሚሰጥበት ነው፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ሸንጎ ይግባኝ ብሎ የመጣ ሰው ቅሬታውን አስወግዶና እርቅ ፈጽሞ ይመለሳል እንጅ ይግባኝ የሚለው አካል አይኖርም፡፡ በዚህ ሸንጎ መፍትሄ የሚያገኙ ግጭቶች ከባድ ግጭቶችና በሌሎች ሸንጎዎችና ከአባ ሮጋዎች በይግባኝ የመጡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ይህ ሸንጎ በጌዴኦ ብሄር ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውም ስለሆነ የትልልቅ ግጭቶችና የሁሉም ይግባኞች መጨረሻ ውሳኔ መስጫ ነው፡፡

## አባ ገዳ (ጋዲቾ)

> "የአባ ገዳ አመራረጥ የተለየ አካሄድ አለው ማለትም ሁሉም ልጆች ተሰብስበው ባለስልጣን ለመሆን የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ምንም አይነት ጠባሳ የሌለባቸው፣ ካልተፋቱቻች ሚስት የተወለዱ፣ በባህል እውቀት የበለጸጉ የሚሉት ይሆናሉ፡፡ በመጨረሻም እነዚህ የተመለመሉ ልጆች ይመረቁና ሁሉም ወንፊት ይዘው ውሃ ቀድተው እንዲያመጡ ወደ ወንዝ ይላካሉ፡፡ ከዛ በወንፊቱ ውሃውን ሳያፈስ ያመጣው አምላክ የመረጠው ስለሆነ ተመርጦ ስርአተ ሹመቱ ይፈጸምለታል፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ምጃኔ ጎበና፣ 02/06/2005)፡፡

በጥቅሱ እንደተገለጸው በዚህ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው በጣም በጥንቃቄና በልዩ መስፈርት የሚመረጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው በቅድስና ደረጃ ላይ የሚገኝና የማበረሰቡ ህመም የሚያመው ሳይታክት ለማህበረሰቡ የሚታትር እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ሰው ካለው ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ በተጨማሪ ልእለ ተፈጥሯዊ የሆኑ ባህሪያት ሲሰጡትና ምንም ነገር የማያቅተው ተደርጎ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ ይህም ሰውየውን ሚታዊነት ባህሪ ያላብሰዋል፡፡ አባ ገዳን እንደ ተጋዳሊ(hero)ና እንደ ቅዱስ ሰው(holy man) አድርጎ ማየት ይቻላል፡፡ Camphbell የአንድ ተጋዳሊ ሽ ገጽታዎች በተሰኘው መጽሀፉና Petter ቅዱሱ ሰው የተሰኘው ጽሁፍ የአንድን ማበረሰብ ቅዱስና ጀግና ሰው መለኪያዎች ከልዩ ልዩ ሚቶችና ትረካዎች በመቅዳት አለማቀፋዊ መስፈርት አስቀምጠዋል፡፡

የጌዴኦ ገዳ (ባሌ) ስርአትም ሆነ የጌዴኦ አባ ገዳ አነሳስ Petter በተለያየ የአለም ክፍል ገጠሮች በመዟዟር ካገኟቸው ውጤት ማለትም
"ቅዱሱ ሰው በንቃት ይንቀሳቀስባቸው በነበሩት ጠ/ግዛቶች የነበሩት መንደርተኞች የአመራር ቀውስ ያንገሸገሻቸው÷ ፍትሕ የጠማቸው ነበሩ፡፡ የአርኪዮሎጂ መረጃዎች የሚያሳዩት ነፃነት ናፋቂና ለራሳቸው ክብር ያላቸው ገበሬዎች አዲስ መደብ ከቀደምቱ ሥርዓት ጋራ መቆራረጡንና በውጤቱም የጋርዮሽ (መደብ-አልባ) ማኅበረሰብ መፈጠሩን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደሚባለው ቅዱሱ ሰው የተነሳው በሀገሪቷ ላይ በወረደ መከራና መርገምት ምክንያት አይደለም" (Brawon,93,1971)፡፡

የጌዴኦ ገዳ ስርአትና የመጀመሪያውን አባገዳ አነሳስን የሚገልጸው አፈታሪክም የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡ ማለትም ማህበረሰቡ የነጻነት እጦትና የጎሳሎ አስተዳዳሪዎች ፍጹም የሆነ የኢኮኖሚና የስልጣን የበላይነት ባንገሸገሻቸው ጊዜ ነበር አማራጮችን ይዞ ብቅ ያለው፡፡ ይሄውም የመጀመሪያው የባሌ መሪ ጎሳሎውን የሚያጠፋበትን ስልት ቀይሶ እንዴት ባለ

ሁኔታም እንደሚያስተዳድር ጭምር አመኔታን በማግኘት ነው ስልጣኑን የተረከበው (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/05/2005)፡፡

የጌዴኦ ብሄር ቅዱስ ሰውን(አባ ገዳን) ቃሉን መጠበቁ፣ የመንደሩን ሰዎች ከእንቅፋቶች መጠበቁ፣ ለአካባቢው ማህበረሰቦች በአቅራቢያቸው በመገኘት ፍትህን መስጠቱና አድካሚና አሰልች የነበሩትን ሙግቶች ማሳጠር መቻሉ በቅዱሱ ሰው መስፈሪያ ልክ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የጌዴኦ አባ ገዳ ብሄሩን ከአስቸጋሪ ህይወቶችና ከእንቅፋቶች የሚጠብቅ ፍትህን በአጭር ጊዜና ያለመድልኦ የሚሰጥ ከሰፋ የመደብ ልዩነት አውጥቶ በጋራ የማስተዳዳርን ጽንሰ ሃሳብ ያነገበ መሆኑ ነው፡፡ ይሄም እንደ Petter አገላለጽ እንዲህ አይነት አስተዳደርን ያመጣ ሰውን አክብሮትን ለመቸር የሚያመችና ህብረተሰቡም እንደ ቅዱስ ለመቀበልና እንደ ጀግና ለማወደስ እንዲመቸው ሊያደርግ የሚችል አስተዳደሩንም እንዲቀጥል ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡ ለዚህም ነው የጌዴኦ ገዳ ስርአት በየዘመኑ የገጠሙትን እንቅፋቶች በመቋቋም አሁንም ድረስ ከነተቀባይነቱና ለመዝለቅ የቻለው ማለት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም Camphbell ቅድስናን የተቀዳጀ ሰው ባህርያት ናቸው ያላቸው ሃሳቦችም ከጌዴኦ አባገዳ ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ቅዱስ ሰው እንደ ቅዱስ ሲኖር ከዓለማዊው ነገር ራሱን ያራቀ ወይም ስጋዊውን ዓለም የናቀ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አመጋገቡ በጣም ጥቂት፣ ንግግሩ ቁጥብ፣ አዕምሮው በተመስጦ ውስጥ የሚኖር፣ የነፃነት ሰው የሚሆን፣ ለማህበራዊ ደረጃው የሚጨነቅ ከራስ ወዳድነትና ከወሲብ ደስታ የሚርቅ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ሰው ተመስጦውንና ቅድስናውን ሊያደፈርስ ከሚችል ነገር ራሱን ያርቃል፡፡ ትኩረቱ ሁሉ በራሱ አመለካከት መሠረት የዕድቅ መንገድ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ነገሮች ማድረግ ላይ ይሆናል (Campbell, 2004, 354)፡፡

የጌዴኦ አባ ገዳም በCampbell የቅዱስ ሰው መገለጫ ናቸው ተብለው የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ነው፡፡ ይህም አለማቀፋዊ የሚት ስርአት ወይም ሞኖ ሚትን እንደሚጋራ የሚያሳይ ነው፡፡ ቁም ነገሩ ግን የሞኖ ሚት ስርአትን መጋራቱ ሳይሆን ተመራማሪዎቹ ይህን ቀመር ለመቀመር ሲያጠኑ በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ ያገኙት የቅዱሱ ሰው ፋይዳዎችን ለመፈተሽ የሚሆን አቅጣጫን የሚጠቁም ሃሳብ መፈንጠቃቸው ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ልእለሰባዊ ባህሪ የተሰጠው ምርጥ የመፍትሄ አካልና ሰው ተደርጎ መታሰቡ ምንን ያስከትላል? ማህበረሰቡስ ይህን ያህል የሚወደውና

የሚያከብረው ከቅዱሱ ሰው ምን ፈልጎ ነው? የሚለውን መመርመር ተገቢ መሆኑን ያሳየናል፡፡

ስለዚህም ለተከታዮቹ ምን ዓይነት ፍላጎቶቻቸው ናቸው የሚሟሉላቸው? ብለን ስንጠይቅ ቅዱስ ሰው በመጀመሪያ ከጥንታዊው የህይወት ሂደቶች የተወረሱ ብኸርታዎችን ይፈታል፡፡ ሁለተኛ በባህላዊ ስርአቱ ውስጥ ያለ ምርጥ አስተዳዳሪ ነው፡፡ ሶስተኛ የተጨነቀ አጽናኝ ነው፡፡ አራተኛ አጽናኝነቱ ቅዱሱን ሰው ያለበት አካባቢ አዛዥ አድርጎ እንዲቀበለው ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ማህበረሰቡ ያን ግለሰብ እንደ አስተዳዳሪ ብቻ ሳይሆን ከአምላክ በታች ከሰዎች በላይ እንዳለ አካል ቆጥረውት እንዲሽቆጠቆጡለት የሚያደርጉም ናቸው፡፡

በዚህ መንገድ የጌዴኦ ብሄር አባላት እንደቅዱስና ጀግና የሚቆጥሩትን አባገዳቸውን ማከበራቸውንና እንደ የአምላክ መልክተኛና በሰውና በአምላክ መካከል ያለውን ዳገት በመሰላልነት የሚያገናኝ፣ ሰፊውን የኑሮ ልዩነት በማጥበብ ሰዎችን ከጭቆና አገዛዝ የሚገላግል፣ ያለአድልኦ ፍትህን የሚሰጥና ከመንግስት ያጡትን ቅልብጭ ያለ መፍትሄና ከቢሮክራሲ ነጻ የሆነ የፍትህ ስርአት የሚለግስላቸው በመሆኑ በአስተዳደሩም ሆነ በፍትህ አሰጣጡ እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል፡፡

የጌዴኦ ገዳ ስርአት አዛዥ የሆነው ግለሰብ ይፈጽማቸዋል ተብለው የተቀመጡትን ሚታዊ አስተሳሰቦች ማለትም ዝናብ ማዝነብ፣ ርግማኑና ምርቃኑ በዛው ቅጽበት መፈጸም ከሁሉ በላይ ደግሞ ድንገት አባገዳው ተከታያቸውን ሳይመርጡ ሞት ቢቀድማቸው ብሄሩና ከልጆቻቸው መካከል አንዱን በአባ ገዳነት ለመሾም ሁሉንም በወንፊት ውሃ ቅዱ በማለት አባ ገዳ የሚሆነው ሰው ከወንፊቱ ውስጥ ያለው ውሃ አንድም ጠብታ ሳይጎድል ይዞት ይመጣል(የቡድን ውይይት፣ ገደብ ወረዳ)፡፡ የሚለው ሚታዊ ትረካና አስተሳሰብ ማህበረሰቡ በባህላዊ አስተዳደሩና በፍትህ አሰጣጡ የበለጠ እንዲተማመን የማድረግና መረጋጋትን የመጠበቅ ተግባርን የመፈጸም አቅም ያለው ነው፡፡

## 4.4. በብሄሩ የግጭት መፍቻ ተቋማት ወንበር የሌላቸው ቡድኖች

በጌዴኦ ብሄር በተለያዩ ምክንያቶች ለዳኝነት አይበቁም ተብለው የማይመረጡ የአካባቢው ማኅበረሰብ ክፍሎች አሉ? እነማን ናቸው? ለምንድነው ማእቀብ የሚደረግባቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይገኙ ከቀደመው ትውፊት ጋር እያያያዝኩ እተነትናለሁ፡፡

የጌዴኦ ብሄር ግጭቶችን በሚፈታበት ወቅት እንዲሳተፉ የማይፈቅድላቸው ሶስት የብሄሩ አካላት አሉ፡፡ እነሱም ሴቶች ነፍስ ያጠፉ ሰዎችና በልዩ ልዩ እደጥበባት የሚተዳደሩ ግለሰቦች (ፉጋዎች) ናቸው፡፡ በመሆኑም በነዚህ ሶስት ወገኖች መገለል ውስጥ ሁለት አይነት የማንነት የርእዮተ አለማዊ ጽንፎች ጎልተው ይወጣሉ፡፡ እነኝህም ጽንሰ ሃሳቦች ስርአተ ጾታዊ ርእዩተ አለም (Gendr ideology) እና ሌላ ወገን (The other) የሚሉት ናቸው፡፡

የጌዴኦ ብሄር አባላት በአፈታሪካቸው እንደሚገልጹት በቀደምቱ የንግስቷ የአስተዳደር ወቅት ሰፍኖ የነበረው እማዊ ስርአት ነበር፡፡ የስርአተ ጾታ ባለሙያዎች በስርአተ ጾታ ቀመራቸው ጠንካራ ፣ አስተዳዳሪ፣ ጀግና፣ የመፍትሄ አካል ወዘተ. ተደርጎ የሚቆጠረው ተባእት ነው የሚለው አመለካከት ለጌዲኦ ብሄር አባላት አይሰራም ነበር፡፡ ምክንያቱም የጌዴኦ ብሄር እማዊ ስርአት(አኮማኖዮ) ተባእትነት የሚባለውን ስርአተ ጾታዊ ጽንሰ ሀሳብ ለእንስቶች የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የቀጠለው የጎሳሎ የአስተዳደር ስርአት እስኪመጣና አባዊነት መቀንቀን እስኪጀመር ድረስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ጎሳሎ የተሰኘው አስተዳደር ስርአት አነሳሱም ሆነ ውጤቱ እማዊ ስርአት አራማጅ የሆነውን አኮማኖየ ስርአት በመገርሰስ ስርአተ ጾታዊ የበላይነቱን ከሴቶች በመንጠቅ ተባእታይነትን ወደ ወንዱ መመለስ የሚለውን አላማ ያነገበ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እማዊ ስርአቱ ካበቃበት ጊዜ ጀምሮ ግጭቶችን የመፍታትም ሆነ የማስተዳደሩን ሚና ሙሉ ለሙሉ የወሰደው ወንዱ ነው፡፡

በሌላ በኩል ስለአኮማኖየ (የንግስት አስተዳደር) አነሳስና ውድቀት የሚሰጠው ተረክ [11] ሴቶች ሰልጣን እንደማይገባቸውና አስተዳዳሪነት እንደማይችሉ የተብራራበት ነውም ልንለው እንችላን፡፡ ይህ አካሄድ በሌሎችም ባህሎች ውስጥ የተለመደ እንደሆነ የእንስታዊነት በባህል ውስጥ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ እንዲህ አይነቶቹን ትረካዎች ለሁለት አላማ ሊያቀርቧቸው ይችላሉ፡፡ እነሱም አንደኛው አምባገነንነት መድረሻው ውድቀት መሆኑን ለማስረዳት ሁለተኛው ደግሞ የሴቶች ወደ ሸንጎ እንምጣ ሀሳብ መከላከያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

---

[11] የዚህ አይነት ሃሳብ ያለው የአቶ አብርሀም አለሙ ቃላዊ ትረካ ሴቶችን ዝቅ እንደሚያደርጊያ የርእዮተአለም መሳሪያ በሚለው መጣጥፍ ውስጥ በጅማ ኦሮሞ ውስጥ ከሚተረኩት ታሪኮች መካከል የንግስቷ የጭካኔ አገዛዝና ንግስቷ ሀላፊነቷን ያለመወጣቷን ሁኔታ በመግለጽ ሴቶች እንምራ ብለው እንዳይጠይቁ ብሎም እንገዛም ብለው እንዳያምጹ ርእዮተ አለማቸውን ለማጽናት የሚጠቀሙበት እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል የጌዴኦ ብሄር ባህላዊ ሸንጎና የአስተዳደሩ መዋቅር ብሄሩ ፉጋ[12] ለሚላቸው እደጥበብን እንደመተዳደሪያ አድርገው ለያዙ የማህበረሰብ ክፍሎች ቦታ የለውም፡፡ ለዚህ አጥጋቢ ምክንያት ወይም የጸና ማብራሪያ አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን ከተለያዩ ሰዎች ጋር ባካሄድኩት ቃለመጠይቅ ከተገለጹልኝ ሃሳቦች መካከል እነዚህ ማህበረሰቦች የጌዴኦ ብሄር አባላት አይደሉም፡፡ ጌዴኦ ፉጋ የለውም፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/05/2005) የሚለው ገለጻና ከአባት የመጣ ነው፡፡ እነሱ መፍትሄ አይሰጡም እንዲሁ ሲጠሯቸው በሌሊት ጉዳያቸውን ፈጽመው መሄድ እንጅ እነሱም አይመጡም ቢመጡም አናማክራቸውም፡፡ እነሱ ግን ተበደልን ሲሉ ሽምግልና ይኬድላቸዋል (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ከተማ፣ 20/08/2005)፡፡ የሚሉት ገለጻዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በነዚህ አገላለጾች የምንረዳው ዋና ጉዳይ የጌዴኦ ገዳ ስርአትም ሆነ የማህበረሰቡ መዋቅር ሌላ ወገን ብሎ ድንበር የሚያሰምር መሆኑን ነው፡፡ ይህን ድንበር ለመጣስ የሞከረ እና ብሄሩን በሽምግልና ማገልገልን እንደመብት ጥያቄ ያቀረበ የማህበረሰብ ክፍል የለም፡፡ ይህ ደግሞ ብሄሩ ለእያንዳንዱ በጎሳ፣ በጾታ ወይም በሙያ ቡድንም ሆነ በሌላ አደረጃጀት የተሰመረውን የማህበራዊ ሚና ድንበር ለማፍረስ ያለመሞከርን ነው፡፡

በአጠቃላይ ስናየው ግን በጌዴኦ ማህበረሰብ ሴቶችና ፉጋዎች ለሽምግልና አይመረጡም፡፡ በተለይ ሴቶች ጓደኞቻቸውንና ታናናሾቻቸውን እንዲሁም ልጆቻቸውን ከመምከርና ከመገሰጽ ያለፈ የግጭት መፍታትና የማስታረቅ ሚና አይጫወቱም፡፡ ነገር ግን ግጭቶችን የማብረድና የማረጋጋት ውስጣዊ ሚናቸው እንደተጠበቀ ነው፡፡ ማለትም ግጭቶች ሲፈጠሩ የማጋጋልና ሁኔታውን የማባባስ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል በዛው መጠንም ከባድ ግጭቶች ሲፈጠሩ ሁኔታውን ቀዝቀዝ የማድረግ እና ሰላም የማስፈን ሚና ሊኖራቸው ስለሚችል የአካባቢው ሽማግሌዎች በእጀዙር ስለግጭቱ ከሴቶች ጋር ሊማከሩ ይችላሉ፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክተውም ወይዘሮ አስረሴ የሚከተለውን ታሪክ ገልጸውልኛል፡፡

> "አንድ ዘመዳችን አንድ የሰፈር ሰው ሰደበው የሰደበውም በሚስቱ ፊት ነው እና ሁለቱም በጣም ተናደዱና ምስትየውም እሱንም መልሶ በባለቤቱ ፊት እንዲያዋርደው ፈልጋ ትገፋፋው ጀመር የሷ ሃሳቧ እንዲያዋርደው ፈልጋ ነበር እንጅ እንዲህ ይከራል ብላ አላሰበችም ነበር መቼም ሴት የላከው ነው የምትለ እናንተ… ከአንቱ ጋር ሆነው በሌሊት ቤቱን ሊያቃጥሉና ሲወጣም ሊገድሉት ፈልገው ሲዶልቱ ሚስትየው ትሰማና የቀጠሩትን ቀን እንደምንም በዘዴ አሳልፋ ጉዳዩን ለሃይቻዎች በመንገር ሃይቻዎች መጥተው አባትና ልጁን ተቆጥተው

[12] በጌዴኦ ብሄር አባላት ዘንድ ፉጋ ማለት በእደጥበብ ሙ ያ የሚተዳደር ማለት ነው፡፡

ከሰውየው ጋርም አስታርቀው ሄደዋል" (ቃለመጠይቅ፣ ወይዘሮ አስረሴ ማሙሽ፣ 23/08/2005)፡፡

ከላይ በቀረበው የአብነት ታሪክ ላይ እንደምንረዳው ሴትዮዋ በመጀመሪያ የነበራት ሚና በሰዎቹ መካከል የተፈጠረው ችግር ባለበት እንዳይቆም የማድረግ ነበር፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በጣም ተባብሶ ከባድ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሆነ ሲታወቃት እንደገና ጉዳዩን የማብረድ አካሄድ እንደተከተለች እንረዳለን፡፡

በእደጥበብ የሚተዳደሩት የማህበረሰብ ክፍሎችም በባሌ የስልጣን ደረጃዎች ውስጥ ቦታ ኖሯቸው ግጭት ለመፍታት ባይችሉም በግድያ ግጭት አፈታት ሪቹዋል ወቅት ገዳይን የማንጻት ሚና አላቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው አንዱ ጉዳይ ነፍሰ-ገዳዩን ብዙ ክብር በሌለው የማህበረሰቡ ክፍል እንዲታጠብ በማድረግ ስሜቱን መጉዳት ሲሆን ሁለተኛው በነፍሰ-ገዳዩ ላይ ሰፍሮበታል ተብሎ የሚታሰበውን ክፉ መንፈስ የሚያስወግዱት እነሱ ናቸው ተብሎ መታሰቡ ናቸው፡፡ በተለይ በሁለተኛው ሀሳብ ላይ የሚገኘው ዋናው ጉዳይ የእደጥበብ ባለሙያዎቹን መናፍስትን የማዘዝ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

## 4.5. የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ አውድ

ሪቹዋል ሲጠና ከማህበራዊ አውዱ ጋር አስተሳስሮ ማጥናት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ርእስ ስር የምናየው ዋና ጉዳይ ሁለቱ ሸንጎ ቦታዎች ማለትም በጩጬ አካባቢ ሸንጎ ማክሰኞ ከጥዋቱ ሶስት ስአት ጀምሮና በገደብ አጠቃላይ ሸንጎ ሀሙስ ከጥዋቱ አራት ሰአት ጀምሮ ሲካሄድ ያስተዋልኩትን ስርአተ ክዋኔ በገለጻና በክዋኔው ውስጥ ያስተዋልኩትን አንዳንድ ትእምርታዊ ጉዳይ በቃለመጠይቅ ካጣራሁት ጋር እያስተሳሰርኩ ነው ፡፡

የጌዴኦ ብሄር ግጭት የሚፈታባቸው ቀናት እንደየ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ይለያያሉ፡፡ ማለትም በአብዛኞቹ አካባቢዎች የገበያ ቀናትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲሆን በሌሎቹ ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎችና የአካባቢው ሰዎች በመስማማት ያደረጉት ነው፡፡ ስአቱ ግን ምንጊዜም ቢሆን ጥዋት ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሽማግሌዎቹ ምግብ ሳይበሉ ውሃም ሳይነኩ የሚያከናውኑት የጸሎት፣ የምርቃት፣ የማስማልና የእርግማን ስነስርአት ስላለ ነው፡፡ የጌዴኦ ብሄር አባላት ወደሶንጎ ሲሄዱ ከምግብና ከመጠጥ እንዲሁም ውሃ ከመንካት ይቆጠባሉ፡፡ የብሄሩ የግጭት አፈታት ስነስርአት በሚካሄድበት ቦታ(ሶንጎ) ውስጥ የተለያዩ ስነስርአቶች ይካሄዳሉ፡፡ እነዚህም ልመና(ጸሎት)፣ ሆላ ማለት(ያልታጠቀን ሌባ የመርገም ስነስርአት)፣ መሃላ መፈጸምና የጉዳይ መስማት መርሃ ግብሮች ናቸው፡፡

የጌዴኦ ሸንጎ የሀገር ሽማግሌዎች በአንድ ጉባኤ ለመሰየም ከአምስት በላይ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሃይቻ፣ ሙራ፣ ጸሃፊና ቢያንስ ሁለት የኃይማኖት አባቶች ናቸው፡፡ ምልከታ ባካሄድኩባቸው ሁለት ቀናት የግጭት አፈታቱ ከመጀመሩ በፊት የሀገር ሽማግሌዎቹ እና የሃይማኖት አባቶች በአንድ ላይ ከሶንጎው ጎጆ በስተቀኝ በኩል ወዳለ ሚዳማ ጸሎት መፈጸሚያ ቦታ በሰልፍ ሄደዋል፡፡ እነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች በጭራሮ አጥሯ አጠገብ በቆመ ባለ ባላ እንጨት ላይ በትሮቻቸውን በማስቀመጥ በቅደም ተከተል እየሾለኩ ወደጸሎት ቦታው አመሩ፡፡ ይህ ድርጊት ራሳቸውን ከክፉ መንፈስ ነጻ ለማድረግ የሚፈጽሙት ስርአት ነው፡፡ ምክንያቱም ክፉ መንፈስ ይህን የጭራሮ በር አልፎ እንደማይሄድ ስለሚታሰብ ነው፡፡[13]



ፎቶ ግራፍ ቁጥር አንድ፡- ሃዩዎችና ወዩዎች በበትር ማስቀማጫው እየሾለኩ ወደ ጸሎት ቦታ ሲሄዱ

ታዳሚወቹም ከነሱ ጀርባ ከተቀመጡ በኋላ የሃይማኖት መሪዎቹ ጸሎታቸውን ጀምረዋል፡፡ ይህን የጸሎት ስነስርአት የሚመሩት በገደብ አጠቃላይ ሸንጎ የሸንጎው መሪ ሃይቻ ጀቦ ኩራ ናቸው፡፡ ታዳሚዎቹም አብረው በመጸለይና 'አሜን' በማለት እንደሚሳተፉ ተመልክቻለሁ፡፡ የጸሎቱ ይዘትም በመጀመሪያ የጌዴኦን ሰባት ጎሳዎች ስም በመጥራት የእነዚህ ጎሳዎች አምላክ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በሁለተኛነትም የማጌኖን ታላቅነት የሚያሳይ ነው፡፡ ይሄውም

| | |
|---|---|
| *Ati laqqaateken* | *አንተ ሰሚ ነህ* |
| *Ati dhuggaaten* | *አንተ እውነት ነህ* |
| *Aridda heqqitetexxee* | *ህዝቡን ስለጠበክ* |

13 በጭራሮ አጥር ውስጥ ማለፍ ህሙማንን ከበሽታ ለመፈወስ አገልግሎትና አጋንንት አድሮባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን ጭምር ለመፈወስ የሚደረግ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| *Olaa heqqitetexxee* | *ጎረቤቶቻችን ስለጠበክ* |
| *Bogga heqqitetexxee* | *ሀገራችን ስለጠበክ* |
| *Gossa heqqitetexxee* | *ብሄሩን ስለጠበክ* |
| *Galateeffantannon* | *እናመሰግንሀለን* |

በማለት ለአምላካቸው ያላቸውን ክብር በማሳየት ይጸልያሉ፡፡ የመጀመሪያውን ዙር ጸሎት ከጨረሱ በኋላ ወደ ሁለተኛው ጸሎት ሳይሸጋገሩ ሆላ ሊያስብል የመጣ ሰው መኖሩን ጠየቁ፡፡ በእለቱም አንዲት ሴት ከታዳሚዎቹ መሃል ተነስታ ቤቷን ዘግታ ከሄደችበት አንድም እቃ ሳይቀር መዘረፏንና ሌባውን እንዲረግሙላት ጠየቀች፡፡ ከዛም ሆላ የማለት ስርአተ ጸሎት አካሄዱ፡፡ ስርአተ ጸሎቱም የተለያየ ግን ተያያዥ ይዘት ያለው ነው፡፡ የመጀመሪያው የአምላክን ታላቅነት የሚገልጽና ከሰዎች የመጣውን ስሞታ የሚያሳስቡበት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| *Ee-magenoo* | *አቤቱ እግዚያብሔር ሆይ* |
| *Ati Ardiki magenon* | *አንተ የህዝብ አምላክ ነህ* |
| *Ardi kin nu'on kula'n'en* | *ህዝብህ ወደኛ ስሞታ እያቀረበ ነው...* |

በሚለው ጸሎት ውስጥ በአንጻሩ አስጸላዩ በህዝብና በአምላክ መካከል እንዳለ አገናኝ አካል መሆኑንም የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ ስልጣኑ ከተራው ታዳሚና ባለጉዳይ የተለየ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ይህም የስልጣን መዋቅርን የሚያሳየን ነው፡፡ በጌዴኦ ብሄር የግጭት መፍቻ ተቋም ውስጥ የሚገኘው የስልጣን መዋቅርም በአምላክ በባለስልጣናቱና በማህበሩ መካከል ድንበር ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በአምላክና በባለስልጣናቱ መካከል ያለውን ድንበር የሚያሳየን የጸሎቱ ክፍልም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| | |
|---|---|
| *No'o manjoken* | *እኛ ሰዎች ነን* |
| *Ati magenooken* | *አንተ አምላክ ነህ* |
| *No'o anfaben'on* | *እኛ አላየንም* |
| *No'o egenebon'on* | *እኛ የምናውቀው ነገር የለም* |
| *Yaane kini* | *ነገር ግን* |
| *Ati affeetteen* | *አንተ አይተሀል* |
| *Ati egendatton* | *አንተ ታውቃለህ* |
| *Baxxeexxa karra Annakkee ati leeliishi* | *አንተ የጠፋውን ንብረት ለባለንብረቱ አስገኝለት* |
| *Mooreeka kinni Ati lekka abid...* | *የሰረቀውን ደግሞ አንተ እግሩን ያዝልን...* |
| *Issi doo do'o waali* | *እግዚያብሄር ሆይ አንተ አፍዝዘው* |

ከላይ በቀረበው ጸሎት እንደምንመለከተው ሆላ ልታስብል የመጣችው ሴት ጉዳዩን ካስረዳች በኋላ በቅርብ የምታገኛቸው ባለስልጣን ሰዎች መፍትሄ እንዲሰጧት ነበር

የጠየቀችው፡፡ ነገር ግን ባለስልጣኖቹ ለአምላካቸው በሚጸልዩት ጸሎት ውስጥ የነሱን አቅም ልክ ወይም ችሎታቸው የት ድረስ እንደሆነ የሚያስረዱት(በዚህ አውድ ውስጥ የቀረበችውን ሴት ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ታዳሚውን ሊወክል ይችላል) ስሞታ ወደኛ መጥቷል በሚለውና እኛ ሰዎች ነን በሚለው አገላለጽ ነው፡፡ አያይዘውም ጸረ ሰላም የሆነና የማህበረሰቡን መረጋጋት ሊያቃውስ የመጣ ጠላት መኖሩን ይህንም ማህበሩ የሚያወግዘው መሆኑን ለአምላካቸው በጸሎት መልክ ለታዳሚው ደግሞ ለሌባው በቀረበ ግሳጼ መልክ ያቀርቡታል ማለት ነው፡፡ የመጨረሻ የሆነው የሆላው ክፍል ደግሞ ቅጣቶችን እንዲሰጥና ግፉን በሚዛናዊ አይኑ እንዲያይ ለአምላክ ከመንገር በቀጥታ የመልእክቱን ተቀባይ ሌባውን የሚያደርጉበት ነው፡፡ ይሄውም ከተራው ማህበረሰብ የሚለያቸውንና በእርግማን ከነሱ የሚወጣውን የመገሰጽ ስልጣን የሚያሳዩበት ነው ማለትም ይቻላል፡፡ በዚህ ክፍል ሌባው ላይ ክፉ የተባለው ነገር ሁሉ እንዲደርስበት ይረግሙታል፡፡

| | |
|---|---|
| Ati kinni moodhalchi | አንተ ደግሞ ሌባው |
| Doodo'i | ፍዘዝ፡፡ |
| Tutum | ዶልዱም (ደንዝዝ)፡፡ |
| Lattoxxe | አያሳድግህ፡፡ |
| Ba'i | ጥፋ፡፡ |

የሰረቀው ሰው ንብረቱን እንዲመልስ ወይም ሌባው ባለበት ፈጣሪ እንዲቀጣው የሚካሄደው የጸሎት አይነት የሚደመደመው የጸለዩት ጸሎት እንዲሳካ በመመኘት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| *Ee maggennoo* | *አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ* |
| *Ati kadha no'oxxa laqe* | *አንተ ልመናችንን ሰምተህ* |
| *Galata adhitatoke kadi* | *ለምስጋና አብቃን፡፡* |

በአጠቃላይ ሆላ የማለት ስነስርአቱ ውስጥ ተደብቆ ጥፋት የሰራ ወንጀለኛን ለማግኘት ከሚደረገው እርግማንና የወንጀል ምርመራ አካሄድ በተጨማሪ የማህበረሰቡን የደረጃ መዋቅር ማለትም በአምላክ፣ በሃዩዎችና ወዩዎች እንዲሁም በተራው የማህበረሰብ ክፍል መካከል ያለውን የስልጣን መዋቅር የሚያሳይም ነው፡፡ ይህ የስልጣን መዋቅርም በአምላክ(ማጌኖ) በኩል ከማህበረሰቡ መጥቶ በመሪዎቹ በኩል ወደእሱ የመጣውን መልእክት ሰምቶ ፈጣን ምላሽ መስጠት ነው፡፡ በሃዩዎችና በዎዩዎች የሚታየው የስልጣን መጠን ወንጀለኛን በእርግማን እንዲጠፋ ማድረግ፣ የሰዎችን ስሞታ ወደ ልእለ ተፈጥሮ ማሻገርና ምላሽ መስጠት፤ ለተጎጅ መልካም ምኞትን በመግለጽ በተስፋ መሙላት

የመሳሰሉትን መወጣት በሀይማኖት አባቶቹና በገዳ ባለስልጣኖቹ የሚፈጸም ነው፡፡ ለተራው ህዝብ የሚሰጠው የስልጣን አቅም ደግሞ የልእለ ተፈጥሮ ተራዳኢነት እንዳይለየውና በአምላክና በሰው መካከል ሆነው የሚመሩት አስተዳዳሪዎቹ እንዳያዝኑበት ራሱን ከወንጀል ነጻ ማድረግ ነው፡፡

ሆላ የማለቱ ጸሎት እንዳበቃ ባለስልጣናቱና የሃይማኖት አባቶቹ በገቡበት እየሾለኩ በእጃቸው ያለውን ከስሩ ጦር ያለበትን ዘንግ መሿለኪያው ውስጥ ባለው ባላ እያስደገፉ በማስቀመጥ ወደላይ ወጥተው በሶንጎው ግቢ ውስጥ ወደሚገኘው ታላቁ ዛፍ በመሄድ የመጨረሻውን ጸሎት ጸለዩ፡፡ ይህ ጸሎት የሚጠብቃቸውን ዳኝነት የመስጠት ተግባር አምላካቸው እንዲባርክላቸው የሚለምኑበትና ወደ ሀገርና መንግስትም ዘልቀው መልካም ምኞት የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም፡-

| | |
|---|---|
| Ee *magenoo* | አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ |
| Techixxe bukki'a kinni | ለዛሬው ጉባኤ ደግሞ |
| Ati no'oxxe oddo'n affemi | አንተ በመካከላችን ተገኝ |
| Ati dhuggaate kadhattannon | አንተን በእውነት እንለምንሀለን |
| Dhuggaate hasonanosha gargaar | እውነቱን እንናገር ዘንድ አንተ እርዳን |
| Fuggoka,naapha maddeten hiisi | ክፉውን ጠላት ያዝልን |
| Arada nageesi | ህዝብህን ጠብቅ፣ ሰላምን ስጥ |
| Olaa nageesi | ለጎረቤቶቻችን ሰላም ስጥ |
| Boga nageesi | ለሀገራችን ሰላም ስጥ |
| Mootumma nageesi | ለመንግስታችን ሰላም ስጥ |

ፀሎቱን እንደጨረሱም በሃዩዎችና ወዩዎች መሪነት ወደሶንጎው ውስጥ ተገባ፡፡ ወደሶንጎ ስንገባ ወንዶች በፊት ለፊት በር ሲገቡ ሴቶቹ በጀርባ በኩል ባለው በር ገባን፡፡ ከገባን በኋላ ሴቶቹ ከወንዶቹ ተነጥለው በገቡበት በር ዙሪያ ሲቀመጡ ወንዶቹም እንደዚሁ ተቀምጠዋል፡፡ ሃይቻውና ሌሎች ሽማግሌዎችም እንደ ስልጣን ደረጃቸው እየተገባበዙና እየተከባበሩ ከታዳሚው ፊት ለፊት ባሉ ባርጩማ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ሁሉም ሰው ቦታ ቦታውን ይዞ ሲያበቃ ሃዩዎችና ወዩዎች ድጋሚ በጸሎት መንፈስ በመሆን


| | |
|---|---|
| *Bukki no'oxxa abideennen muunxxano-qiccon Ati nu'on wolti hedhi* | ጉባኤያችንን ጀምረናል እስከፍጻሜው አንተ ከኛ ጋር ሁን |

በማለት የመግቢያ ጸሎት በድጋሚ አሰምተው የግጭት መፍታት ሂደቱ መጀመሩን በይፋ አበሰሩ፡፡ ሽማግሌዎች በሚሰጡት ቅደም ተከተል መሰረት ወይም እንዳቀማመጣቸውና

እንዳደራረሳቸው ባለጉዳዮች እየተነሱ እከሌ በደለኝ፣ ልጀን ደፈረብኝ፣ ባለቤቴን ደፈራት፣ ንብረቴን ሰረቀ፣ ልጆቹ ሰደቡኝ የመሳሰሉ በደሎቻቸውን በየተራ እያቀረቡ ሽማግሌዎቹም እያስማሙ፣ እየቀጡና መፍትሄ እየሰጡ ቆዩ፡፡

አካሄዱም ተከሳሾች እየተነሱ ጉዳያቸውን በየተራ ያስረዳሉ፡፡ በክስ ሂደት ወቅት ከሳሽ ወደፊት ቀረብ ብሎ ሲናገር ተከሳሽ ከከሳሹ በስተጀርባ ቆሞ ሀሳቡን ያስረዳል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለጉዳዮዎች እየተሸቆጠቆጡና ለሀገር ሽማግሌዎች ያላቸውን ክብር በሚያሳይ መልኩ መናገር ይኖርባቸዋል፡፡ ተከሳሹ ጥፋቱን ካመነ እንደ ወንጀሉ አይነት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል ወይም ለሰራው ነውር ጉዳይ ግሳጼ ከበዛም ከማህበሩ እንዲገለል ሊያስደረግ ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይም በቃለ ጉባኤ ያዥው እየተመዘገበ ሁሉም በእለቱ የተገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ይፈርሙበታል፡፡ ጉዳዮችን በፋይል ማስቀመጥ የጀመሩት ከመቼ ወዲህ እንደሆነ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ቁርጥ ያለውን ጊዜ ማስቀመጥ እንደሚቸገሩ ገልጸውልኝ በመንግስት ስልጠና ተሰጥቷቸው እነሱም አስፈላጊነቱን አምነውበት እያደረጉት መሆኑን ገልጸውልኛል (ቃለመጠይቅ፣ ጀቦ ኩራ፣ 02/06/2005)፡፡

አፍ እላፊ እንደ ደረጃው የገንዘብ ቅጣት፣ ከሸንጎ መባረር እልፍ ካለም እስከ ማስረገም ይደርሳል፡፡ በገደብ አጠቃላይ ሸንጎ ምልከታ በማደርግበት ወቅት የተፈጸመውን ከመስክ ረዳቴ እንደተነገረኝ ልጆቹ ልጄን አስገድደው ደፈሩብኝ በሚል ተከሶ የቀረበው ሰው የክህደት ቃሉን ለዳኞች በማስረዳት ላይ ሳለ የሸንጎው ቃለ ጉባኤ ያዥ ሃሳቡን ጠቅለል አድርጎ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ በመበሳጨት "አንተ ምን አገባህ ዝም በልና የማወራውን ጻፍ እኔ ለባለስልጣናቱ ነው የምናገረው" በሚል ለጸሃፊው ክብር በማይሰጥ መልኩ ሲናገር ሃይቻው በጣም ተበሳጭተው ወዲያውኑ ሁለት መቶ ብር ቀጥተው ይቅርታ እንዲጠይቀው አድርገው ችሎቱን አስቀጥለዋል፡፡



**ፎቶ ግራፍ ሁለት፡-** በአፍ እላፊ(በስነስርአት ባለማውራት) የተቀጣውን ገንዘብ ሲያስረክብ

በሽምግልናው ወቅት ተከሳሾች ወንጀሉን እንዳልፈጸሙ በፍጹም ከካዱ እንዲተውና ስህተታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁ እንደሚሻል ካልሆነ ግን እንዲምሉ ሊደረግ እንደሚችል አስረድተዋቸዋል፡፡ ጥፋቱን እንደሰሩ ወይም የተወሰነ ጥፋት እንዳለባቸው እያወቁ ቢክዱ ግን ሊደርስባቸው የሚችለውን ነገር እንዲያስቡበት፣ የተለያዩ ሰዎችን በስህተት ምለው ወዲያውን መሞት ታሪኮች ይነገራቸዋል፡፡ እንዲያስቡበት የአንድ ሳምንት ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ የአንድ ሳምንት ጊዜ ብቻቸውን ሳይሆን ከቤተ ዘመድ ጋር የሚገናኙበትና የሚመክሩበት እንዲሆንም ከአደራ ጭምር ያሳስቧቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሹ ልጅ ነው ብለው ካመኑ ወላጆቹን በተለይም አባት ካላቸው አባታቸውን ይዘው እንዲመጡ ለቀጣዩ ሳምንት የሸንጎ ቀን ይቀጠራል፡፡

ምልከታ ባካሄድኩበት ወቅት አንድ ታዳጊ በአጎቱ ተከሶ ቀረበ፡፡ ከመስክ ረዳቶቼ እንደተረዳሁት የክሱ ሀሳብም የከሳሽ ባለቤት በታዳጊው ጓደኛ ተገዳ መደፈሯ፣ ተከሳሽ ሆኖ የቀረበው ታዳጊም የአጎቱን ሚስት በማስደፈር በመተባበርና ለደፋሪው ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ነበር፡፡ በዚህ ክስ ሁሉም የሸንጎው አባላት በጣም መደንገጣቸውና ጉዳዩ ከአእምሯቸው በላይ መሆኑን በተለያየ አካላዊ ገለጻና ግሳጼ ይገልጹ ነበር፡፡ ልጁም ተራው ደርሶ ጉዳዩን ሲያስረዳ ጓደኛው ለጾታዊ ግንኙነት ይፈልጋት እንደነበር ገልጾ ፈጽመሃል ስለተባለው ጉዳይ ግን ምንም ነገር እንደማያውቅ ነበር ያብራራው፡፡

በዚህ ጊዜ ሊያስምሉት እንደሚችሉና በሃሰት ቢምል የሚፈጠረውን አደጋ ደጋግመው ቢያስረዱትም ልጁ በሃሳቡ ስለጸና ለሚቀጥለው ሳምንት አባቱን ይዞ እንዲመጣ ቀጥረውታል፡፡ ይህ ቀጠሮ የተከሳሽ እውነተኛነት የሚታይበት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሽማግሌዎቹ ከማስማላቸው በፊት በሃሰት የማሉ ሰዎች ላይ መሃላው የሚያመጣባቸውን ጦሶች ደጋግመው ያስረዳሉ፡፡ ተከሳሽ እምላለሁ እንጅ ምንም አልበደልኩም በሚለው ከጸና ወይም ከካደ ከሳሹ እንደገና ይጠየቃል፡፡ ከሳሹም እንዳይጎዳ ይፈልግ እንደሆነና ከሆነም ሳይምል ይቅር እንዲለው ይጠይቁታል፡፡ ይሄም አንዱ የምርመራ ሂደት መሆኑን የሀገር ሽማግሌዎች ገልጸውልኛል፡፡

ተከሳሾቹ ይቅርታ እንዲደረግላቸው ሳይሆን ምለው እውነተኝነታቸው እንዲመሰከርላቸው ከሆነ የሚፈልጉት የሀይማኖት አባቶች ወስደው እንዲምሉ ያደርጓቸዋል፡፡ መሃላውም

ምንም ውሸት አልተናገርኩም ምንም አልበደልኩትም እሱ እንዳለው ሆኖ ቢገኝ አምላኬ ይፍረድብኝ፣ የሃገር ሽማግሌዎችንም ንቄ እውነት ሳላወጣ ከቀረሁ እግዚያብሄር እውነት ያውጣብኝ የሚል ነው፡፡

ከሳሽ ጉዳዩን አሰምቶ ተከሳሽ ሳይገኝ ቢቀር በሚያውቀው ሰው ወይም በሸንጎው ተላላኪ በኩል እንዲገኝ ደብዳቤ ይላክለታል፡፡ ነገር ግን ደብዳቤውን አይቶም ቢሆን ላይመጣ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የሸንጎው ባለስልጣናት ለአካባቢው ሚሊሻ ጽህፈት ቤት ወይም ለአካባቢው ፖሊስ ጽህፈት ቤት ተፈላጊው ተከሳሽ ተገዶ እንዲቀርብላቸው በደብዳቤ ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ የሸንጎ ቀን ተከሳሹ በፖሊስ ተገዶ ይቀርባል፡፡ እንደቀረበ ሲጠራ የቀረበትን አርባ ብር ተቀጥቶ ወደ ክስ ሂደቱ ይገባል፡፡ በዚህ አካሄድ ውስጥም የዘመናዊውንና የባህላዊውን ተጣምሮ መገኘት እናይበታለን፡፡ ይህም የባህልን ትውፊታዊባህሪ ማለትም መሰረታዊጉዳዮችን መያዝና ከዘማነዊነት ጋር አብሮ መዘመን መቻልን የሚያሳይ ነው፡፡

## 4.6. የከባድ ግጭቶች ስርአተ ክዋኔ

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የሚቀርቡት የከባባድ ግጭቶች ስርአተ ክዋኔ ሂደት በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ስርአተ ክዋኔዎች ግጭቶቹ የመፈጥሩትን ከባድ የሆነ አለመረጋጋት ለመመለስ ሲባል የሚከወኑ ናቸው፡፡

### 4.6.1. የግድያ ግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ሂደት

የግድያ ወንጀል እንደ ሌሎቹ የግጭት አይነቶች ተደጋግሞ የሚከሰት አይደለም፡፡ ነገር ግን በተከሰተበት ጊዜ ሁሉ ማህበረሰቡን ከፍተኛ የሆነ አለመረጋጋት ውስጥ የሚከት ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ደግሞ በልዩ ልዩ ምክንያቶች አለመረጋጋቶች ሲገጥሙት በተለያዩ መንገዶች ለመፍታት ይሞክራል፡፡ ከነዚህ አለመረጋጋትን የመቀነሻ መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ስርአተ ክዋኔዎችን መፈጸም ነው፡፡ የጌዴኦ ብሄር አባላትንም ወደ ማህበራዊ ቀውሶች ሊከቱ የሚችሉ እንደ ዝናብ መጥፋት፣ በሽታ፣ የሰብል መጥፋት፣ እንስሳትና ሰብሎችን የሚጎዱ በሽታዎችና ነፍሳት መከሰትና የተለያዩ አይነት ግጭቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የተለያዩ አይነት ስርአተ ክዋኔዎችን ይፈጽማሉ፡፡ ስርአተ ክዋኔዎችችም አብዛኞቹ አምላካቸው አስቀምጦልናል ብለው የሚያስቡትንና በቃላዊ

ትረካዎች አማካኝነት ሲተላለፉ የመጡላቸውን ደንቦች ስለጣሱ የተከሰቱ ስለሚስላቸው የሚካሄዱ በመሆናቸው ጸጸትንና ይቅርታ ልመናን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

በብሄሩ ግድያ ሲፈጸም ጥፋቱ የአንድ ሰው ጥፋት መሆኑ ቀርቶ የገዳዩና የሟቹ ወገኖች የቀደመ ጥፋት መገለጫ ብሎም የፈጣሪ ቅጣት ተደርጎ ስለሚታሰብ ሁለቱም ወገኖች ድንጋጤ ውስጥ ይገባሉ፡፡ በመሆኑም የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች እጃቸው እንዲገባና ጉዳዩ በዚሁ መፍትሄ እንዲያገኝ በራቸውን ይከፍታሉ፡፡ የገዳይ ወገኖች ልጃቸው በሰራው ጥፋት በመጸጸት ሽማግሌዎቹን ከሟች ቤተሰቦች ይቅርታ እንዲጠይቁላቸው ይለምናሉ፡፡ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶችም ይህን የመፍታት ሃይልና የማስታረቅ ሃላፊነት ከፈጣሪ እንደተሰጣቸው ስለሚያስቡ የማረጋጋት ስራቸውን የሚጀምሩት ግድያው እንደተፈጸመ ነው፡፡

ስርአቱ ሲጀመርም የሟች የሩቅ ዘመድ የሆኑ አረጋውያንን ፈልገው 'እርቅ ይፈጸም ከኛ እናንተ ትቀርባላችሁ፤ አግባቡልን፡፡ ገዳይን እኛ ይዘነዋል፡፡ እንደገደለው እኛ እንገድልላችኋለን፡፡ ብላችሁ ቤተሰቦችን አግባቡልን በማለት ንገሩልን' ብለው ይልኳቸዋል፡፡ ለሟች ቤተሰቦች ዝምድና ያላቸው ሽማግሌዎችም ወደ ቤተሰቦቹ ሄደው አይዟችሁ የልጃችን ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም ገዳዩ እኛ ጋር አሁን ይመጣል እንቀጣዋለን እናንተ ሀዛናችሁን ጨርሱ በማለት ማረጋጋቱን ይጀምራሉ፡፡ አያይዘውም ጉዳዩ ከፈጣሪ ታዛገሮች ውሏል፡፡ እንግዲህ ሀዘናችን እንጨርስና እናስታርቅ እያሉ ያግባባሉ፡፡ በመጨረሻም ቀስ በቀስ እያለዘቡ የባሌ ባለስልጣናት እጃቸው እንዳለበት እየተናገሩ የሟች ቤተሰቦችን ለእርቅ ያግባባሉ (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

የገዳ ባለስልጣናቱ ሽማግሌዎቹን ለማግባባት የሚጠቀሙበት ቋንቋ ማለትም ገዳዩን እኛ እንገድልላችኋለን የሚለው አገላለጽ በሁለት መንገድ መታየት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በፊት በነበረው የግድያ ግጭት አፈታት ስነስርአት መሰረት በግፍ የገደለ ሰው በሞት እንዲቀጣ ይወሰንበት ስለነበር ቋንቋው ሳይለወጥ አሁንም ድረስ በዚሁ መቀጠሉን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ግን አሁንም ድረስ እየተከናወነ ያለውን ገዳይን በስነልቦናው እንዲሞት የማድረግን ጉዳይ የያዘ ነውም ልንለው እንችላለን፡፡

የገዳይን ቤተሰቦችንም ገዳይ እጁን ካልሰጠ እጁን እንዲሰጥ እንዲያግባቡትና የገደለው ወንድሙን ስለሆነ እንዲያስታርቁት ካልሆነ ግን ጦሱ በነሱ ላይም እንደሚብስ

ያስረዷቸዋል፡፡ ስለዚህ ገዳዩ በቀጥታ እጁን ለመስጠት ይመጣል፡፡ ወይም ደግሞ በጣም ከፈራና ከተጸጸተ ሰዎችን ለማየት አይን የለኝም በማለት ወደ ሀይቻዎች ሽማግሌ ይልካል፡፡ ቀጥሎም የሃይማኖት አባቶች የባሌ ባለስልጣኖችና ሌሎች የብሄሩ አባላት ለግድያ ያበቃውን ምክንያት እና የአገዳደሉን ሁኔታ አንድ በአንድ ያጣራሉ፡፡ ልዩ ልዩ ምርመራዎችንም ያደርጋሉ፡፡ ምርመራው በጣም ሰፊና ውስብስብ ነው፡፡ የምርመራው ሂደትም ሊባሻይ ወይም ምስክር መፈለግ እልፍ ካለም የሟችንና የገዳይን የቀደመ ማንነት እስከመመርመር የሚደርስ ነው፡፡ ገዳዩንም ከተደበቀበት እንዲወጣ ያደርጉና ፍርዱን እንዲቀበል ያደርጉታል፡፡ በዚህ ጊዜ የገዳይ ቤተሰቦች ለበቀል እንዳይነሳሱ ምክርና እርግማን ሲያከናውኑ የገዳይ ቤተሰቦችም ወንጀል እንዳያድበሰብሱና የበለጠ ቅጣት ከፈጣሪ እንዳይደርስባቸው አስረጅዎችን በመጥቀስ ይመክሯቸዋል፡፡

የወንጀሉ አይነትና ምክንያት በተገቢው መንገድ ከተመረመረ በኋላ ፈጻሚው አቅዶበትና በጭካኔ ከሆነ፤ ገዳዩ ከዚህ በፊትም ያለው ስነምግባር ጥሩ ካልሆነና ሟች በእንጻሩ በበጎ የሚነሳ ከሆነ ሽማግሌዎቹ በገዳይ ላይ እስከሞት ድረስ የመፍረድ ስልጣን ነበራቸው፡፡ እስከሞት ድረስ ይቀጣ የነበረው ሚኒሊክ በግዛት ማስፋፋት ጌዴኦን እስከተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስ ማለትም እስከ 1885 ዓ.ም ገደማ ነበር፡፡ አሁን ግን ጉዳዩን ዘመናዊው የፍትህ ተቋም ስለሚይዘው እንዲህ አይነት ፍርድ ሳይሆን ደም ማድረቁ ዘላለማዊ እንዲሆንና ገዳዩም ከገባበት በደም መቆሸሽ እንዲነጻ የማድረግ ስነስርአት መፈጸም ነው (ጥላሁን እብዶ፡30/05/2005 )፡፡

በጌዴኦ ብሄር የግድያ ግጭት ሲፈታም አንድ የራሱን ሰው (ጠላት ተብሎ ያልተፈረጀና የጌዴኦ ብሄር ወገን የሆነን ሰው) የገደለ ደም ሲያፈስ እንደ “ረከሰ” ስለሚቆጠር ከላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች እንዲያልፍ ይገደዳል፡፡ በዱሮ ጊዜ የግድያ ስነስርአቱ እንደተፈጸመ የአገዳደሉ ሁኔታ ተመርምሮ እንዳለቀ ነበር የደም ማድረቅ ሥነ ስርአቱ የሚፈጸመው፡፡ አሁን አሁን ግን ገዳዩ በዘመናዊው የፍትህ ተቋም የሚዳኝ በመሆኑ ፍረዱን ጨርሶ እንደወጣ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡ ይህ ስርአተ ክዋኔ በ Van Gennep ሶስት የህይወት ኡደት ደረጃዎች ጋር ይገጥማል፡፡ እነዚህን ሶስት ደረጃዎች የህይወት ኡደት ስርአተ ክዋኔ ላይ በመመራመር ቢቀምራቸውም ለሌሎች የስርአተ ክዋኔ አይነቶችም እንደሚያገለግሉ ገልጿል (Gennep,1996, 134)፡፡ የጌዴኦ ብሄር ግድያ የፈጸመ ሰው እነዚህ ሶስት ደረጃዎች ያልፋል፡፡

መጠየቅ አይፈቀድላቸውም፡፡ ምክንያቱም አንድም የሰራው ከባድ ወንጀል እንዲህ ካልነጻለት ለሱም ለዘሩም የሚተርፍ ዘላለማዊ ቅጣት ከፈጣሪው የሚያስከትል መሆኑ ስለሚታሰብ ሲሆን በሌላ በኩልም በዛ ስአት ሰዎቹ የክፉ መንፈስ ሰለባዎች ስለሆኑ ጥያቄው ከነሱ ሳይሆን ከክፉው መንፈስ የተላከ እንደሆነ ስለሚፈራ ነው፡፡

ይህ አይነቱ እጥበት ከተካደ በኋላ ወንዝ ላይ በግ ታርዶ በላዩ ላይ እየዞረ 'ጦስ በዚህ ላይ ይለፍ ጦስ በዚህ ይሂድ' እያሉ ያዞሩባቸዋል ገዳዩም ሆነ ሚስቱ ሳያዩ በጉን ደብቀው ይወስዱታል፡፡ በእጥበቱ ወቅት ከገዳዩና ከገዳዩ ባለቤት ላይ የነበረው ክፉ መንፈስ በሰዎቹ አናት በጉን ሲያዞሩት የበጉ ቅድስና እንዲያባርረው ነው፡፡ ( ቃለመጠይቅ፡አቶ ቴሮ ጃርሶ፣ 02/ 06/2005) በመቀጠልም ገዳይና ባለቤቱ አዳዲስና ውሃ ያልነካው ልብስ ለብሰው ከዚህ በፊት ለብሰውት የነበረውን ማንኛውንም አይነት ልብስና ጌጣጌጥ በሙሉ ለፉጋዎቹ ይሰጧቸዋል፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ጥያቄ ይነሳል፡፡ ይሄውም በጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታትና የባሌ መዋቅር ውስጥ ስልጣን የማይሰጣቸው የእደጥበብ ባለሙያዎች በገዳዩና በገዳዩ ባለቤት ላይ አደረ የተባለውን ክፉ መንፈስ እንዴት ሊያስወጡት ይችላሉ? የሚለው ነው፡፡ ይህን አስመልክቶም በቃለመጠይቅ ወቅት ያገኘሁት መረጃ እንደሚያሳየው ፉጋዎች ክፉ መንፈስ የማይፈሩና ክፉ የተባለው መንፈስም በነሱ ላይ ሀይል እንደሌለው የሚጠቁሙ ናቸው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ፣ 20/08/2008)፡፡

#### 4.6.1.2. ሽግግር

በሁለተኛው ወይም በሽግግር ደረጃ ሰውየው ከማህበረ ባህላዊው ሁኔታ በራቀ መልኩ እንግዳ እንዲሆን የሚደረግበት ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ጊዜ እያንዳንዱ ስምምነት የተካሄደበት ድርጊት ሁሉ ይፈጸምበታል፡፡

የመንጻት ስነስርአቱ እንደተጠናቀቀ ከክፉ መንፈሱ የተፈወሰው ገዳይ ወደ ሁለተኛው የሽግግር ደረጃ ይሄዳል፡፡ በዚህም መጀመሪያ የሚሄደው ሽማግሌዎችና የሟች ቤተሰቦች ተሰብስበው ወደሚገኙበት ቦታ ማለትም ወይ ወደ ገዳይ ቤት ወይ ወደ ሟች ቤት ወይም ሰውየው ወደተገደለበት ቦታ ነው፡፡ በዚያም የሟች ቤተሰቦችና የሀገር ሽማግሌዎች ተቀምጠው ይጠብቋቸዋል፡፡ አቀማመጣቸውም ተራርቀው ወይም በመካከላቸው ክፍት ቦታ ትተው ነው፡፡

በእርቅ መፈጸሚያው ቦታ በቅድሚያ የሚካሄደው ስነስርአት ፋጫ[14] የማውጣት ስነስርአት ነው፡፡ ፋጫ አውጡ ይባላሉ፡፡ ሟችን ለሞት ገዳይን ደም ለማፍሰስ የዳረገው ምንድን ነው? ምን የሰራችሁት ሀጢያት አለ? በቤተሰብ ብድር ያልመለሰ፣ ሰውን የበደለ፣ የሰረቀ ወይስ ክፉ ያደረገ ሰው አለ? በማለት ይጠይቋቸዋል፡፡ ይኸኔ በሁለቱም ወገን በድብቅ የሰሩትን ወይም ባለማወቅ ያደረጉትና ከዚህ በፊት ያልተከሰሱበት ወይ የደበቁት ነገር ካለ ሳይፈሩ ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም አሁን እያስታወሱ ካልተናገሩ ጦሱ ድጋሚ አይለቀንም ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡

ይህ ስነስርአት የራሱ የሆነ ማህበረፖለቲካዊም ሆነ ግለሰባዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ማለትም አንድ ሰው ባለማወቅም ሆነ እያወቀ የፈጸመውና በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ሀጢያት የሚቆጠር ወይም ወንጀል ተብሎ የተፈረጀ ጉዳይ ካለ ስነልቦናዊ እረፍት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ይህ ስነስርአት ሲካሄድ ጉዳዩን ለእምነትና ለፖለቲካ መሪዎች ሲናገረ የሚሰጠው ስነልቦናዊ ጽዳት ቀሪ ህይወቱን ከወንጀልና ከጸጸት ነጻ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ስለዚህ ፋጫ የማውጣት ስነስርአትን ለጌዴኦ ብሄር አባላት ወንጀለኛን ከማንጻት ወደ ማህበረሰብን ማንጻት የሚያሳድግ የስርአተ ክዋኔው መዋቅር ነው ልንለው እንችላለን፡፡ በሌላ በኩል በህበረተሰቡ ውስጥ ተደብቆ የቆየን ወንጀልና ወንጀለኛ የሚያጋልጥ በመሆኑ በሰዎች መካከል የሚኖርን በጥርጣሬ የመተያየት ሁኔታ ያረግበዋል ማለትም ይቻላል፡፡ ፋጫ የማውጣት ስነስርአት ወንጀልን መናዘዝ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ ወንጀልን ላለመፈጸም ቃል የመግባት ስነስርአትን ያካተተ መሆኑም የሚፈጸሙ ወንጀሎችንም ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን የወንጀል ስጋት የሚቀንስ ነው፡፡

ፋጫ የማውጣት ስነስርአቱ እንደተገባደደ የገዳዩ አባት ወይም አንድ የእድሜ ባለጸጋ የገዳይ በር ላይ በግ አርደው ደሙን ሶስት ቦታ ላይ ያፈሱታል፡፡ ከዛም የበጉ ቆዳ ከእግሩ አካባቢ ተገፎ በቆዳው የነብሰ ገዳዩ እጅ ይታሰርና ይቀመጣል፡፡ ነብሰ ገዳዩ እጁን እንደታሰረ ሁሉም ታዳሚ እንዲያየው ይደረግና ምርቃት አዘል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ ይሄውም ሁለተኛ እጁ ስለት ድንጋይና ዱላ እንዳያነሳ፡፡ ታሰር እስረኛ ነህ፣ እጅህን አምላክ ይጠብቅልህ በማለት ይገስጹትና ይፈቱታል፡፡ የታረደው በግ ቆዳው ተገፎ እስኪያልቅ ድረስ ለብቻው ይቀመጥና እንዳለቀ ቆዳውን ለብሶ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ይህ

---

[14] ፋጫ የማውጣት ስነስርአት ማለት ሀጺያትን መናዘዝ ማለት ነው፡፡ ይህ ስነስርአት አንድ ሰው የፈጸመውን ስሁተት እንዳይጸጽተው እና ሁለተኛ እንዳይግመው ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡ በዚህ ስነስርአት ማንኛውም ሃጺያት ይቅር ይባላል፡፡ ይቅርታውም ከእምላክም ከሰውም ወገን እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከፋጫ ተነስቶ ቂም የሚይዝ ወገን ተጎጅ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ማንኛውም ሰው ቢሆን ያለፍርሀት የሰራውን ክፉ ነገር ይናዘዛል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን በፋጫ ማውጣት ስነስርአት ወቅት አንድ ሰው ሰው ምን ይለኛል ብሎ ወይም በትእቢት ፋጫ ሳያወጣ ቢቀር የሰራው ሀጺያት ከሱም አልፎ በዝርያው ላይ ከባድ ቅጣት የሚያመጣ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

የሚደረገውም የተገደለ(በሰው እጅ የታረደን) በግ ቆዳ ለብሶ መቆሙ እንድም እሱም ከዚህ በኋላ በሰዎች ፊት እንደሞተ ሰው እንጅ በህይወት እንዳለ እንደማይቆጠር እንድም እርጥብ ቆዳ መልበስ ክብርን የሚነካ በመሆኑ የገዳዩን ስሜት ለመጉዳት ነው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

ከዛም የተወሰኑ ሰዎች ገዳዩ እጁ ታስሮበት የነበረውን ቆዳ ይዘው ምንጊዜም የማትደርቅ ለምለም ተክል ላይ ለማሰር ይሄዳሉ፡፡ ይህም ያጠፋው ነፍስ እንደ ተክሏ እንዲለመልም ነው፡፡ በሌላ በኩል ሽማግሌዎቹ የሟችን ቤተሰቦች እንደ ተክሏ ለምልሙ፣ አትክስሙ፣ ልጃችሁ ቢገደልም ዘራችሁ አይጥፋ ደጋግማችሁ ብቀሉ በማለት ሲመርቁ በተመራቂዎቹ ውስጥ የበለጠ ተስፋን የማጫር አላማ ሊኖረው ስለሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም ይህች ተክል የቃል ኪዳንና የአምላክ ድንቅ ስጦታ እንደሆነች ስለምትታመንና በየትኛውም አደገኛ ጊዜ ቢሆን የማትጠፋ የአምላክ በረከት የማይለያት ነች ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለገዳዩ የምህረት ቃል ኪዳን ለሟች ቤተሰብም የመልካም ምኞት መግለጫ ትደረጋለች ( ቃለመጠይቅ፣አቶ ቴሮ ጃርሶ፣ ገደብ፣ 02/ 06/2005)፡፡

እነኚህ ስነስርአቶች የሚደረጉት ለሟች ቤተሰቦች መልካም ምኞትን ለመግለጽ ለገዳይ ቤተሰብ ደግሞ ጸጸትን ለመስጠት ነው፡፡ ይህም በገዳይ ላይ ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርስበት ነው፡፡ የመንጻት ስነስርአቱ ከመገባደዱ በፊት በጉ እንደታረደ ሶስት ቦታ ላይ የፈሰሰው ደም ላይ ገዳዩ ሶስቴ ወደፊት እየሄደ ወደ ኋላ ይመለስና ሶስተኛውን በፊት ለፊቱ ሄዶ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ ከዛ በኋላ ከገባበት ሀጺያት ነጻ ነው፡፡ የእርኩስ መንፈስ ሰለባነቱና ለማህበረሰቡ ስጋትነቱ ሙሉ በሙሉ ባይጠፋለትም በጣም ይቀንስለታል፡፡ እነዚህ ሁሉ የሽግግር ሂደት ደረጃዎች ሰውየው የገባበት ወንጀል ጨርሶ ከሱ እንዲወገድና ተመልሶ ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖር በማሰብ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡

እጅን በበጉ ቆዳ መታሰር፣ የበጉን ቆዳ ለብሶ እንዲቆም መደረግ፣ እጁ የታሰረበትን ቆዳ ለምለሟ ዛፍ ላይ ለማሰር መሄድ የመሳሰሉት ሰውየውን የነበረበትን የፍጹም ጸጸትና የጥፋተኘነት ስሜት በአንድ በኩል የበለጠ የሚያባብሰው ሲሆን በሌላ በኩል ግን እስካሁን ከሰው ጋር አብሮ የመብላት፣ በነጻነት የመውጣትና የመግባት፣ ምግቡን እንደሰው ሳይሆን እንደእንስሳ የመቀበሉን ሁኔታ የሚያስቀርለት መሆኑ ለነብሰ ገዳዩ እፎይታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

### 4.6.1.3. አዲስ ማንነት ማግኘት

በGennep ባለሶስት ደረጃ መዋቅር መሰረት የመጨረሻው የእንድ ውስን ሪቹዋል ሶስተኛው ደረጃ አዲስ ማንነትን ማግኘት ነው፡፡ ሶስተኛው የሽግግር ደረጃ ሰውየውን ወደአዲሱ ማንነቱ እንዲመጣ የሚደረግበት ሂደትን የሚገልጹ ትእምርቶች የሚካዱበት ነው፡፡ በዚጊዜ ስርአተ ክዋኔው የሚፈጸምለት ሰው አዲስ ስምና መለያ ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ሂደትም በባህሉ አመጋገብስነስርአትመሰረት ምግብ ይቀርባል፡ በዚህ ደረጃ ላይ ነፍሰ ገዳዩን ወደ ማህበረሰቡ የመቀላቀል ተግባራት የሚከወኑ ይሆናል፡፡ስለዚህ የባሌ ባለስልጣናትና የሃይማኖት አባቶች በጋራ ሆነው ይህን የእርቅ መፍታት ሂደት ሲያከናውን የነበረን አምላክ በማመስገን ወደ ምግብ ስነስርአት ይሸጋገራሉ፡፡ የታረደው በግም ይጠበስና በባሌ ስርአት ቀዳሚውን ሹመት የያዙት ሰዎች በመጀመሪያ ይቀምሱታል፡፡ በመቀጠልም ገዳይና የሟች ቅርብ ዘመድ እንዲጎራረሱ ተደርጎ መብላት ይጀመራል፡፡ ምግቡ ተበልቶ ሲያልቅም የሟች በጣም ቅርብ ዘመድና ገዳይ ከንጹህ ማር የሚሰራውን የጌዴኦ ብሄር ጠጅ (ቦካ) በአንድ ዋንጫ እንዲጠጡ ይደረጋል፡፡ ቦካ በብሄሩ አባላት ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የክብር ደረጃ የሚሰጠው የመጠጥ አይነት በመሆኑና በአንድ ዋንጫ መጠጣታቸው ከጥላኝነት ወደመልካም ወዳጅነት የሚያሸጋግራቸው ነው፡፡ በአንድ ዋንጫ ቦካ ከመጠጣቱ በመቀጠልም የገዳይ ወገኖችና የሟች ወገኖች ሙሉ በሙሉ እንደታረቁና ቂም በቀል ቢያስቡ አምላካቸው ቅር እንደሚሰኝባቸው ይነገራቸውና ሴሮ(ደንብ) ተደርጎ ይታረቃሉ፡፡ ሴሮውም ከዚህ በኋላ ደንብ አፍርሶ ቂም በቀል የሚያስብ ሰው ቢኖር አምላክ ይቅር አይበለው፣ ዘሩን ብኩን ያድርግበት የሚል ነው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

ከእርቁ ሂደት መጠናቀቅ በኋላ ግን ነፍሰ ገዳዩ አዲስ ስምና ማንነት ይዞ ይቀራል፡፡ ይሄውም እጁ ያለፈ(ነፍሰ ገዳይ) የሚል ነው፡፡ ከዚህም ጋር በርካታ የሆኑ ማህበራዊ መስተጋብሮቹ አዲስ ቅርጽ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ እነሱም እንደ ሙሉ ሰው ሳይሆን እንደ ጎደሎ ክፉ መንፈስ ማደሪያ ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ቀድሞ ምንም ያህል የተከበረ ቢሆን አሁን ይቀላል፤ ሁሉንም ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ይነፈጋል፡፡ ማለትም በባሌ ስርአት አርከን አይመረጥም፣ ሸንጎ ላይ እርጥብ ቅጠል አይነጠፍለትም፣ ምንም አይነት ሃሳብና ውሳኔ መስጠት አይችልም፣ እንዲያውም ቢችል ወደሸንጎ ክልል እንዳይገባ ይደረጋል፡፡

ትላልቅ ጸሎቶች ማለትም የደራሮ [15] በዓል አከባበር፣ ለልዩ ልዩ ሰቆቃዎች ማስታገሻ ተብለው በሚዘጋጁ ጸሎቶች አይሳተፍም፣ ማንም ሰው ቅቤ እንዲቀባውም ሆነ እሱ ማንንም ቅቤ እንዲቀባ አይደረግም፡፡ ብዙው ሰው በህይወት እንዳለ ሰው አይቆጥረውም፡፡ ሲሞት የሚቀብሩት ሶስት የቅርብ ዘመዶቹ ብቻ ናቸው እንጅ ማንም መጥቶ ለቅሶው አይደምቅለትም፡፡ እንዲሁም እንደማንኛውም ሰው እኩል ተዝካር አይወጣለትም፡፡ ሲጠራም ከራሱ ስም ይልቅ በቤተሰቦቹ ወይ በልጆቹ ካለዚያም ሰው የገደለው የሚለው ተቀጽላ ይሆናል፡፡ ይህም ፍጹም ስነልቦናውን የሚጎዳ ስለሚሆን ጎስቋላ ኑሮ እንዲገፋ ሊያደርገው ይችላል፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ቢያማርሩትም ምንም አይነት እርምጃ ሊወስድ አይሞክርም፡፡ ምክንያቱም አንዳች እርምጃ እንዳይወስድ የሽማግሌዎቹ ግዝት ያስረዋል፡፡ ይህን ሁሉ ጥሶ ግን አንዳይነት እርምጃ እወስዳለሁ ቢል የሱ ጦስ ዘር ማንዘሮቹን ይጎዳል ተብሎ ስለሚታመን ከቻለው አብሮ መኖር እጅግ ከከበደው ግን ሀገር ለቆ ይጠፋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/ 05/ 2005)፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የአዲሱ ማንነቱ መገለጫዎች ቀጣይ እድሜውን ሙሉ የሚከተሉት በነብሰገዳይነቱ ምክንያት የተሰጡት አዳዲስ ማንነቶቹ ናቸው፡፡

#### 4.6.2. የጎሳ ግጭት አፈታት ስርአተ ከዋኔ

የጎሳ ግጭት በጌዴኦ ብሄር የተለመደ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአንድ ወንድማማች ልጆች ነን ብለው ማመናቸው፤ በጌዴኦ አዳያአ ታላቁ ሸንጎ መማማላቸው እንዲሁም አሁንም በጋብቻና በቤተዘመድ አማችነት መተሳሰራቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ነገር ግን በ1999ዓም ሎጎዳና ደራሻ ጎሳዎች ተጣልተው ያውቃሉ (ቃለመጠይቅ ፣ተካ ቦሩ፣ 26/05/2005)፡፡ ይህ ግጭት የተፈጠረው በተራ አለመግባባት ይሁን እንጅ እስከ ደም ማፋሰስ የደረሰ ነበር፡፡

ግጭቶቹ እንደተከሰቱ የአካባቢው ሸንጎ ሃይቻዎችና ሌሎችም እየገሰጹ ለማብረድ ሞክረው ነበር ነገር ግን ግጭቱ በተገቢው መንገድ ቁጥጥር ስላልተከናወነበት በየጊዜው በማገርሸት ከፋተኛ የሆነ ውድመት አድርሷል፡፡ በመጨረሻ ግን ግጭቱ እንዲበርድና በወንድሙ ላይ ነፍጥ ያነሳ የጎሳን አባል ገስጸው አባገዳው በመከልከላቸው ግጭቱ ቆሟል፡፡ የግጭቱን ምክንያትና ዘላቂ መፍትሄውንም ለመጠቆም ሽማግሌዎቹ መሬት ላይ እየተቀመጡ አምላካቸውን እየተማጸኑና ለወረደው የእርስ በእርስ ግጭት ይቅርታና ሰላምን በጸሎት እየተማጸኑ ለማርገብ ሞክረዋል፡፡ በመጨረሻም ከሁለቱም ወገን የሆኑና ከሁለቱም ወገን

---

[15] ደራሮ የጌዴኦ ዘመን መለወጫ በአል ነው፡፡ በዚህ በአል በየትኛውም የእድሜ ክልል የሚገኝ የብሄሩ አባል የሆነ ሰው ሁሉ ለአባ ገዳው ከየአመረቱት ምርት ግብር ያስገባሉ፡፡ በምላሹም ምርቃትና በረከት ይዘው እንደሚመለሱ ያስባሉ፡፡ በጸሎትና ብአል በማክበሩ ስነስርአት መገኘትንም እንደልዩ በረከት ይቆጥሩታል፡፡

ውጭ የሆኑ በአይናቸው ያዩ ሰዎች እየማሉ ምስክርነት እየሰጡ ለረዥም ጊዜ የቆየ ምርመራ ተካሂዶ በደሉ የአንድ ወገን ወይም መሰረታዊ የጥቅም ግጭት ያለመሆኑን መረዳታቸውን ገልጸዋል፡፡ በስሜታዊነት ተነሳስቶ በእጁ ነፍስ የጠፋበት ሰው በህግ ቁጥጥር ስር ስለዋለ ሲመለስ የመንጻት ስነስርአት እንደሚፈጸምለት ገልጸዋል (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ቱሮ ጃርሶ፣ 02/ 06/ 2005)፡፡

የሁለቱ ጎሳዎች ግጭት አፈታትን ስነ ስርአትን በሚመለከት ደግሞ በመጀመሪያ ከተጣሉት ጎሳዎች መካከል ከአምስት ሰዎች በላይ ለግጭት አፈታቱ ይመረጣሉ፡፡ ከዛም ከሁለቱም ጎሳዎች በተውጣጣ ገንዘብ አንዲት መውለድ ያቆመች ላም እና ልዩ ልዩ ባህላዊ ምግቦች እና መጠጦች ይቀርባሉ፡፡ ከዛም አባገዳው እና ካቢኔዎቻቸው እንዲሁም የሀይማኖት አባቶች በአንድ ላይ ሆነው ጸሎት እና ምርቃት ያከናውናሉ፡፡ ከዛም ላሚ ታርዳ ከጎድን አጥንቱ አንዱ በሁለቱ ተጋጭዎች መካከል እንዲሰበር ይደረጋል፡፡

በዚህ ስነስርአት ወቅትም እናንተ የአንድ አጥንት የአንድ ደም ልጆች ናችሁ ለምን ትጣላላችሁ? የእናንተን ጥል የሚፈልገው ወንድም የወንድሙን ደም እንዲያፈስ አጥንቱን እንዲሰብር የሚያደርግ አጋንንት ከመካከላችሁ ይራቅ፡፡ ለአጋንቱ ይሄው የማትወልደውን ላም ደም ፈሶለታል አጥንቷንም ሰብረንለታል ስለዚህ ከናንተ ይራቅ እናተም የሰበራችሁት የወንድማችሁን አጥንት ነውና ፈጣሪ ይቅር ይበላችሁ፡፡ በማለት የታረደችው ላም ስጋዋ ይጠበሳል፣ ድግስም ይሆንና ከሁለቱ ጎሳዎች፣ ከገዳ ካቢኔዎችና ከሃይማኖት አባቶች የተውጣጡት አስታራቂና ጥለኞች በጋራ ይበላሉ፡፡

በመጨረሻም ከሁለቱም ወገኖች አንድ አንድ ተወካይ ይመርጡና ከተጠበሰው ስጋ ላይ ይጎራረሳሉ፡፡ ድጋሚ እንዳይጋጩም ተማምለው በአንድ ዋንጫ ቦካ የተባለውን ከማር የተሰራ ጠጅ ነገር ይጠጣሉ፡፡ ይህም እርቁ ሁልጊዜ እንዲኖር የሚያደርግ ጉዳይ ነው ተብሎ ይታመናል (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

### 4.6.3. የብሄር ለብሄር ግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ

የጌዴኦ ብሄር ከሁለቱ አጎራባች ብሄሮች ማለትም ከጉጅና ከሲዳማ ጋር በልዩ ልዩ ምክንያቶች ተጋጭቶ ያውቃል፡፡ ከሲዳማ ጋር በጣም በጥንት ጊዜ እንደተጋጩ የሚነገር ሲሆን ከጉጅ ጋር ደግሞ በ1995 ዓምና በ1998 ዓም ተጋጭተዋል፡፡ እነዚህ ግጭቶች በጌዴኦ ብሄርም ሆነ በሲዳማና ጉጅ ብሄሮች ውስጥ አሰቃቂ ሊባል የሚችል ጥፋት ያደረሱ

ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች የሚፈቱት በጎንደሮ ስርአትና ልዩ ልዩ የእርግማን ስርአተክዋኔዎችን በመፈጸም ነው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

ከሁለቱም(ሲዳማና ጉጅ) ጋር የሚፈጠረው ግጭት መነሻው የግለሰቦች አለመግባባት ከሆነና ከጌዴኦ ወይም ከተጋጭው ወገን የነፍስ መጥፋት ከተፈጠረ ጉዳዩ ሳይባባስ እርቅ እንዲፈጸም ከሁለቱም ወገን ሽማግሌ ይጠራል፡፡ በቡድን ወይይት ወቅት እንደተረዳሁት ግጭቱም የሚፈታው በጌዴኦ በኩል ከንጹህ ማር የሚሰራውን ቦካ በማቅረብ ሲሆን በጉጅ ወይም በሲዳማ ወገን ደግሞ ለእርድ የሚሆን ከብት ወይም በግ በማቅረብ ይሆናል፡፡ ይህ የሆነበት ምክኒያትም ጌዴኦ አርሶ አደርና ንብ አናቢ በመሆኑ የተነሳ በቀላሉ ማቅረብ የሚችለው ከማር የሚሰራውን ቦካ ሲሆን አጎራባቾቹም አርብቶ አደር በመሆናቸው ማቅረብ የሚችሉት በቀላሉ ማግኘት የሚችሉትን በግ ወይም ከብት ነው፡፡ አሁን አሁን ለእርቅ ማስፈጸሚያ የሚሆነው  አብዛኛው ወጭ የሚሸፈነው በመንግስት ሆኗል፡፡ እነዚህ ምግብና መጠጦች ከቀረቡ በኋላ በሁለቱም በኩል የየብሄሩ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም ባህላዊ አስተዳዳሪዎች በተገኙበት የጎንደሮ ስርአት ይፈጸማል (ቃለመጠይቅ፣ ጥላሁን እብዶ፣ 30/05/2005)፡፡

በሌላ በኩል በብሄሮቹ መካከል የተፈጠረው ግጭት በግለሰብ ሳይሆን በብሄሮች መካከል ሆኖ ጥሉ በሁለቱም ብሄሮች የእርስ በእርስ ጦርነት የሚያስከትል ከሆነ በጌዴኦ ብሄር በኩል የሚደረገው አምስት አሮጊቶችን በመምረጥ ጦርነቱ በሚካሄድበት ደንበር አካባቢ እንዲጮሁ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያት በሶስቱም ብሄሮች ሴቶችን መግደል የተወገዘ በመሆኑ ማንም ስለማይገድላቸው ነው፡፡ በኋላም ሴቶቹ ከጌዴኦ ብሄር የላኩትን የሰላም መልእክት ለዛኛው ወገን በማድረስ ምልሽ ይዘው ይመጣሉ፡፡ ያኛው ወገን ለእርቅ ዝግጁ ከሆነ የሁለቱም ወገን አባገዳዎችና የሃይማኖት አባቶች በተገኙበት እርቅ ይከናወናል፡፡

በእርቁ ወቅትም ከብትና ቦካ ይቀርብና በሁለቱም አባገዳዎች ከብቷ እንድትታረድ ትደረጋለች፡፡ ከዛም ከከብቷ የሚወጣውን ደምና ቦካውን በመቀላቀል አንድ ላይ ከየብሄሩ ለእርቅ በተመረጡት ሰዎች ጭንቅላት ላይ ይደፋታል፡፡ ይህ የሚደረገውም ተጋጭዎች ከገቡበት ሃጢያት ለማንጻት ነው፡፡ ሌላው ትእምርታዊ ጉዳይ ከላሟ አንዱን የጎድን አጥንት በመውሰድ የሁለቱም ወገኖች አባገዳዎች በቢላዋው የማይቆርጥ ክፍል በአንድ ላይ በመስበር ነው፡፡ ይህም ሁለቱን ወገኖች እልህ የሚያጋባውን የእልህ አጋንንት ለማስወገድ ነው፡፡ በቢላዋው ጀርባ ወይም በማይቆርጠው ክፍል አጥንቱን የመስበራቸው ምክንያት

ደግሞ ስለት መጥፎ እንደሆነ ለማሳየትና የሚሰበረው አጥንትም የሁለቱን ተጋጭዎች የአንድ አጥንት ልጅነት(ወንድማማችነት) የሚወክል በመሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻም የታረደችውን ላም ስጋ በአንድ ላይ በመጥበስ አብረው እንዲበሉና ቦካውንም የሁለቱ ብሄር ተወካዮች በአንድ ላይ እንዲጠጡ በማድረግና የሁለቱም ብሄሮች የሀይማኖት አባቶች ምርቃት አድርገው የሚቋጩት ነው (የቡድን ውይይት፣ ቡሌ ወረዳ፣ 20/08/2005)፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የጌዴኦ ብሄርን የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ያሣየ ነው፡፡ በመሆኑም ይዞት የተነሳው ዋና አላማ የጌዴኦን ብሄር የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔን አውዳዊ ትንተና በማካሄድ ብሄሩ ለግጭትና ለግጭት አፈታት ያለውን ግንዛቤ መመርመር ነው፡፡ በአጠቃላይ ብዙ ጊዜ በጌዴኦ ብሄር ባህላዊ የፍትህ መስጫ ተቋም ቀርበው መፍትሄ የሚያገኙት ግጭቶች ማስረጃ የሌላቸው ግጭቶች ናቸው፡፡ በምልከታና በቃለመጠይቅ የተገኙትን የግጭት አይነቶች በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚያስከትሉት የቀውስ መጠን፤ ከማህበረሰቡ የእሴት አይነትና ግጭቶችን ከሚፈቱት ተቋማት በመነሳት ቀላል ግጭቶች፣ መካከለኛና ከባድ ተብለው ይታወቃሉ፡፡

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ብዙ ጊዜ ከሚፈጠሩት ቀላል ግጭቶች ውስጥ የቤተሰብ ግጭትና በጎረቤታሞች አማካኝነት የሚከሰቱ ግጭቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች ቀላል በመሆናቸው መፍትሄ የሚያገኙትም በቤተሰብ ጉባዔና በአካባቢ ሽማግሌዎች ነው፡፡ ግጭቶች ሲፈቱም አብሮ ከመብላትና ከመጠጣት ለበደሌ ይቅርታ አድርጊልኝ ከመባባል የዘለለ ስርአተ ክዋኔ አይኖርም የተለየ ምግብና መጠጥም አይቀርብም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የግጭት አይነቶች መካከል ከበድ ያሉ ስርቆቶች፣ የድንበር መገፋፋት፣ ብድርን መካድ፣ ድብደባና አካል ማጉደል ዋና ዋና የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች ከአካባቢ ሶንጎዎች እስከ አባ ገዳ ድረስ ሊያደርሱ የሚችሉ ግጭቶች ናቸው፡፡ በግጭቶቹም የሚደርሰው የጉዳት መጠን ከፍ ያለ ስለሚሆን ግጭቶችን ለመከላከል ከተፈጠሩ በኋላም ለመመርመርና መፍትሄ ለመስጠት የተለያዩ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች ይከወናሉ፡፡

በዚህም መሰረት ፈጻሚው ያልታወቀ ስርቆት ሲፈጸም ሌባው ባለበት ሆኖ ጉዳት እንዲደርስበት የመርገም ስነስርአት ይፈጸማል፡፡ በድንበር አማካኝነት የሚፈጠርን ግጭት መፍትሄ ለመስጠት የላንጤ ተከላ ይከናወናል፡፡ ይህም ለሁለት አላማ ሲሆን አንደኛው ላንጤ እምነታዊ ትእምርት ያለው ተክል ስለሆነ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ላንጤ የማይጠፋና ስር የማይሰድ ስለሆነ የድንበሩን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ መፍትሄ ለመስጠት የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡ ብድርን መካድ በተለያዩ ጊዚያት ለብሄሩ ሸንጎ የሚቀርብ ግጭት ሲሆን የሚፈታውም ተበዳሪ ነው የተባለን ሰው በማስማል ስነስርአት ውስጥ ነው፡፡ ሌላው በጌዴኦ ብሄር የሚፈጠር የግጭት አይነት ድብደባ ነው፡፡ ይህን

ግጭት ለመፍታትም በመጀመሪያ ቁስል የማድረቅ ስርአትና ክዋኔ ከተካሄደ በኋላ ጎንደሮና ሴሮ በማድረግ የእርቅ ስነስርአት ይከናወናል፡፡

ከባድ ግጭት ደረጃው ላቅ ያለና ከባድ የሆነ ስነልቦናዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚያስከትል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የጌዴኦ ብሄር አባላት ከባድ ግጭት ብለው የሚፈርጁቸው ነብስ ማጥፋት፣ የጎሳ ለጎሳ ግጭትና የብሄር ግጭት ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በአጥፊውም ወገን ሆነ በበዳይ ወገን የሚያደርሱት አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት በጣም የከፋ ስለሚሆን የብሄሩ ባህል በሚያዘው መሰረት የተለያዩና ውስብስብ የሆኑ ስርአተ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፡፡ የሚፈጸሙት ስርአተ ክዋኔዎችም ወንጀልን ለመመርመር፣ ወንጀለኛን ከፈጸመው ሀጢያት ለማንጻትና ተበዳይንና የተበዳይን ወገን በስነልቦና ለማረጋጋትና ለመካስ የሚካሄዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ስነ ስርአቶችና ክዋኔዎችም የራሳቸው የሆነ ፋይዳና መዋቅር ያላቸው ባህላዊና እምነታዊ ድርጊቶችንና ስነ ስርአቶችን የያዙ ናቸው፡፡

በጌዴኦ ብሄር ግጭቶች የሚፈቱት እንደ ግጭቶቹ ደረጃ ከአባወራ እስከ አባገዳ ባለው የስልጣን መዋቅር ነው፡፡ ግጭቶችን ለመፍታት ሚና የሌላቸው የማህበረሰቡ ክፍሎችም ሴቶችና በእደጥበብ የሚተዳደሩት የማበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ የጌዴኦ ብሄር ግጭቶችን የመፍታት ሚና ካላቸው ተቋማት መካከል የቤተሰብ ጉባኤዎች፣ የአካባቢ የገር ሽማግሌዎችና፤ አካባቢያዊ ሶንጎዎች፣ የሮጋ ሶንጎዎች፣ ጠቅላላ ሶንጎዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት እንደቀረቡበት ቅደም ተከተል የሚፈቱት የግጭት አይነትም ሆነ የሚሰጣቸው የተቀባይነት ሁኔታ ይለያያል፡፡ ከላይ የቀረቡት የብሄሩን ፖለቲካዊ ማህበራዊና ባህላዊ ድርጊት የሚመሩ የብሄሩ ወሳኝ ሰዎች ስልጣናቸውን ከፈጣሪ የሚያገኙትና የመምራት ጥበብና ግጭት የመፍታት ሀይል ከሰማይ አምላክ(ማጌኖ) የተቸራቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለዚህ የተናገሩት አንዱም ሳይቀር የሚፈጸም ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህም በብሄሩ አባላት ዘንድ ውሳኔያቸውን የሚከበር ያደርግላቸዋል፡፡

የጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ በሚል በተጠናው ጥናት የሚከተሉትን ጉዳዮች እንደ ግኝት መውሰድ ይቻላል፡- በጌዴኦ ብሄር አባላት ግጭቶች ተፈጥሯዊ የሆኑና በጎና እኩይ ውጤቶች እንዳላቸው ሁኔታዎች ሳይሆን ከከፉ መንፈስ የሚላኩና ከዚህ በፊት በተሰራ ሀጢያት ምክንያት የሚመጡ የአምላክ ቁጣ መገለጫዎች እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በመሆኑም መፍትሄ እንዲያገኙ የሚጠበቀው በአምላክ ትእዛዝ ስር ናቸው ተብለው በሚታመንባቸው ሃዩ (የሃይማኖት አባቶች) እና ወዩ (የገዳ ባለስልጣናት) ነው፡፡ ግጭቶች ሲፈቱም ሆነ ሲፈጠሩ ጸሎቶችን ማካሄድ፣ ከሃዩዎችና ከወዩዎች በረከትን

ገመሻት ምርቃትን መቀበል፣ ጥፋቱን የካደንና የብሄሩን እሴት ያላከበረን ሰው በመርገም ለሌሎች መቀጣጫ ማድረግ የመሳሰሉ ሪቹዋላዊ ድርጊቶችን መፈጸም ነው፡፡

የእርግማንና የምርቃን ሪቹዋሉም በማህበረሰቡና በባለስልጣኖቹ መካከል የደረጃ ልዩነት መዋቅር የሚያበጅ ነው፡፡ ይህ ድንበርም ባለስልጣኖቹና የሃይማኖት አባቶቹ ከሰማይ አምላክ(ማጌኖ) የሚሰጣቸውን እርኩስ መንፈስ የማስወጣትና የማዘዝ ስልጣናቸውን ተጠቅመው አቅማቸውን ማሳየት የሚችሉበትን ደረጃ ማስጠበቅ ሲሆን ተራው ህዝብ ደግሞ አኗኗራችንን ይረብሽብናል ብለው የሚያምኑበትን ክፉ መንፈስ ለማራቅ ያላቸው ጉጉት ለባለስልጣናቱ ትእዛዝ እንዲመሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ የደረጃ መዋቅርም በጌዴኦ ብሄር ውስጥ ስናየው ማህበረሰቡን የማረጋጋትና ግጭቶችን የመቆጣጠር ሚናው ከፍ ያለ ሆኖ እንገኘዋለን፡፡ መዋቅሩ ጸንቶ እንዲቀጥልም ልዩ ልዩ ዝርው ቃል ተረኮች የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በተለይም እውነተኛ ናቸው ተብለው የሚነገሩት የእብነት ታሪኮች የባለስልጣናቱን ስልጣን የሚያጸኑ ማህበሩ ደግሞ የበለጠ እንዲያምን የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በጌዴኦ ብሄር ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚካሄደው ስርአተ ክዋኔ ከብሄሩ ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች(እምነታዊ፣ ስነቃላዊ፣ አስተዳደራዊ ወዘተ.) ጋር መግጠሙ የግጭት አፈታት ሂደቱን ዘመን ተሻጋሪና ከዘመናዊው የፍትህ ተቋም ጋር ሲነጻጸር በብሄሩ አባላት ዘንድ የበለጠ ተአማኒ የሚያደርገው ነው፡፡

በዚህ ጥናት የጌዴኦ ብሄር ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔን በማጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አግንቻለሁ፡፡ በጥናቴ ወቅት ካጋጠሙኝ ተግዳሮቶች መካከል ጊዜን፣ ገንዘብንና ቋንቋን የሚመለከቱት አብይ የሚባሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም በሌላ የፎክሎር ጥናት የብሄሩ አባላት መግባቢያ የሆነውን ቋንቋ በመልመድ፣ ሰፊ ጊዜ ተወስዶ አብሮ በመኖርና ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ የሆነ ምልከታን በማካሄድ ቢሰራ ከዚህ የተሻለ የብሄሩን እውቀትና ፍልስፍና መረዳት እንደሚቻል አምናለሁ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት የይሁንታ ሃሳብ ከኔ ቀጥሎ የጌዴኦ ብሄር ባህል ላይ ጥናት ለማድረግ የሚያስብ አጥኚ ከላይ ላነሳኋቸው አብይ ተግዳሮቶች መፍትሄ ቢያጅ በተሻለ መልኩ የብሄሩን እውቀት ሊገልጽ ይችላል የሚል ነው፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ምንዳ ገብሬ፡፡ "የጌዴኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ተረኮቻቸው" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 1998ዓም፡፡

ታደሰ ክጴና ሌሎችም፡፡ የጌዴኦ ብሄር ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብረሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 200፡፡

አብርሃም ታደሰ፡፡ " የሲዳማ ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት "፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 1998ዓም፡፡

Asebe Regassa Debelo. "Ethnicity and Ethnic Relation ; The Ethiopian Experiment and The case of GUji and Gedeo." Thesis Submitted For The Degree of Master of Philosophy in indigenous study, University of Toromso , 2007

Barber, Karin. Text and Performance in Africa, Project Muce . *Oral Tradition*, 20/2, 2005, (pp 264-,277).

Bauman, Richard and Charles L Brigs. "Poetics and Performance As Critical Perspective on Language and Social Life." Annual Review Of Anthropology, vol19, (1990), pp59-88

Baum, Richard. "Folklore, Cultural Performances and Popular Entertaiments", A Communication Centered Handbook. Newyork: Oxford University press,1992.

__"Methods Cultural Context of meaning", In A Handbook of American Folklore. Dorson, Richard, M, (ed), 1983.

Bauman, Richard. "Verbal art as performance." American Anthiropologist , New series vol77,no2, 1975, pp290-310.

Bell, Catherin. Ritual Perspective and Dimension . Oxford: Oxford University Press ,1997.

Benamos, Dan" Context in Context.", westeren folklore,vol,52, no214, 1993, PP 209-226.

Bernard, Cook and Garry Macy, Christian Symbol and Ritual an introduction, Oxford: Oxford university press ,2005.

Brown, Peter. "The Rise and Function of Holyman in Late Antiquity." The Journal of Roman Studies, vol. 61 (1971): 80-101. http://www.jstor.org (Accessed Jan 21, 2003)

Campbell, Joseph. The Hero with a Thousand Faces. Princeton: Princeton University Press, 2004.

Christalla, Y. & Stefan, W. Conflict Resolution: Theories and Practice. London: Rutledge. 2011.

Dagne Shibru. "Marriage and Family System Among Gedeo of Southern Ethiopia." Un Published MA Thesis, 1995.

Demise Woressa. "Gedeo Traditional, Social and Legal Organisation." Sociology and and Social Administration, Un Published MA Thesis,1988.

Dorson, R. (Ed). Handbook of American Folklore, Bloomington: Indiana University Press, 1983.

Frank, A.Salamone(eds), Encyclopedia of religious rites Rituals and Festivals. 2004.

Flick, Uwi. An Introduction To Ultimate Research. London: Sage Publication Ltd,2007.

Gray. E .David. Doing research In The Real world, Sage Publications, London: Thousand oaks', New Delhi,2004.

Goldstean, Kenneth. *A Guide Fore Field Workers' in Folklore.* Hatboro: Folklore AssociationsInc, 1964.

Grimes, L.Ronald,. Deeply into The Bone Reinventing Rites of Passage. California: University of California Press, 2000.

Jason, Heda ." Texture Text and Context of the Folklore. Text vs. Indexing." Journal of folkloreresearch , vol 34no 3 Indiana university press (pp221-225).

Martha ,C.Sims and Martin Stephens. Living Folklore an Introduction to the

Study of People and their Traditions . Utah: Utah State University Press , 2005.

Myrvold, Kristina. Inside The Gurus Gate Ritual Uses Text Among The skins in Varanasi. Sweden: University Lund, 2008.

Paulos Alemayehu. "Potentials and Challenges Of Indigenous Institution for good governance : The case of Gada among Gedeo." In Partial Filfilments of degree of Masteres of arts in Sosial Anthropology, Adiss Abbaba university, 2005.

Rappaport, A.Roy. Ritual and Religion in the Making of Humanity . Cambridge: Cambridge University Press, 1999.

Robert, A. Segal(edsl).The Black Well Companion to the Study of Religion. . United Kingdom: Black Well Publishing .ltd.2006.

Scoot, Mitchell. Conflict, Social Change and Conflict Resolution. United Kingdom: Black Well Publishing 2005

Thomas, A. Green. Folklore an Encyclopedia of Beliefs Customs, Tales ,Music and Art, SantaBarbara , California,1997.

Turner, Victor. The Ritual Process Structure and Anti Structure. USA: Cornel Paper Backs, 1991.

Vandaerstoep, and Deirdre Ohnston. Research Methods for Every Day Life. Sanfransisco ; J0ssey Bass,2009.

## አባሪ አንድ፡- ጸሎት እርግማንና ምርቃት

### ጸሎት

| | |
|---|---|
| *Ati laqqaatevven* | *አንተ ሰሚ ነህ* |
| *Ati dhuggaaten* | *አንተ እውነት ነህ* |
| *Ariddu heqqitetexxee* | *ህዝብህን አስጠብክ* |
| *Olaa heqqitetexxee* | *ጎረቤቶቻችን አስጠብክ* |
| *Bogga heqqitetexxee* | *ሀገራችን አስጠብክ* |
| *Gossa heqqitetexxee* | *ብሄሩን አስጠብክ* |
| *Galateefan taanen* | *እናመሰግንሀለን* |

| | |
|---|---|
| Ee maggienno | አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ |
| Techixxe bukkia kini | ለዛሬው ጉባኤ ደግሞ |
| Afi no'oxxe oddon affemi | አንተን እንለምንሀለን |
| Ati dhuggaateni duugaa | አንተ በመካከላችን ተገኝ |
| Haqsonanosha gargaor | እውነቱን እንናገር ዘንድ አንተ እርዳን |
| Fuggokao naapha maddeten Liisi | ክፉውን ያዝልን |
| Arada nageedi | ህዝብህን ጠብቅ ሰላምን ስጥ |
| Alaa nageedi | ለጎረቤት ሰላም ስጥ |
| Boga nageedi | ለህገራችን ሰላም ስጥ |
| Mootuma nageedi | ለመንግስታችን ሰላም ስጥ |

| | |
|---|---|
| *Bukki no'oxxa sanfee* | ጉባኤያችንን ጀምረናል |
| *Nen muunxxano qiccon* | እስከፍጻሜው አንተ ከኛ ጋር ሁን |
| *Atinion weltihethe* | |

### *ሆላ(እርግማን)*

| | |
|---|---|
| *Ee-maggeno* | *አቤቱ እግዚያብሔር ሆይ* |
| *Ati Ardiin maggenon* | *አንተ የህዝብ አምላክ ነህ* |
| *Ardi kin noon kulainien* | *ህዝብህ ወደኛ ስሞታ እያቀረበ ነው...* |

| | |
|---|---|
| *No'o manjoven* | *እኛ ሰዎች ነን* |
| *Ati magenooen* | *አንተ አምላክ ነህ* |
| *No'o anfabenon* | *እኛ አላየንም* |
| *Noo egenebenon* | *እኛ ሊባውን አናውቅም* |
| *Yaane kini* | *ነገር ግን* |


| | |
|---|---|
| *Ati afelden* | አንተ አይተሀል |
| *Ati ejendaten* | አንተ ታውቃለህ |
| *Baxxeexxa karra Anavee atiliisi* | የጠፋውን ንብረት አንተ ለባለንብረቱ ተካለት |
| *Mooreeva yin Ati lekka abid...* | የሰረቀውን ደግሞ አንተ እግሩን ያዝልን... |
| *... Issi doo do'o waali* | እግዚያብሄር ሆይ አንተ አፍዝዘው |
| Ati vin moodhalchi | አንተ ደግሞ ሌባው |
| Doodoi | ፍዘዝ። |
| Tutum | ዶልዱም (ደንዝዝ)። |
| Latoxxeie | አያሳድግህ። |
| bai | ያጥፋህ። |
| *Eemaggenno* | አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ |
| *Ati kadla no'oxxalaqfe* | ልመናችንን ስምተህ |
| *Galatta adhitatobe kaddi* | ለምስጋና አብቃን። |
| *Ee-maggeno* | አቤቱ እግዚያብሔር ሆይ |
| *Ati Ardiin maggenon* | አንተ የህዝብ አምላክ ነህ |
| *Ardi kin noon kulainien* | ህዝብህ ወደኛ ስሞታ እያቀረበ ነው... |
| *No'o manjoven* | እኛ ሰዎች ነን |
| *Ati magenooen* | አንተ አምላክ ነህ |
| *No'o anfabenon* | እኛ አላየንም |
| *Noo egenebenon* | እኛ ሌባውን አናውቅም |
| *Yaane kini* | ነገር ግን |
| *Ati afelden* | አንተ አይተሀል |
| *Ati ejendaten* | አንተ ታውቃለህ |
| *Baxxeexxa karra Anavee atiliisi* | የጠፋውን ንብረት አንተ ለባለንብረቱ ተካለት |
| *Mooreeva yin Ati lekka abid...* | የሰረቀውን ደግሞ አንተ እግሩን ያዝልን... |
| *... Issi doo do'o waali* | እግዚያብሄር ሆይ አንተ አፍዝዘው |
| Ati vin moodhalchi | አንተ ደግሞ ሌባው |
| Doodoi | ፍዘዝ። |
| Tutum | ዶልዱም (ደንዝዝ)። |
| Latoxxeie | አያሳድግህ። |
| bai | ያጥፋህ። |
| *Eemaggenno* | አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ |
| *Ati kadla no'oxxalaqfe* | ልመናችንን ስምተህ |
| *Galatta adhitatobe kaddi* | ለምስጋና አብቃን። |

ምርቃት


| | |
|---|---|
| *Ee-mageno* | አቤቱ እግዚያብሄር ሆይ |
| *Ulfeesee'en* | እንዳከበረን እሱን አክብረው |
| *Htiissooulfeesi* | |
| | |
| *Ardileigal* | በህዝብ መሃል ያኑርህ/ሽ |
| *Hori* | እግዚያብሄር ያብዛህ(ያስፋህ) |
| *Nophi* | ያሳድግህ |
| | |
| *Fubba Sai* | እግዚያብሄር በትልቁ ያስብህ |
| *Fuggokiati* | ክፉውን ከፊትህ ይሰውርልህ |
| *Eddothedho qqe* | |
| *Mongile birrasai* | ቤተሰብህን ያብዘልህ |
| *Horile birrasai* | ከብቶችህን ያብዛልህ |
| | |
| *Karat birrasai* | ሃብት ንብረትህን ይባርክልህ |
| *Orrri Atia ba* | |
| *Nemoo* | ያሰብከውን ሁሉ ያሳካልህ |
| *Ittatolea* | የምትበላው አያሳጣህ |
| *Gophottoo* | |
| | |
| *Hawitatora* | የምትጠጣውን አያሳጣህ |
| *Soprotteie* | |
| | |
| *Mageni Ataa* | እግዚያብሄር በህዝብህ መካከል ሞገስን ይስጥህ |
| *Saaehanauwo* | |
| | |
| *Maggenno* | እግዚያብሄር ሆይ በረከትህ ከበረከታችን ይበልጣል |
| *Noixxe eebababan* | |
| | |
| *Atixne Saxxuen* | ስለህዝብህ አንተ እሱን /እሷን ባርከው/ ባርካት |
| *Atiisso eebisi* | |

## አባሪ ሁለት፡- ፎቶግራፎች


ፎቶ ግራፍ አንድ፡- የገደብ ሶንጎ ከፊል ገጽታ



ፎቶ ግራፍ ሁለት፡- ሶንጎ ግቢ ውስጥ የሚገኘው የበትር ማስቀመጫ ቦታ



ፎቶ ግራፍ ሶስት፡- ሃዩዎችና ምዩዎች በጸሎት ስነስርአት ወቅት




ፎቶ ግራፍ አራት፡- ታዳሚዎች በጸሎት ስነስርአት ወቅት




ፎቶ ግራፍ አምስት፡- ሆላ የሚባልላት ሴት ጸሎት ስትቀበል



ፎቶ ግራፍ ስድስት፡- አጥኝዋ ከግጭት አፈታት ስነስርአት ታዳሚወች ጋር



ፎቶ ግራፍ ሰባት፡- የግጭት አፈታት ስርአተ ክዋኔ ታዳሚዎች በከፊል



ፎቶ ግራፍ ስምንት፡- የአፍ እላፊ የተቀጡ ሰው ብሩን ገቢ ሲያደርጉ



## ባሪ ሶስት፡- የመረጃ ሰጭዎች መረጃ

| . | ስም | እድሜ | የሚኖሩበት ቦታ | መረጃውን የሰጡበት ቀን | መረጃውን የሰጡበት ቦታ | የሙያ መስክ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| . | ጥላሁን እብዶ | 64 | ዲላ | 30/05/2005 ዓ.ም | ዲላ | በጌዴኦ ባሌ ቦባሳ |
| . | ምጃኔ ጎበና | 73 | ገደብ | 22/06/2005 ዓ.ም | ገደብ | አርሶ አደር |
| . | ተካ ቦሩ | 64 | ዲላ | 26/05/2005 ዓ.ም | ዲላ | ጡረተኛ |
| . | ታዮ ሞላ | 32 | ገደብ | 08/06/2005 ዓ.ም | ዲላ | መምህር |
| . | ሀይቻ ቦሩ | 70 | ገደብ | 02/06/2005 ዓ.ም | ገደብ | ነጋዴ |
| . | አቶ ዳንኤል | 33 | ቡሌ | 07/06/2005 ዓ.ም | ቡሌ | የባህል ቢሮ ሰራተኛ |
| . | ወይዘሮ አስረሴ ማሙሽ | 43 | ዲላ | 23/08/2005 ዓ.ም | ዲላ | መምህርት |
| . | አቶ ቴሮ ጃርሶ | 65 | ገደብ | 02/06/2005 ዓ.ም | ገደብ | አርሶ አደር |
| . | አቶ ቹምብሮ ሃለቻዮ | 52 | ገደብ | 19/06/2005 ዓ.ም | ገደብ | አርሶ አደር |
| . | መንገሻ ሀርባዮ | 68 | ዲላ | 23/06/2005 ዓ.ም | ቡሌ | ጡረተኛ |
| 0. | አቶ ጀቦ ኩራ | 73 | ገደብ | 02/06/2005 ዓ.ም | ገደብ | ነጋዴ |
| 1 | አቶ ቂምቢ ዲማ | 80 | ቡሌ | 20/08/2005 | ቡሌ | ጡረተኛ ወታደር |
| 2 | አቶ አላኮ ዳዮ | 65 | ቡሌ | 20/08/2005 ዓ.ም | ቡሌ | ነጋዴ |
| 3 | ሞኮና በሻህ | 74 | ቡሌ | 20/08/2005 ዓ.ም | ቡሌ | ነጋዴ |
| 4 | ኢብዶ ዋቆ | 69 | ቡሌ | 20/08/2005 ዓ.ም | ቡሌ | ጡረተኛ |

## ባሪ አራት፡- ለቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በብሄሩ ውስጥ ምን ምን አይነት ግጭቶች ይፈጠራሉ?
2. በሽምግልና ስርአት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡ እነማን ናቸው?
3. ሽማግሌዎች በምን መስፈርት ነው የሚመረጡት?
4. የሽማግሌዎቹ የስራ ዘመን ገደብ አለው? ካለው ስንት አመት?
5. ለዳኝነትና ሽምግልና አይበቁም ተብለው የማይመረጡ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ ? ካሉ እነማን ? ለምን?
6. ግጭት ሲፈጠር መጀመሪያ ለማን ነው የሚነገረው?
7. ነጋሪው ማን ነው?
8. እንዴት ነው የሚናገረው?
9. ግጭት ሲፈጠር ምርመራ አለ? እንዴት ነው የሚመረመሩት?
10. ሽማግሌዎች ምስክሮችን ጠርተው ቃል ይቀበላሉ?
11. ግጭት ወደ ሽማግሌዎች ሳይቀርብ የሚከናዎን ተግባር አለ?
12. ግጭት እንደተፈጠረ ወንጀለኛው አስቀድሞ ካመነ የፍትህ አሰጣጡ ምን ይመስላል?
13. የሃገር ሽማግሌዎች ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ ምን ይመስላል?
14. ውሳኔ አሰጣጡን በበላይነት የሚመራ የሀገር ሽማግሌ አለ?
15. ሽማግሌዎቹ ውሳኔያቸውን ለባለጉዳዮች የሚያስረዱት እንዴት ነው?
16. የውሳኔ ማሳወቂያ ስርአተ ክዋኔ አለ?
17. የውሳኔ መናገሪያ የተለየ ስፍራ አለ?
18. በዚህ ሂደት ምንምን አይነት ፎክሎሮች አሉ?
19. እነዚህ ፎክሎሮች በሀገር ሽማግሌዎችና በማህበረሰቡ መካከል ምንምን አይነት እውቀቶች ይተላለፉባቸዋል?
20. በብሄሩ ውስጥ በመደበኛውና በባህላዊው የግጭት መፍቻ ተቋም መካከል ምን አይነት ግንኙነት አለ?
21. የፍትህ ተቋሙ አሁን ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል?
22. ከመደበኛው የፍትህ ተቋምና ከባህላዊው የፍትህ ተቋም የትኛው የበለጠ ተቀባይነት አለው?
23. በባህላዊው የፍትህ ተቋም ውስጥ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ለማጽናት የሚጠቅሙ የእብነት ታሪኮች አሉ? ካሉ ታሪኮቹ ቢቀርቡ?

ጌዴኦ ብሄር የግጭት አፈታት ስርአት በሚል የተሰራው ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የራሴ ወጥ
ራ መሆኑንና ከሌላ ምንጭ ወስጄ የተጠቀምኩባቸውን ማንኛቸውንም አይነት ስራዎች
ተገቢው ሁኔታ የጠቀስኩ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ሕሊና ሰብስበው